**DSpace Institution**

**DSpace Repository** **http://dspace.org**

Folklore/Cultural Studies Thesis and Dissertations

2015-09

# þÿ è 4 u • u “ ð ð ë C % } u • p “ ` ð e
# þÿ ¨ p

þÿ ` “ , ð c D

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/14687

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

የፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞች ትንተና በደብረታቦር ከተማ

በሀና ደባልቄ

መስከረም፣ 2015 ዓ.ም

ባሕር ዳር፣ ኢትዮጵያ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

የፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለሁለተኛ ዲግሪ የቀረበ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

# የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞች ትንተና በደብረታቦር ከተማ

በሀና ደባልቄ

አማካሪ አስቴር ሙሉ (ዶር)

መስከረም፣ 2015 ዓ.ም

ባሕር ዳር፣ ኢትዮጵያ

**ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩሚኒቲስ ፋኩሊቲ**

**ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር**

**የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞች ትንተና በደብረታቦር ከተማ**

**በሀና ደባልቄ**

**አማካሪ÷ አስቴር ሙሉ (ዶ/ር)**

**የፈተና ቦርድ አባላት፣**

**አማካሪ**

**ስም……………………………ፊርማ…………………ቀን…………**

**የውስጥ ፈታኝ**

**ስም……………………ፊርማ……………ቀን……………**

**የውጭ ፈታኝ**

**ስም………………….. ……ፊርማ……………………ቀን………**

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህን የጥናት ስራ በተገቢው መንገድ እንዲጠናቀቅ የድጋፍና ክትትል እንዲሁም እርማት ታደርግልኝ ለነበረችው ለአማካሪዬ ለዶ/ር አስቴር ሙሉ ባለችበት ምስጋናዬ ይድረሳት፡፡ በመቀጠል ለዚህ ስራ መሳካት በመስክ መረጃ ሲቀብሉኝ ለነበሩ አብይና አጋዥ የመረጃ ምንጮቼ ላቅ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ በመጨረሻም በሃሳብም ሆነ በሌሎች መሰል ድጋፎች ከጎኔ ለነበሩ ውድ ባለቤቴ ይበልጣል ገላነው እና ልጄ አሐዱ ይበልጣል በተጨማሪም ቤተሰቦቼና ጓድኞቼ ላቅ ያለ አክብሮቴ ይድረሳቸው፡፡

# ማውጫ

ምስጋና ........ i
አጠቃሎ ........ vii
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 2
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4
1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 5
1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 6
1.5. የጥናቱ ወሰን ........ 6
1.6. የጥናቱ አደረጃጀት ........ 7
1.7. የጥናቱ ዘዴ ........ 8
1.7.1 የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........ 9
1.7.1.1 የተጠኚ ናሙና መረጣ ........ 9
1.7.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........ 9
1.7.2.1.ምልከታ ........ 10
1.7.2.2. ቃለ መጠይቅ ........ 11
1.7.2.3. ተተኳሪ የቡድን ውይይት ........ 12
1.7.3. የመረጃ መተንተኛ እና መተርጎሚያ ዘዴ ........ 14
1.7.4. የመስክ ቆይታ ........ 15
1.7.4.1. በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ........ 16
1.7.4.2. የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 17
ምዕራፍ ሁለት ........ 18
2. ክለሳ ድርሳን ........ 18
2.1. ንድፋ ሃሳባዊ ማዕቀፍ ........ 18
2.1.1. እንስታዊነት ንድፍ ሃሳብ ........ 18
2.1.2. ተግባራዊ ንድፍ ሃሳብ ........ 19
2.2. ፅንስ ሃሳባዊ ማዕቀፍ ........ 21
2.2.1. የስነ ቃል ምንነት ........ 21


2.2.2. የቃል ግጥም ምንነት ....................................................................22
2.2.3. የቃል ግጥም ባህርያት ....................................................................24
2.2.4. የቃል ግጥም ፋይዳ....................................................................24
2.2.5. የእንስታዊነት ወይም የሴትነት ምንነት....................................................................25
2.2.6. ማህበራዊ ሚና ....................................................................26
2.3. የተዛማጅ ፁሁፍ ቅኝት ....................................................................27
ምዕራፍ ሶስት ....................................................................31
3.የደብረታቦር ከተማ አካባቢያዊና ማህበረ ባህላዊ መልክ ....................................................................31
3.1. የከተማው አጭር ታሪክና የህዝብ ሁኔታ ....................................................................31
3.1.1. የከተማው የአየር ፀባይና መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ ....................................................................32
3.2. ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረዳጃ እና ዝምድና መፍጠሪያ ተቋማት ............33
3.2.1. እድር ....................................................................34
3.2.2. እቁብ ....................................................................35
3.2.3. ወንፈል ....................................................................35
3.2.4. የቤተሰብ አመሰራረት ....................................................................36
3.2.5. የሴቶች የስራ ሃላፊነት....................................................................37
3.2.5.1. የልጅ አስተዳደግ ስልት ....................................................................37
3.2.5.2 የቤት አያያዝ ወይም ስነ ውበታዊ ጉዳዮች....................................................................38
3.2.5.3. የሴቶች ማህበራዊ ኑሮ....................................................................39
ምዕራፍ አራት ....................................................................40
የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞች ትንተና ....................................................................40
4.1. በደብረታቦር ከተማ ማህበረሰብ በቃል ግጥሞች አማካኝነት የሚገለጡ የሴቶች ሚናዎች....................................................................40
4.1.1. ከተፈጥሮ ወይም ከእንስታዊነት አንፃር ሚገለጡ የሴቶች ሚና............41
4.1.2. ከስራ ወይም ማህበራዊ ተግባራት አንፃር የሚገለጡ የሴቶች ሚና.......42
4.2. የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞች....................................................................49
4.2.1. ጥንካሬና ብርታትን የሚገልፁ ....................................................................49
4.2.2. መልካምነትን የሚያሳዩ ቃል ግጥሞች....................................................................53
4.3. ቃል ግጥሞቹ ለተተኳሪ ማህበረሰብ የሚያስገኙት ፋይዳ ....................................................................57
4.3.1. ስነ ልቦናዊ ፋይዳ....................................................................58

4.3.2. ተግባራዊ ፋይዳ ....................................................................60
4.3.3. ማህበራዊ ፋይዳ....................................................................61
ምዕራፍ አምስት........................................................................63
5.ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሃሳብ...................................................63
5.1. ማጠቃለያ ........................................................................63
5.2. የይሁንታ ሃሳብ ...................................................................64
ዋቢ መፅሀፍት..........................................................................66
አባሪ1. በአካባቢው የሚዜሙ የፍቅር ቃል ግጥሞች ...........................69
አባሪ 2. አብይ የመረጃ ምንጮች÷ ...............................................71
አባሪ 3. አጋዥ የመረጃ ምንጮች፤ ...............................................71

ደብረ ታቦር




**ምስል 1፡- የደብረ ታቦር ክተማን የሚያሳይ የደቡብ ጎንደር ዞን ካርታ** (ከዞኑ ካርታና ፕላን መምሪያ የተወሰደ)




**ምስል 2፡- ተጠኞቹን ቀበሌወች የሚያሳይ የደብረ ታቦር ከተማ ካርታ**

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የሴቶችን ሚና ማደላደያ የሚያሳዩ ቃል ግጥሞች መመርመር በሚል ርዕስ ጥናት የተደረገ ነው። ይህንን ዋና ዓላማ መሰረት በማድረግ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎችን አካቶ ይዟል። በቃል ግጥሞች የሚገለጡ የሴቶችን ሚናዎች መለየት፣ማደላደያ ቃል ግጥሞችን መግለፅ እና የሴትንት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞችን ፋይዳ ማሳየት የሚሉት ናቸው። ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ጥናቱ ትኩረት ባደረገበት በደብረታቦር ከተማ በሚገኙ ቀበሌዎች በምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መረጃዎች ተሰብስበዋል። በመስክ ላይ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች በሁለት ዋና ዋና አርዕስቶች ከተፈጥሮ ወይም ከፆታዊ ሚና እና ከስራ ተሳትፎ የሚገለፁ፣ የሴትነትና ፆታዊ ሚናን የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ የማህበረሰብ ክፍፍሎችን፣ድልድሎችን በሚያሳዩ ልማዳዊ ህጎች መሰረት ሴትን ለማደላደል የሚዜሙ ቃል ግጥሞችን በይዘትና በጭብጥ የተከፈሉ ሲሆን የሚዜሙ ቃል ግጥሞች ደግሞ ጥንካሬን ተሳትፎን የሚገልፁ፣ መልካምነትና ወይም ፆታዊ ሚናን በሚሉ ጭብጣዊ መከፋፈያዎች ከእንስታዊነትና ተግባራዊ ፋይዳቸዉ አንፃር ተደራጅተው ቀርበዋል። በዚህም ጥንካሬንና ብርታትን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች በማህበረሰቡ ውስጥ ሴቶች በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መዋቅራዊ ስርዓቶች ከወንዶች በተለየ መልኩ ያላቸውን የጥንካሬ ሚና የሚያሳዩ ናቸው። መልካምነት የሚያወሱ ደግሞ ከሴትነታቸው ወይም ከፆታዊ አንፃር ለልጅ አስተዳደግ፣ ጥሩ ቤተሰብ ለመመስረትና በመልካም ስነ ምግባር ልጆችን ለማነፅ ያላቸው ጉልህ ድርሻ የሚያስርፁ ሲሆኑ ስለፆታዊ ሚና የተቀኙ ቃል ግጥሞች ደግሞ የሴትነት ሚናቸውን በስራ፣ በማህበራዊ ግንኙነቶች የመረዳዳትና የመተሳሰብን ፅንስ ሃሳብ የሚያስረዱ ናቸው። በእያንዳንዱ ምድብ በተደረገው ትንተና መሰረት፣ ጥናቱ ከደረሰባቸው ግኝቶች መካከል የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው። የጥንካሬና የብርታት ቃል ግጥሞች ሴቶችን በብርታታቸው የሚያደላድሉና የሚያሞግሱ እንዲሁም ከጀግንነትና ከኃላፊነት ጋር ተያይዘው የተተነተኑ ናቸው። በመልካምነት የቀረቡት ግጥሞች ሴት እናት፣ እህት፣ ሚስት፣ አያት፣አይት ወይም ምራት፣ አክስት፣ ጓደኛና አማት በምትሆንበት ጊዜ ለወንዶች አርያ ስለመሆናቸው ለጥሩ ቤተሰብ መመስረት ሚና መኖራቸውን የሚያሳዩ ናቸው።

ከፆታዊ ሚና አንፃር የቀረቡት ደግሞ ከሴቶች የሙያ ባልትና፣ ማህበራዊ ግንኙነቶች፣ ከቁጠባና ከፆታዊ ሚና ጋር በተገናኘ ነው፡፡ በአጠቃላይ ቃል ግጥሞቹ የሴቶችን በማህበረሰብ ውስጥ የሚኖራቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ታሪካዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ባህላዊና መዋቅራዊ የማደላደያነት ሂደቶችን የሚያሳይ ስለሆነ የሚመለከታቸው የማህበረሰብ አጥኝዎች፣ የታሪክና የስነ ስብ ተመራማሪዎች የስነ ፀሁፍ ባለሙያዎች፣ የትምህርት ባለሙያዎች፣ የፖለቲካና የአስተዳደር ሰዎች ወ.ዘ.ተ ይህንን ጥናት እንደመነሻ በመጠቀም የሴቶችን ፆታዊ ሚና የሚያደላድሉ ቃል ግጥሞችን በሚገባ በማስረፅ ማህበረሰቡን ለማስተዳደርም ሆነ ለእድገትና ለልማት ቢገለገሉበት የተሻለ ይሆናል፤ የሚሉ የመፍትሄ ሃሳቦችም ተቀምጠዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ይህ ጥናት ተተኳሪ ማህበረሰብ እንደ ሌሎች አካባቢ ቡድኖች ሁሉ ስነ ልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ሁነቶችን ለማሳደግ፣ ማህበራዊ መዋቅሮችንና ስርዓቶችን ወይም ተግባሮችን ለማስቀጠል ቃል ግጥሞችን እንደ አንድ መሳሪያ ይጠቀሙበታል። ቃል ግጥም የአንድን ማህበረሰብ የአመጋገብ፣ የኗኗር ስልትን፣ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለማስተሳሰር፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ ገፅታዎችን ለማንፀበረቅ የሚዉል የስነ ቃል ዘርፍ ነው። ቃል ግጥም ሴቶችን በቡድኑ ውስጥ የሚኖራቸውን እንቅስቃሴ፣ ሚና፣ ማህበራዊ ደረጃና ከፍታ ከተለያዩ ክስተቶች ጋር በማዛመድ ይቀኙበታል። ይህ ቃላዊ ቅኝትም ቃል ግጥሞቹ ከህዝቡ የአኗኗር መልክ የተፈጠሩና ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ ናቸው። ይህን በተመለከተ ፈቃደ (1991፣86) ሲገልፅ÷ «ይህ ህዝባዊ ግጥም በአንድ ሰው ተደርሶ በመዜም፣ በመከወንና በመተላለፍ የህዝብ ሊሆን ይችላል»፤ በማለት ያስረዳል። ይህም ማለት ቃል ግጥሞች ከሰው ልጆች ማህበራዊ መስተጋብር የሚመነጩና በግለሰብ ተደርሰው በህዝቡ የሚከወኑ እንደሆኑ መረዳት ይቻላል። በተተኳሪ ማህበረሰብ ከሚዜሙ ቃል ግጥሞች መካከል ከስራ፣ከፍቅር፣ ከጦርነት፣ ከደስታና ከፆታዊ ሚና አንፃር የሚዜሙ ይታወቃሉ።

እነዚህም በአካባቢው የሴትነትን ሚና ለማደላደልና ማህበራዊ ደረጃቸውን ለማሳየት የሚዜሙ ቃል ግጥሞች ከዜማና አዝናኝ ስሜት ከመፍጠር ባሻገር በማህበረሰቡ ስነ ልቦናዊ ጉዳዮችን ለማጠናከር፣ማህበራዊ መዋቅሮችንና ልማታዊ እሳቤዎችን ለማስረፅ ጉልህ ድርሻ አላቸው። አቢሲኒያ መዝገበ ቃላት ሲገልጸው፤ ማደላደል ማለት ማስተካከል፣ ማከፋፈል እና ተስተካክሎ እንድቀመጥ ማድረግ ማልት ሲሆን ወቅትንና ጊዜን መሰረት በማድረግ የሚቀርቡ ቃል ግጥሞች ሴት ልጅ በማህበረሰቡ በሚቀመጡ ደረጃዎች የሚኖራት ሚና ለሌሎች የቡድን አባላት መልካም ተግባራትን በማካፈል፣የሚወለዱ ህፃናት፣ ወንዶችንና የሚያገቧቸውን ባሎች በግብር፣ በሁኔታ በመቅረፅና በማስተካክል ወይም በማደላደል የሚገለጡ ሚናዎችን በማሳየት አስተዋፆኦ አላቸው።

ተተኳሪ ማህበረሰብ በስራ፣ በክብረ ባዓላት፣ በእርግዝናና በውልደት ጊዜ ወ.ዘ.ተ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉን የሀዘን ይሁን የደስታ የርዕስ በርዕስ ግንኙነቶችን ለማደላደልና ለማስቀጠል ይጠቀሙባቸዋል፡፡ በመሆኑም በተተኳሪ ማህበረሰብ የሚዜ ቃል ግጥሞች በሴቶች የህይወት መንገድ ውስጥ ላይ የሚኖራቸውን ከእንስታዊ እና ከተግባራዊ አስተዋፆኦዎች አንፃር ለመመርመር ሲባል ከሌሎች አካባቢዎች በተለየ መልኩ፤ በመታዘብ ጥናት ማድረግ ችያለሁ፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ስነ ቃል በቋንቋ አማካኝነት የሚተላለፍ የሰው ልጅ ኪናዊ ተግባቦቶችን ለማንፀባረቅ የሚያስችል የፎክሎር ዘውግ ነው፡፡ ይህንንም በተመለከተ ዘሪሁን (2005፣20) ሲገልፅ፡-

> ስነ ቃል በመነገር፣ በመተረት ወይም በመዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከዎን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያና ልዩ ልዩ ክስተቶችንና የህይወት መስኮችን መግለጫ ኪነ-ጥበብ ነው፡፡ በስነ ቃል ህዝቦች ማንነታቸውን ያሳዉቁበታል፣ የዝርያቸውን አመጣጥ ይተርኩበታል፤ስለ አካባቢያቸው በአጠቃላይ ስለ አለማቸው ያላቸውን ፍልስፍና ይቀር ጹበታል፡፡ ስነቃል ወግና ልማዳቸውን አጠንክረው የሚያቆዩበት ዋነኛ መሳሪያቸው ነው፡፡ ሀዘን ደስታቸውን፣ ምኞት ተስፋቸውን፣ ፍቅር ጥላቻቸውን፣ድል ሽንፈታቸውን፤ ድጋፍ ተቃውሟቸውን በአጠቃላይ የህይወታቸውን መልኮች ያንጸባርቁበታል፡፡ ታሪካቸውን በተከታዮቻቸው በማስተላለፍ የዝርያቸውን ተከታታይነት ያረጋግጡበታል፤በማለት ያስረዳል፡፡

ከዚህም አንፃር ስነ ቃል በመናገር፣ በመዜምና በመንጎርጎር በቃል የሚፈጠር ሲሆን የራሱ የሆነ የመከወኛ አጋጣሚ፣ ከዋኝና ታዳሚ ያለው ሲሆን በዚህ ፈጠራ ህዝብ አመለካከቱን፣ ስሜቱን፣ ፍላጎቱን፣ ድጋፍና ተቃውሞውንና አጠቃላይ የህይወት ገፅታቸውን መግለፅ የሚያስችል የጋራ እወቀት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ በተጨማሪ ሰለሞን (2007፣80) ሲገልፅ÷‹‹ስነ ቃል በሰው ልጅ የእርስ በእርስ

መስተጋብር ወቅት ወይም በተወሰኑ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚቀርብ የህዝብ የፈጠራ ውጤት ሲሆን ቃላዊ ተስተላልፎን መሰረት በማድረግ በትውስታ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገር የፎክሎር ዘርፍ ነው››፡፡ ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው ስነ ቃል የሰው ልጆችን ሕልውና መግለፅ የሚያስችል መሆኑን እና ለመከዎን አንድ ምክንያትና አጋጣሚ የሚፈልግ ቃላዊ ጥበብ ነው፡፡ እንዲሁም ማህበረሰቡ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው ያስተዋላቸውን እና ያጋጠሙትን ገጠመኞች እንዲሁም የተሰማውን ስሜት የሚያንፀባርቅበት ሲሆን በማስታዎስ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ የእውቀት አይነት ነው፡፡ በስነ ቃል አያሌ የሰው ልጅ የህይወት ክፍሎች፣ ፍልስፍናዎችና እምነቶች ይገለፃሉ፡፡ በዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው ተተኳሪ ማህበረሰብ ስርዓተ ፆታ ላይ ያላቸው አመለካከትና እምነት በስነ ቃል ከሚገለፁ ሀሳቦች ውስጥ አንዱ በሆነው ቃል ግጥም ነው፡፡ በቃል ግጥም የሴቶች ጀግንነት፣ ድክመት፣ የቤት ውስጥ ሀላፊነት፣ ሩህሩህነት በማህበረሰብ ውስጥ ያላቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ተግባራዊና መዋቅራዊ ፋይዳና ሚና፤ ማህረሰቡ ስለ ሴቶች ያለው አመለካካት ወ.ዘ.ተ የሚገለፅበት ስነ ቃላዊ ፈጠራ ነው፡፡ ይህ ስነ ቃላዊ ፈጠራ ወይም ቃል ግጥም ምትና ምጣኔ፣ ዜማን መሰረት አድርገው የሚቀርቡ ስነ ቃላዊ ስራዎች ሲሆኑ ቃል ግጥሞች የሰዎችን ስሜት የመንካት ችሎታ ያላቸው፣ አይሬሴ የሆኑ፣ በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች የሚከወኑና የሚቀርቡ የህዝብ ሃብት ናቸው፡፡ ከሚከወኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ወይም አውዶች መካከል ስራ፣ ክብረ በዓላትና ሀዘን በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በነዚህ ማህበራዊ አውዶች ደግሞ ስለሴቶች ሚና ሚቀኙ ቃላዊ ግጥሞች አሉ፡፡ ይህም ማለት በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ለሴቶች የተሰጠ ሀላፊነትና ሚና አላቸው፡፡ ይህ ሀላፊነት እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ከባድ ወይም ቀላል፤ ትንሽ ወይም ብዙ ሊባል የሚችል ቢሆንም፤ በብዙው ሁኔታ ግን ከሴቶች የሚጠበቁ ከፍ ያሉ ሚናዎች መኖራቸውን የጥናት ሰዎች ይገልፃሉ፡፡ ይህን በተመለከ ደበበ (1999፣45) ሲገልፅ÷ “በየትኛውም ማህበረሰብ ሴቶች በሁሉም የስራ መስክ እንዲሁም ማህበራዊ ህይወት እዚህ ቀረ የማይባል ድርሻ አላቸው፡፡ ከቤተሰቦቻቸው ጀምሮ እስከ ማህበረሰቡ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በአብላጫው የህይወትን ውጣ ውረድ የሚወጡት ሴቶች እህቶቻችን ናቸው”፤ ሲሉ ገልፁታል፡፡

ከዚህም አንፃር የሴትነት ሚና ሲባል ሴት የማህበረሰብ አባላት ሁሉ ለቡድናቸው ህልውና መጠበቅ ሲሉ የሚወጡትና የሚከውኑት ሃላፊነትና ተግባር እንደሆነ መረዳት ያስችላል፡፡ ሚናውም በዕድሜ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በጾታ ወዘተ. የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንንም አስመልክቶ Genilloud (2000, 4) ሲያስረዳ÷ የሴቶች ሚና ሙሉ ለሙሉ የሚገለጸው አንድን ጉዳይ በሚከወንበት እና በሚከናወነው ጉዳይ ላይ ማለትም በተከዋኙ እና በከዋኙ መካከል የሚኖረው መስተጋብር እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ስለዚህ፣ሚና በአድራጊው እና በተደራጊው ጉዳይ መካከል በሚደረግ ግንኙነት መሰረት የሚመጣ ሃላፊነት ነው፡፡ የተከዋኙ ጉዳይ ጠባይ የከዋኙን ጠባይ የሚቀርጽ መሆኑንም መረዳት ይቻላል፡፡ በአንድ ማህበረሰብም እንበል ቡድን ውስጥ ግለሰቦች ወይም ንዑሳን ቡድኖች ያላቸው ሚና በተለያዩ መንገዶችና ፈጠራ ስልቶች ሊገለፁ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ መገለጫ መንገዶችና ፈጠራ ስልቶች ውስጥ ቃል ግጥም አንዱ ነው፡፡ ይህ ጥናትም በተተኳሪ ማህበረሰብ ውስጥ የሴቶችን ሚና ለመግለፅ ብሎም ለማደላደል ከሚጠቀምባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ የሆነውን ቃል ግጥም ትንተና ላይ በማተኮር ተሰርቷል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ርዕስ ለማጥናት መነሻ የሆኑ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል በመጀመሪያ ለጥናት ትኩረት ባደረኩበት አካባቢ በመንግስት የስራ መስክ መምህርነት ሙያ ለአምስት አመት ያህል በዙሪያው ስሰራ የቆየሁ ሲሆን በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎችና ህዝብ ከበራዎች ስለሴቶች ሙገሳና ሚና የሚያንፀባርቁ ቃል ግጥሞች ሲደረደሩና ሲዜሙ መስማቴ የእረጅም ጊዜ ትውስታዬ ነበር፡፡ በመሆኑም በአካባቢው ማህበረሰብ ቃል ግጥሞች ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ ልቦናዊ መስተጋብሮችን ለማቃናት የሚኖራቸውን ፋይዳና ሚና ለመመርመር ፅኑ ፍላጎት ስላደረብኝ መነሻ ሆኖኛል፡፡

ሁለተኛም እኔ ባደረኩት ዳሰሳ በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ ድግሪ የተሰሩት ስራዎች በመውሰድ ከእኔ ጥናት ጋር በአንፃሩ ያላቸውን ተመሳሳይነት እና ተዛማጅነት

በመለየት እንዲሁም ያላቸውን ልዩነትና ክፍቶች ለመሙላት ሲባልና በተዛማጅ ስራዎች ላይ ያሉትን ክፍቶች መሙላት አዲስ የማህበረሰብ ገጽታዎችን ለማሳየት፣ የጥናቱን ስልትና ዘዴ ለማጠንከር አነሳስቶኛል፡፡

ሶስተኛው በቃል ግጥሞች አማካኝነት የሚገለጡ የሴቶች ሚናዎችን ምን ምን እንደሆኑ በማሰብና የሰዎችን አመለካከት ለማቅናትም ሆነ ለማሳደግ በጥናት የተረጋገጠ ተጨባጭ መረጃ ለማግኘት በደብረታቦር ከተማ የሚዜሙ የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞችን ተጠግቶ ባጠናው፤ የሚል ፍላጎት ስላደረብኝ እና ከርዕስ አኳያ ትኩረቱ ስለሳበው መነሻ ሁኖኛል፡፡

በተጨማሪም አራተኛው መነሻ ምክንያቴ ደግሞ በአንፃሩ የሴቶች ታሪካዊ ጭቆና፣ ደካማና የበታችነት የሚያዎሱ ሁነቶች አለመቀነሳቸው፤ ለምን? ከዚህ የተለየ አይኖርምን የሚል ሃሳብ በማንሳት ያንን የመፈተሸ ፍላጎት ስላደረብኝ ሴቶች በጀግንነታቸው፣ በእናትነታቸው በሙያቸው፣ በሚስትነትና በእህትነት ያላቸው ሚናና ፋይዳ ምን? እንደሚመስል ለመግለፅ ሲባል ጥናቴን በደብረታቦር ከተማ የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞች ትንተና በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለማጥናት ተነሳስቻለሁ፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞችትንተና መመርመር ነው፡፡ ይህንን ዋና ዓላማ መሰረት በማድረግ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎችን አካቶ ይዟል፡፡

- ❖ በቃል ግጥሞች የሚገለጡ የሴቶችን ሚናዎች መለየት
- ❖ ማደላደያ ቃል ግጥሞችን መግለጽ
- ❖ የሴትንት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞችን ፋይዳ ማሳየት የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

የዚህ ጥናት መጠናት ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንፃር ለጥናት ዘርፉ የሚበረክተው የራሱ የሆነ አስተዋጽዖ ይኖራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከጠቀሚታዎቹም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- በተተኳሪው ማበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሴቶች ያላቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተሰትፎ እና ሚና ሌሎች አካላት እንዲያውቁ እና እንዲገነዘቡ ያደርጋል

- በሴትነት ሚና ማደላደያ ስነ-ቃሎች ውስጥ ያለውን የሴቶች ሚና አቀራረጽ ለማወቅ ለሚፈልግ አንባቢ መረጃ በመስጠት ያገለግላል፡፡
- ሌሎች አጥኚዎች በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ለማካሄድ ቢፈልጉ መረጃን በመጠቀም አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡
- አንድ ህዝብ በየዘመናቱ ያካበተውን እውቀት እና የህይወት ገጠመኝ በቃል ግጥሞች ይቀርሳል ስለሆነም የተጠኙ ማህበረሰብ ዕምነት ዝንባል እና ፍላጎት በማወቅ መልኩ ያለውን የእውቀት ክፍተት ይሞላል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በደቡብ ጎንደር ዞን በደብረታቦር ከተማ የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥምች ለመተንተን የተዘጋጀ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱን በተገቢ መንገድ ለማጠናቀቅ ሲባል በጊዜ፣ በቦታና በአቅም መገደብ ጥናቱን ውጤታማ ያደረገው ዘንድ በደብረታቦር ከተማ አስተዳደር ከሚገኙ ስድስት የከተማና የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ሶስቱ ቀበሌዎች ላይ ትኩረት አድርገያለሁ፡፡ እነሱም፡- አስፋው ግራር ሰፈር፣ ፀጉር ምካኤል እና ህሩይ ናቸው፡፡ እነዚህ ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያት አንደኛው ካለው የጊዜና የገንዘብ እጥረት የተነሳ ሁሉንም ቀበሌዎች ለማካተት አስቸጋሪ ስለሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም የጥናት ክልሉ ወይም ቦታው በሰፋ ቁጥር ከአቅምና ከጊዜ አንፃር አስተማማኝ መረጃ ማግኘት ይከብዳል፤ ብየ በማሰብ እና ነገሮችን በጥልቀት ለመመርመር አያስችለኝም በማለት ነው፡፡ ሌላኛው ምክንያት ደግሞ ትኩረት የተደረገባቸው ቀበሌዎች ሰፊ የህዝብ ብዛት ያላቸው፣ በመሆኑና

በከተማው ውስጥ ከሚገኙት ቀበሌዎች በአንፃሩ ተመጣጣኝ የሆነ የእምነት፣ የሃይማኖት፣ የስራ ክፍፍልና ማህበራዊ ተጋሮዎች ምጥጥን ያሉባቸው እንደሆኑ ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ጥር 30/2014 ዓ.ም በአገኘሁት መረጃ መሰረት ነው፡፡ በተጨማሪም በግሌ ባደረኩት አጠር ያለ ዳሰሳ ጥናት በታለመለት ጊዜ፣ ቦታ እና ገንዘብ እንዲጠናቀቅ ማድረግ አላማውን ለማሳካት መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት ያስችሉኝ ዘንድ በነዚህ ሶስት ቀበሌዎች ላይ ተዎስኛለሁ፡፡

ከይዘት አንፃር ከአራቱ የፎክሎር ዘውጎች ውስጥ ስነ ቃል ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን በስሩ ከሚካተቱት ዝረው ቃል ትረካ፣ አጫጭር ቅርፆችና ቃል ግጥም መካከል የሴቶችን ሚና ለማደላደል በሚዜሙ ቃላዊ ግጥሞች የተመሰረተ ነው፡፡

ስለሆነም፤ ትኩረት ባደረኩባቸው ቀበሌዎች ከሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች በይበልጥ የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥም ትንተና በደብረታቦር ከተማ በሚል ርዕስ ላይ ያተኮረ እና የተወሰነ ነው፡፡

## 1.6. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በደቡብ ጎንደር ዞን በደብረታቦር ከተማ ማህበረሰብ የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞ ትንተናን ለመግለጽ የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህም በምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ዋና ዓላማና ዝርዝር ዓላማ፣ የጥናቱ ፋይዳ፣ ወሰን የጥናቱ አደረጃጀት፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የናሙና መረጣ፣ የመረጃ መሰብሰቤና የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች በዋናነት የተካተቱ ሲሆን ከተመረጡት የመረጃ ምንጮች ከአንዴም ሁለት ጊዜ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በአይነታዊ ምርምር ዘዴ የመረጃ ማጠቃለልና ቅነሳ እንዲሁም ገላጭ የትንተና ስልት ተግባር ላይ ስለ መዋላቸው ተገልጾል፡፡ በመስክ ሂደቱም የተገኙ ተሞክሮዎችን፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍተሄዎች ቀርበዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ደግሞ ንድፍ ሃሳባዊ ማዕቀፍ፣ ፅንስ ሃሳባዊ ማዕቀፍና የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ሲኖሩ በምዕራፍ ሶስት በጥናቱ የትኩረት ክልል እና አዋሳኝ ቦታዎች ላይ አከባቢያዊ ገለፃ ቀርቧዋል፡፡ የማህበረሰቡ መገለጫ የሆኑ ሁነቶች ማህበራዊ እሴቶች የሴቶች የስራ ሃላፊነት፣ የቤት አያያዝና ስነ ውበታዊ ስልቶች፣ የቤተሰብ አመሰራረትና የልጅ አስተዳደግ ስልቶች በዝርዝር

ቀርበዋል። በአጠቃላይ የወረዳውን እና የጥናት ክልሉን የሚጠቁሙ መግለጫዎች ተቃኝተዋል።

በምዕራፍ አራት የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥም ትንተናን ላይ በመስክ ምልከታ እና በተመረጡ ዓብይ እና አጋዥ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን በደረጃ የቀረቡ ሲሆን የጥናቱ ግኝት የሆኑ በቃል ግጥሞች አማካኝነት የሚገለጡ የሴቶች ሚናዎችን፣ የሴትን ሚና የሚያሳዩ ቃል ግጥሞች ከማህበራዊ ተግባርና ከተፈጥሯዊ መልካምነት የሚገልጡ ቃል ግጥሞች ለተተኳሪ ማህበረሰብ የሚሰጡትን ፋይዳ ገፅታዎች በዝርዝር ቀርበዋል። በመጨረሻም በምዕራፍ አምስት ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች ይገኙበታል።

## 1.7. የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋለው አይነታዊ (qualitative) ተብሎ የሚጠራው የምርምር አይነት ነው። አይነታዊ ምርምርን አስመልክቶ Best (1981፣31) ሲገልፅ÷ አይነታዊ የምርምር ዘዴ ያለምንም አሃዛዊ መረጃ ሁነቶችን እና ሰዎችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሊገለፅ ይችላል፤ በማለት ያስረዳሉ።

ከዚህም በተጨማሪ ያለው (1998፣19) "በአይነታዊ ምርምር ተመራማሪው በተወሰነ አንድ ጉዳይ ላይ በማተኮር በጣም ውስን ቁጥር ያላቸው የጥናት ተሳታፊወችን በመውሰድ ያነሳውን ችግር በጥልቀት ከተለያዩ አቅጣጫወች የሚመለከቱበት ነው። ተመራማሪው ለማጥናት የፈለገበትን ጉዳይ በመጠን ሳይሆን በዐይነት የሚገልፅበት ነው" በማለት ያስረዳሉ። ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናትም በቁጥር እና በአሃዝ መረጃዎችን የማይጠቀም ሲሆን ይልቁንስ የሰዎችን አስተሳሰብ፣እውቀት እና እሴቶችን የሚገለፁ መረጃዎች የሚተነተኑብት በመሆኑ አይነታዊ የምርምር ስልቶች (qualitative method) አገልግሎት ላይ ውለዋል።

### 1.7.1 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ ከሚገኘው የጥናቱ አካላይ የተጠኝ ናሙና መረጣ ተካሂዷል፡፡

#### 1.7.1.1 የተጠኝ ናሙና መረጣ

ለዚህ ጥናት መሳካት የተጠኝ ምርጫ ማድረግ ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ ከዚህም አንፃር ዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴን መርጫዩ በማድረግ ተጠቅሜአለው፡፡ አላማ ተኮር የናሙና ዘዴን በተመለከተ ያለው (2004፣ 36) ሲገልፁ፡- "አላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ከጥናቱ ዓላማ አንፃር ነው፡፡ እነማንን ብመርጥ የምፈለገውን መረጃ ለሲጡኝ ይችላሉ፡፡ የሚሉትን ለመመለስና ለማሳካት ሲባል ዓላማ ተኮር ይመርጣል"፤ በማለት ያስረዳል፡፡ ከዚህም አንፃር ዓላማየን ማሳካትና ጥናቱን ውጤታማ ለማደረግ ስል ጥልቅ ግንዛቤ ያላቸውን፣ ለስርዓት ክዋኔው ጉልህ ሚና የሚኖራቸውን ሰዎች በመለየት ከሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥም ጋር ቅርበት፣ ችሎታው ያላቸውን እና ከጉዳዩ ጋር በማስተሳሰር ከሚናገሩ ሴቶችን፣ ረጅም ልምድ ካላቸው አዋቂ ወንዶች፣ አባቶች፣ አዛውንቶችና ተተኪ ሴት ልጃገረዶችን በመለየትና በማጥናት ሳስብ እንደ መረጃው አይነት፣ አሳታፊነት የስብጥር ቡድንም ተጠቅሜአለው፡፡ በአጠቃላይ አይነታዊ የምርምር ስልት በመከተል መረጃዎች በመሰብሰብ ተሰርቷል፡፡

### 1.7.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

በዚህ ጥናት ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ስነ ቃሉ በሚከወንባቸው ባህላዊና ማህበራዊ አውዶች፣ በክዋኔ ላይ የተሳተፉት ከዋኞችና ታዳሚዎች፣ ለክዋኔው መንስኤ የሆኑት የክዋኔው ምክንያትና አጋጣሚዎች ናቸው፡፡ ቀዳማይ መረጃዎቹም ወደ መስክ በመውጣት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች በሰርግ፣ ክብረ ባዓላት፣ በክርስትና እና በተለያዩ የስራ ክዋኔ ወቅት በአውዱ የሚገኙትን ከዋኝና ታዳሚዎች፣ በመመልከትና በመጠየቅ፣ የሴቶች ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞችን የተመለከቱ መረጃዎች በተፈጥሯዊ መቼት ተሰብስበዋል፡፡ የሴቶች ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞች የሚያሳዩ ክዋኔዎችን ማግኘት ያልተቻለውንና የሴቶችን ማህበራዊ ህይወትና የዕለት ተዕለት ውሎ የተመለከተውን

መረጃ ከክዋኔ ውጭ አርቲፊሻል መቼትን እንደሁኔታው በመጠቀም በቃለ መጠይቅ ሰብስቤያለሁ፡፡

ርዕሰ ጉዳዩን የተመለከቱ ንድፈ ሃሳቦችና ፅንሰ ሃሳቦችን ከተለያዩ መፃህፍት፣ መጣጥፎች፣ ከቤተ መፃህፍትና ኢንተርኔት እንዲሁም ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች በካልዓይ የመረጃ ምንጭነት ተጠቅሜያለሁ፡፡ ይህ ጥናት የተነሳበት አላማ ግብ ይመታ ዘንድ ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ማለትም ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይት በተግባር ላይ ውለዋል፡፡

### 1.7.2.1.ምልከታ

ምልከታ ለዚህ ጥናት ለመረጃ መሰብሰቤነት ተግባር ላይ የዋለ ስልት ነው፡፡ Sapsford, and juup (2006, 57) ሲገልፁ፦ ምልከታ አንድን ሁኔታ በትክክል መታዘብ ነው፡፡ ነገር ግን መረጃውን በአይናችን አይተን እንድ ደግፈው፣ እንድንቀበለው እንድን ሰማው መሆን አለበት፡፡ ምልከታ ምንጊዜም የምንጠቀመው መረጃ ወይም እውቀት ለማግኘት መሆን አለበት፤ በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከዚህም አንፃር ምልከታ በአካል ተገኝተን መረጀው ምን እና ምን ማለት እንደሆነ፣ የትና መቼ የሚሉትን ጥያቄዎች የምንመልስበትና የምንታዘብበት በአይናችን አይተን በጆሮ ሰምተን የምናረጋግጥበት ስልት ነው፡፡ ምልከታ ቀጥተኛ ኢ ቀጥተኛ ተሳትፏዊ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ እነዚህም የምልከታ ዘዴዎች ተሳትፏዊና ኢ ተሳትፏዊ ዘዴዎች ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል፡፡ ቀጥተኛ ተሳትፏዊ የምልከታ ዘዴ በአውዱ በመገኘት ክዋኔውን ለመገንዘብ ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም ማስታወሻ ለመያዝና ለመቅረፅ አያስችልም፡፡ በሌላ በኩል ኢ ቀጥተኛ የምልከታ ዘዴ በክዎና ጊዜ ከዳር በመሆን በተሳታፊዎች ላይ መነቃቃትን ለመፍጠር፣ ማስታወሻ ለመያዝ፣ በመቅረጸድምጽ ለመቅዳትና ፎቶ ለመያዝ ያስችላል፡፡

በመሆኑም የሴቶች ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞች በተለያዩ ወቅቶችና ማህበራዊ አውዶች የሚፈጠሩ ሲሆን ግጥሞቹ የሚከወኑበትን ማህበረ ባህላዊ አውድ ኢ ቀጥተኛ ተሳትፏዊ ዘዴን ከመስክ ሰዎቹ ጋር በደንብ እስከምለማመድ ሳካሂድ እቆይና ከዚያ መረጃዎችን በማስታዎሻ ደብተርና በመቅረፀ ድምፅ

ለመያዝ ፅሞናዊ ዘዴን እያፈራረኩ ተጠቅሜያለሁ፡፡ የደብረታቦርን ከተማ በደብ የማውቀው አካባቢ በመሆኑ ባህሉን፣ ቋንቋውን፣ የአኗኗር ስርዓቱንና የስራ ክዋኔውንም በመሳተፍ ስላሳለፍኩት ወደ ማህበረሰቡ ዘልቆ በመግባት ግልፅና ትክክለኛውን ፎክሎራዊ ገፅታ ለማግኘት ስለሚያስችለኝ ተሳትፏዊ ወይም ቀጥተኛ የምልከታ ዘዴን ተጠቅሜያለሁ፡፡ በተጨማሪም ኢ ቀጥኛ ተሳፏዊ የምልከታ ዘዴን የክዋኔውን ሂደት በደንብ በመታዘብና ለመሳተፍ አመችነት ያላቸውን ጥቃቅን ጉዳዮች ዳር ሆኖ በመመልከት በማስታወሻ ለመያዝ፣ በመቅረጸድምጽ ለመቅዳትና ተሳታፊዎችን ለማበረታታት እንደ አስፈላጊነቱ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

### 1.7.2.2. ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ በዚህ ጥናት ከምልከታ በተጨማሪ በመረጃ መሰብሰቤነት ተግባር ላይ ውሏል፡፡ በመሆኑም ለቃለ መጠይቅ ከተዘጋጁት ጥያቄዎች በተጨማሪ በምልከታ ወቅት የሚፈጠሩትን ጥያቄዎች ለመመለስና ክፍተቶቹን ለመሙላት ስለሚያስችለኝ ቃለ መጠይቅን ተጠቅሜያለሁ፡፡ mack, et al. (2005, 29) ሲገልጹ ፦

> ቃለ መጠይቅ ምንጊዜም አንድ ጠያቂ እና አንድ መልስ ሰጭ ፊት ለፊት በመገናኘት በጥልቀት የሚሳተፉበት እና መረጃ የሚገኝበት ስልት ነው፡፡ አጥኚው ከግለሰብም ሆነ ከህዝቦች ጋር ባለው ግንኙነት፣ የህይወት ተሞክሮ ልክ እና መጠን በመገናኘት መረጃ የሚሰበሰብበት ስልት ነው፡፡ እንዲሁም የአጥኚው ሙያዊ ችሎታ እና የአጠቃቀም ዘዴ የቃለ መጠይቁ ጥልቀት የሚወሰን፤ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ከዚህም መገንዘብ እንደ ሚቻለው ቃለ መጠይቅ ድርጊቶችን በአካል ሲከወኑ ማየት ባይቻልም ምስል ከሳች በሆነ ገለፃ መረጃ የሚገኝበት ስልት እንደ ሆነ መታዘብ ይቻላል፡፡ በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት በመስክ ስራ ላይ በምርምሩ፣ በአጥኚው ፍላጎት የተመሰረቱ እና በድንገት የሚገኙ መረጃዎች እንዳሉ የሚገልጽና እነዚህን መነሻ ሃሳቦች በመያዝ መረጃ መሰብሰብ እንደሚቻል ያስረዳል፡፡ Goldstien (1964, 113) ሲገልፅ÷ የተለያዩ ጥያቄዎችን ለተመሳሳይ መረጃ አቀባዮች እንዲሁም፣ ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ለተለያዩ መረጃ አቀባዮች መጠየቅ፣ የቀደምት

ቃለ መጠይቆችን መረጃ ወጥነት አለመኖር ለመመርመር፣ የመረጃ አቀባዮችን ውስብስብ ሁኔታና ስሜት ግልፅ ለማድረግ፣ የተለያዩ ጉዳዮችን ለማዳበር የሚያስችል መሆኑን፤ ገልፆል፡፡

ይህም ማለት ቃለ መጠይቅ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ወይም የተሻለ ግንዛቤ አላቸው ተብለው ከተመረጡ መረጃ አቀባዮች ጋር በመገናኘት መረጃ የሚሰበሰብበት ስልት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ቃለ መጠይቅ የመረጃ ሰጭዎችን እውቀት፣ እምነት፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ደርጊት፣ ገለፃና ምክንያት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ያስችላል፡፡ በዚህ ዘዴ በክዋኔ ወቅት ከሚገኙት ከዋኞችና ታዳሚዎች፣ የፆታ፣ የእድሜና የሙያ ስብጥር በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ስብጥር የተጠቀምኩት የተለያዬ እውቀት፣ ክህሎት፣ ችሎታና አመለካከት ካላቸው መረጃ ሰጭዎች ጥልቅ መረጃ ለማግኘት ያስችለኛል ብዬ በማሰብ ነው፡፡ለመረጃ ሰጭዎች የቀረበው የቃለ መጠይቅ ጥያቄ ክፍትና ዝግ ጥያቄ ሲሆን፣ ክፍት ጥያቄ ለጠያቂውም ሆነ መረጃ ሰጭው ነፃነት የሚሰጥ በመሆኑ ከዚያው ላይ ጥያቄ በመፍጠር አስፈላጊውን በቂ መረጃ ለማግኘት አስችሎኛል፡፡ ዝግ ጥያቄ አጭርና ማብራሪያ የማያስፈልጋቸውን መረጃዎች ለመሰብሰብ ተጠቅሜበታለሁ፡፡ ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በምልከታ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ክፍተ ለመሙላት፣ ለማዳበርና ትክክለኛነት፤ ለማረጋገጥ እንደ አስፈላጊነታቸው በማስታወሻ ደብተርና በመቅረፀ ድምፅ ምስል ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህን መሳሪያዎች መጠቀም አጠቃላይ የክዋኔውን እንቅስቃሴ ለመቅረፅ እና መረጃዎችን ለመሰብሰብ አስችሎኛል፡፡

### 1.7.2.3. ተተኳሪ የቡድን ውይይት

ተተኳሪ የቡድን ውይይት በዚህ ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ከዋሉት መካከል አንዱ ነው፡፡ ተተኳሪ የቡድን ውይይት በአንድ ርዕሰ ጉዳይ የተለያዩ ሰዎችን በመጠየቅ እና እንዲወያዩ በማድረግ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው፡፡ ያለው (2004-197) ሲገልፅ፦ «ተተኳሪ የቡድን ውይይት የሚካሄደው በችግሩ ዙሪያ በቂ መረጃ ሊኖራቸው ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡትን በመውሰድ በሚነሳው ጥያቄ ዙሪያ

በቡድን በመሆን እየተወያዩ መረጃ የሚሰጡበት ሲሆን ከ5 እስከ 12 ሊደርሱ ይችላሉ። ይህም የቡድን ቃለመጠይቅ ማለት ይቻላል»።

ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ተተኳሪ የቡድን ውይይት በአንድም ሆነ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አስተሳሰብ፣ እውቀት እና ችሎታ ካላቸው የመረጃ አቀባዮች ጋር መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ስልት ነው። የመረጃ አቀባዮች የሚሰማቸውን ሁሉ የሚገልጹበት የተሻለ ወይም የተጠናከረ መረጃ በአንድ ጊዜ ማግኘት የሚያስችል መሆኑን መረዳት ይቻላል። በተተኳሪ ማህበረሰብ ለሴትነት ሚና ማደላደያ የሚዜሙ ቃል ግጥሞች ክዋኔ ላይ የቡደኖች አደረጃጀት፣ ስለሚያስተላልፉት የማህበራዊ መዋቅሮች፣ ስለሚሰጧቸው ስነ ልቦናዊ ፋይዳ፣ ተስተላልፎ እና አተገባበር በተመለከተ መረጃ መሰብሰብ ተችሏል። mack, et al (2005, 51) ደግሞ ሲገልጹ፦

> ተተኮሪ የቡድን ውይይት ውጤታማ የሆነ አይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ማህበራዊ ደንቦች ለማጥናት አጥኚው ቡድኖችን በቁጥር በመወሰን ስለ ራሳቸው እና አካባቢያዊ ሁኔታዎች በመጠየቅ የሚሰበስብበት ነው።ቡድኖች ስላለቸው አስተሳሰብ፣ ስለ ሚኖራቸው ማህበራዊ እና የጋራ ሁነቶች የሚመረምርበት ወይም መረጃ የሚሰበስብበት ስልት ነው። እንዲሁም አንድ ወይም ሁለት አጥኘዎች ብዙ ተሳታፊዎችን በጋራ በማድረግ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ውይይት ሚያደርጉበትና መረጃ የሚሰበስቡበት ዘዴ ነው።

ከዚህም ለመረዳት እንደተቻለው በጥናቱ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ቡድኖች እኔ ይሆኑኛል ብየ የመረጥኳቸው ከተለያየ ቦታና ሁኔታ የተገኙ መረጃ አቀባዮችን በማወያየት መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ስልት ነው። ተተኳሪ ማህበረሰብ በተለያዩ ማህበረ ባህላዊ ገጠመኞችና አውዶች በሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች የሚታዩትን ቡድናዊ ገፅታዎችን፣ የርዕስ በርዕስ ግንኙነት፣ ማህበረሰቡ ለሴቶች የሚሰጠውን ማህበራዊ ደረጃ መረጃ አቀባዮችን በቡድን በማዋቀር መረጃ መሰብሰብ ተችሏል። በተተኳሪ ቡድን ውይይት የሴቶች፣ የወንዶችና የስብጥር ብሎ በመክፈል ከሴቶች ሚና ማደላደያ የሚሆኑ ቃል ግጥሞችን ሚና እና ፋይዳ በሚያሳዩ ጥያቄዎች መረጃ ተሰብስቧል። በቡድን ከ5 እስከ 10 የሚደርሱ አባላትን በመደልደልና በማዋቀር

አስፋው ግራር ቀበሌ ሶስት ቀን፣ ፀጉር ሚካኤል ሁለት ቀን እና ህሩይ ቀበሌ ሁለት ቀን በአጠቃላይ ለ ሰባት ጊዜ የቡድን ተኮር ውይይት በማድረግ ማጥናት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ዘዴ ሴቶች በህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና የሚያስረዱ ቃል ግጥሞችን ፋይዳ፣ ተስተላልፎ በጋራ በማውያየት፣ መረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን ማጥናት ተችላል፡፡

### 1.7.3. የመረጃ መተንተኛ እና መተርጎሚያ ዘዴ

በዚህ ጥናት ጥሬ መረጃዎችን ከላይ በቀረቡት የመረጃ ስልቶች መሰረት ከተመደቡ በኋላ ከቤተ መፃህፍትና ከመረጃ መረብ ከተገኙ ንድፈ ሃሳብና ፅንሰ ሃሳቦች ጋር እያገናዘበ ተንትኖ ጥናቱን ውጤት ላይ ለማድረስ ጥረት ተደርጓል፡፡ የጥናቱ ዘዴ ዓይነታዊ የምርምር መተንተኛ ላይ በማተኮር ገላጭ የምርምር መተንተኛ ስልትን በመጠቀም መረጃዎችን በዓይነታቸው እና በቅድምተከተል ተተንትኗል፡፡ በመስክ ምልከታ የተገኘውን መረጃና ክዋኔዎችን በጥንቃቄ በመመልከት፤ ለሴትነት ማደላደያነት የሚዜሙ ቃል ግጥሞችን ከማህበረሰቡ ማህበራዊ አደረጃጀትና የስራ ክፍፍል አንፃር ሲከዎኑ በመሳተፍ በመመርመር ከንድፍ ሃሳቦች ጋር በማገናዘብ ተንትኗል፡፡ በቃለ መጠይቅ የተገኘውን መረጃም በጥንቃቄ በመጻፍና ከመረጃ ምንጮች በተደጋጋሚ በማረጋገጥ፣ በመከለስ በምልከታ ለተገኙ መረጃዎች ማጠናከሪያነት በሚገባው ቦታ በማስገባት ተንትኗል፡፡ እንዲሁም በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተገኙትን መረጃዎች እንደ ቃል ግጥሞቹ ሚና እና ተግባር ሴት እናት፣ ሚስት፣ እህት፣ አይት፣ አያት፣ጓደኛ እና አክስት ስተሆን የሚኖራትን ሚና ቅደም ተከተል በሆነ መልኩ ለቡድኑ በተጠየቁ ጥያቄዎች መሰረት ወደ ጽሑፍ በመገልበጥ ለእያንዳንዱ የቃል ግጥም ክዎና እና ከሚተላለፉት መልክቶች አንፃር ማብራሪያ በማድረግ እና ፋይዳውን በመጠቆም መረጃው ተተንትኗል፡፡ በተጨማሪም የተሰበሰቡትን መረጃዎች ከእንስታዊ እና ከተግባራዊና ንድፍ ሃሳቦች አንፃር በመመልከት መተንተን ተችሏል፡፡

### 1.7.4. የመስክ ቆይታ

ይህ ጥናት በደቡብ ጎንደር በደብረታቦር ከተማ ወስጥ በሚገኙ ስድስት የከተማና አራት የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ በሶስቱ ቀበሌወች በጸጉር ምካኤል ፣በአስፋው ግራር እና በህሩይ ለሴትነት ሚና ማደላደያ የሚዜሙ ቃል ግጥሞች ትንተና የቀረበና አይነታዊ የምርምር ስልትን የተከተለ ስራ ነው፡፡ ጥናቴን ከግብ ለማድረስ ከነሀሴ 30/12/13 ዓ/ም ጀምሮ የቅድመ ዳሰሳ ጥናት በማድረግና ርዕስ በመምረጥ፣ እንዲሁም በአካባቢው የተሰሩ ስራዎችን በማፈላለግ ሳከናውን ቆይቻለሁ፡፡ በመቀጠልም የጥናት ርዕሱ ከፀደቀበት ጊዜ ጅምሮ የድርጊት መርሃ ግብር በማውጣት የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ማድረግ ተችሏል፡፡

ከታህሳስ 20/12/14 ዓ/ም ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የድጋፍ ወይም የትብብር ደብዳቤ በመያዝ ወደ ከተማው አስተዳደር በመሄድ ለሚመለከታቸው ለባህል ቱሪዝም ፅ/ቤት፣ ለወረዳውና ለተመረጡት ቀበሌዎች ጉድኝት መሪዎች እና ለሌሎች የአስተዳደር አካላት በማሳየት አንፃራዊ ግንኙነት መፍጠር ተችሏል፡፡

በተቀረፀው የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት ከአማካሪ ጋር በመነጋገር በዙሪያው ያሉ ስራዎችን ማንበብና የንድፍ ወይም ትልመ ጥናት ስራ በመስራት ማስገምገም ተችሏል፡፡ የእርማት ስራው እንዳለቀ ትልመ ጥናቱን በሚመጥን መልኩ በሁለት ኮፒ በማቅረብ በፈታኞች የተሰጠኝ ግብረ መልስና ጥቆማ በመያዝ ወደ መስክ ተመልሻለሁ፡፡

የደብረታቦር ከተማ የማውቀው ቢሆንም ለጥናቱ የእንግዳነት ስሜት ተሰምቶኛል፡፡ ቢሆንም በዙሪያው ስላሉ አስተሳሰቦች ሴት እናት፣ እህትና ሚስት ስትሆን ያላት ሚና ምን ያህል ነው? ማህበረሰቡ ለሴቶች ምን ያህል ግምት ይሰጣል? በቃል ሚዜሙ ቃላዊ ጥበቦች ክዋኔዎች ትርጓሜ ለሴትነት ሚና ማደላደል አስተዋፆኦ አላቸው? የሚሉትን በማንሳት ለማስገንዘብ ጥረት አድርጌያለው፡፡ በመቀጠልም ለጥናት በመረጥኳቸው ቀበሌዎች የማህበረሰቡን ወግና ልማድ በመጠበቅ ስለ ጉዳዩ አስገንዝቤለሁ፡፡ በተጨማሪም ቤተሰባዊነት ጉዳዮችን በማስቀደም ቀለል ባለ መንገድ እንዲቀርቡኝና እንዲነግሩኝ በማህበራዊ ህይወት በመጠጋት ችግሮችን ማቅለል ተችሏል፡፡ ለምሳሌ÷ አውደ ምህረት በመሄድ፣ ሴቶች ሚገኙበት አውድ መገኘት፣

አራስ ሴቶችን በመጠየቅ፣ ልቅሶ በመድረስ ከድሮ በተሻለ መልኩ በመቅረብ እና በመፈፀም ሁነቶችን ማቃለል ችያለው።

ትኩረት በአደረኩባቸው ቀበሌዎች አካባቢ የመንግስት የስራ ሃላፊዎችን ማለትም ከቀበሌ አስተዳደሮች፣ ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎችና ታወቂ የሀገር ሽማግሌዎች በቤተሰቦቼ አማካኝነትና መስክ ስነ ምግባር (filed work and discipline) ትምህርት በአገኘሁት እውቀት መሰረት መግባባት ላይ በመድረስ ጥናታዊ ስራው ጊዜ እንደሚያስፈልገው በማስረዳት ስራዬን ጀምሪያለው። ሰዎችን ቀጠሮ በማስያዝና በተባልኩት ቀን በመሄድ ማጥናት ችያለው። የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞች መተንተን እንደመሆኑ መጠን ሴቶች ከሚሰበሰቡባቸው ቦታዎች በመገኘት፣ ሴቶችን በይበልጥ በመቅረብና በቁሳቁስ በመደገፍ መግባባት ችያለው። ባህሉ በሚፈቅደው መልኩ በማክበር ከአነጋገር፣ ከአለባበስም ጥንቃቄ በማድረግ የመስክ ቆይታ ማድረግ ችያለው።

ከመስክ ቆይታ በኂላ ከግንቦት 30/09/14 ዓ/ም ጀምሮ የተሰበሰቡትንና የተገኙትን መረጃዎችን ማደራጀት፣ መመደብ፣ ማረም ችያለው። ነገር ግን በፍጥነት የተቀረፁ፣ ያልተለዩ፣ ትርጉም የሌላቸው መረጃዎች አግኝቻለው። በዚህም እንዳስፈላጊነቱ በስልክም፣ በአካልም በመሄድ እንዲሁም በመደጋገም ማስተካከል ችያለው። በመቀጠልም በመስክ የተገኙን መረጃዎች ማህበረሰቡን በሚያሳይ መልኩና ምርምራዊ ስነ ዘዴን ግምትውስጥ በማስገባት አንፃራዊ በሆነ መንገድ መተንተን እና ለአማካሪ ማሳየት ችያለው። የተሰጠኝን ግብረ መልስ በመውሰድ እና ክፍተቱን ለማስተካከል ጥረት አድርጌለው።

### 1.7.4.1. በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

በጥናት ሂደትም አስተማማኝ የመረጃ ምንጭ ለማግኘትና ታማኝ መረጃ ለማምጣት ሲባል በአንድ ማህበረሰብ ስርዓትና ደንብ መሰረት መንቀሳቀስ ግዴታ ይሆናል። በዚህም ይህን ጥናት በተገቢው መንገድ ለማከናወንና ውጤታማ ለመሆን ሲባል በመስክ ቆይታዬም ሆነ በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች አሉ። እነሱም፦ በሰዎች ዘንድ ጉዳዩን ቀለል አድርጎ ማየት፣ ከተመረጡት መረጃ አቀባዮች ጋር በፈለኩት ስዓትና ወቅት አለማግኘትና ቃል ግጥሞች የሚከዎኑባቸው አውዶች መነሻ

ምክንያታቸው ገጠመኝን ስለሚፈልግ እኔ እንደፈለኩ ማግኘት አለመቻሌ፣ የሚጠቀሱ ውስንነቶች ናቸው። እንዲሁም መረጃ አቀባዮቼ ሆኑ ሌሎች ስለጉዳዩ ግንዛቤ ይኖራቸዋል በሚል የጠየኳቸው ሰዎች ነገሩን መናቅ፣ አንች ታውቂዋለሽ ብለው መመለስ፣ እኛ ይህ የወያኔ ወግ አይመቸኝም በማለት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ ክስተቶች ነበሩ።

### 1.7.4.2. የተወሰዱ መፍትሄዎች

በዚህ የመስክ ስራ ላይ ለተከሰቱ ችግሮች ዘላቂ የሆነ ጊዜያዊ መፍትሄዎችን አስቀምጫለሁ። በዚህም ትኩረት ባደረኩባቸው አካባቢዎች በፆታ ደረጃ፣ ለቡድን ሃላፊዎች፣ ለማውቃቸውን ግለሰቦች፣ ወጣቶች እና የትምህርት ደረጃ ያላቸውን ይበልጥ በመግባባትና ሁኔታውን በሚገባ በማሳመን ችግሩን በተወሰነ መልኩ ማቃለል ችያለው።

በተጨማሪም የሰዎችን መገኛ ወይም አመቺና በዓል ቀናትን በመመስረት በልቅሶ ቤቶች፣ በቤተክርሲቲያን፣ በአደባባዮች፣ የሴቶችን ሃይማኖታዊ ሆነ ባህላዊ የከበራ ቦታዎች፣ አራስ ቤቶችና ወፍጮ ቤት በመሄድ ጥሩ ግንኙነቶችን በመፍጠር፣ በአቅም ሻይ ቡና በማለት፣ ስኳርና ቡና በመስጠት ችግሮችን መቀነስ ተችሏል። የወያኔ ወግ አንሰማም የሚሉኝን ደግሞ እኔ የማጠናው ጥናት ከእነሱ ጋር ምንም አይነተ ግንኙነት እንደሌለው በደንብ በማስረዳት ጥነቴን ማከናወን ችያለው። በአጠቃላይ የማውቃቸውን ሰዎች ሁኔታውን እንዲረዱኝ በማድረግ እና ዝምድናን በመቁጠር፣ በመቀራረብ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን በማከናወን መፍትሄ መሆን ችለዋል።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ክፍል የንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ፣ የፅንሰ ሃሳባዊ እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.1. ንድፋ ሃሳባዊ ማዕቀፍ

በዚህ የንድፍ ሃሳባዊ ማዕቀፍ ርዕስ ለጥናቱ አመቺነት ያላቸው ንድፍ ሃሳቦች ተመርጠዋል፡፡ እነርሱም ከጥናቱ ርዕስ ጋር የቀረበ ግንኙነት ያላቸው እንስታዊነት ንድፍሃሳብ እና ተግባራዊ ንድፍ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ንድፍ ሃሳቦች በዚህ ጥናት ውስጥ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመፈረጅ፣ ለመመዘን እና ለመተንተን አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ Goldestien(1964) ስለ ተሰበሰቡ መረጃዎች ሲያስረዳ፦ በፎክሎር ጥናት በመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በተገቢው መንገድ ማደራጀት እና መተርጎም እንደሚገባ፤ ይገልፃል፡፡ ይህም ትርጓሜ ከዘዴዎቹ ጋር ተስማሚ ከሆኑ ንድፍ ሃሳቦች አንጻር መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡

### 2.1.1. እንስታዊነት ንድፍ ሃሳብ

Nicole (1999 25, 27) ሲገልፅ÷ እንስታዊ ንድፍ ሃሳብ ከፎክሎር ጥናት ጋር እጀግ ቁርኝት ያለውና የቡድኖችን የዕለት ተዕለት የኑሮ ሁኔታንና የፆታዊ እንቅስቃሴና አሳሳል፣ አሰያየምን፣ መብት አሰጣጥንና ማህበራዊ ደረጃን፣ ሚናን ሁሉ የሚመለከት ነው፤ ይላል፡፡ ይህም ማለት የአንድን ማህበረሰብ የኑሮ መስተጋብርና ማንነት ሁነቶን የሚቃኝ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ነው፡፡ ተተኳሪ ማህበረሰብ ሴት ልጅ ስለሚሰጣትና ስለምትሳፍባቸው ማህበራዊ ክልሎች፣ ውጤቶችና ሚናዎች በቃል ግጥሞች ስለመገለጣቸው የሚያሳይ ንድፍ ሀሳብ ነው፡፡ በተጨማሪም Hirdmann (1996, 8-9) ሲገልፅ ÷ እንስታዊነት ንድፍ ሃሳብ ሴቶችን በማህበረሰቡ ውስጥ ስለሚኖራቸው ልዩ ልዩ የህይወት ምልክቶች በትክክል ብቻ ሊገልፅና ሊያደራጅ የሚችል ሃሳብ ነው፡፡ ሴቶች በቡድኑ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎና ደህንነት ከሌሎች ሁነቶችና ነቀፌታዎች በተለያዩ ህዝባዊ ስልቶች የሚያደላድል ነው፡፡ በተጨማሪም በቃላዊ

ጥበቦችና ፁሁፋዊ ስልቶች የሴቶችን ሚና እና የእንስታዊነት ማህበራዊ ግንባታ የሚመለከት ንድፍ ሃሳብ ነው፤ ሲል ያስረዳል። ከዚህ ጋር በማያያዝ

Milaን (2020,) ጨምሮ ሲገልፅ÷ እንስታዊ ንድፍ ሃሳብ ሴት ከወንድ ጋር በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ስነ ፅሁፍ ጉዳዮች እኩል ድርሻ አላት በማለት እና በሁሉም ዘርፍ ነፃ ሁና መስራትም ማሰብም፣ ትችላለች የሚል ብሂል የያዘ ነው። በተለይ በስነ ፅሁፉ ዘርፍ ለሴትነት ሚና ሚሰጣት ትኩረት አናሳ ቢሆንም ለሁሉም የደህንነት መክፈቻ ሴት እንደሆነች፤ ያስረዳል። በተተኳሪ ማህበረሰብ ሴት ልጅ በተለያዩ ማህበራዊ ቅርፆች፣ ስያሜዎችና ደረጃዎች ላይ የምትተገብራቸውን ተግባሮችን ማስረዳት የሚችሉ ቃላዊ ቅኝቶችንና ስልቶችን በመጠቀም በቡድኖች የዕለት ተዕለት ሁነቶች እንዲለመዱና ተሻሽለው እንዲቀጥሉ ያደደርጋሉ።

በተጨማሪ Nicole (1999, 27) ፎክሎሪስቶች ስለ እንስታዊነት እና የሴቶችን ልምድ፣ ተሞክሮ፣ መገለጫዎች በተለያዩ ባህላዊ አውዶቻቸው ውስጥ መርምረዋል። በተለይ ቀደም ሲል የፎክሎር አጥኝዎች በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ የበታችነት፣ የወንዶች የበላይነት ወይም ግለኝነት፣ ደካማ፣ ፀብ ጫሪነት እንደሆኑ እና ሚናቸው ተደብቆ መቆየቱን፤ ያስረዳል።

ይህም ማለት ለሴቶች ፆታዊ ሚዎች የሚሰጡትን ትርጓሜዎችን፣ ስስ አመለካከቶችን በተለያዩ የቡድን የፈጠራ ስራዎች ማለትም ስነቃላዊ በሆኑ ቃል ግጥሞች፣ ተረቶችና አፈታሪኮች እንዲሁም ፁሁፋዊ ስነ ፁሁፎች በመግለፅ ነቀፌታዎችን እንዲቋረጡና እንዲቀሩ የሚያስረዳ ሲሆን በተተኳሪ ማህበረሰብ ቃል ግጥሞችን በመጠቀም በሚኖሩበት ማህበራዊ መስተጋብሮችና ሌሎች ገጠመኞች ላይ የሚቀነቀኑ ህዝባዊ ፈጠራዎች የሴቶችን የቆዩ ስያሜዎችና ውክልናዎች ለማስቀረት ሚና እንዳላቸው ማወቅ ያስችላል።

### 2.1.2. ተግባራዊ ንድፍ ሃሳብ

ይህ ንድፍ ሃሳብ የሰው ልጆች አካባቢያዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲሉ ብዙ ችግሮችን ሲፈቱ እና ተግባሮችን ሲያከናውኑ የሚታዩ ሂደቶችን ሁሉ የሚመለከት

ነው:: ተግባራዊ ንድፍ ሃሳብ ፎክሎሩ የሚኖረውን ፋይዳ እና ቀጣይነት ያለውን የማህበረሰብ ሁኔታ የሚመለከት ነው:: Malinowski (1939, 939) ሲያስረዳ ፦

> የሰው ልጅ ስነ ህይወታዊ ባህርይው ቁልፍ ጉደይ ሆኖ አካባቢያዊ ፍላጎቱን ለማሟላት ሲል አካባቢያዊ ተፅዕኖ ሁሉ ጎን በመቆም ምላሽ ይሰጣል:: ግላዊ ስሜቶች እንዳሉ ሁነው ከማህበረሰቡ ጋር ሳይጣላ እንዴት መቀጠል እንዳለበት የሚመለከት ነው:: እንዲሁም ሰው ሲወለድ ይዞት የተፈጠረ ምኞትና ፍላጎት አለው:: ለዚህም በባህሉ ውስጥ ያለውን ስልትና ስርዓት ተጠቅሞ ጤናውን፣ አካላዊ እና ህሊናዊ ባህርይውን እንዲሳካለት እና እንዲስተካከል ያደርጋል:: ካለ ሆነ ይታወካል፣ ይረበሻል፣ ስነ ልቦናዊ ጉዳት ይደርስበታል:: ሁሉንም ነገር በምቹ ሁኔታ ለማስቀጠል ይፈልጋል፤ በማለት ይገልፃል::

ከዚህ ጥቅስ መረዳት እንደሚቻለው ተግባራዊ ንድፍ ሃሳብ ከፎክሎር ጥናት ጋር ትልቅ ትስስር ያለው ነው:: ማህበረሰቡ ለመኖር ሲሉ ምኞት፣ ፍላጎታቸውን ሁሉ አስተካክለው ለመቀጠልና የተሻለ ደስታ ለማግኘትና ሴቶች ከወንዶች ተመጣጥነው ለመኖር ወይም ሚናቸውን ለይቶ ለማስቀጠል የሚያደርጉትን ሂደት የሚመለከት ነው:: ከዚህ ጥናት ጋር ሲታይ ተተኳሪ ማህበረሰብ ሃዘናቸውን ለመወጣት፣ ደስተኛ ሆኖ ለመኖር እና አይረሴ ስሜቶችን ለመፍጠር፣ ማህበራዊ ህይወታቸውን ለማጠናከርና ከፍ ለማድረግ ቃል ግጥሞችን ያዜማሉ፤ ይደረድራሉ:: በተጨማሪም ለመግባባት፣ ማህበራዊ ችግር ለመፍታት፣ ለልማት፣ ለማንነት ማሳያ፣ ለመንፈስ ርካታ የሚጠቅም እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል:: Brown (1935, 394-398) ሲገልፅ ፦

> የተግባራዊ ንድፍ ሃሳብ በማህበረሰብ ውስጥ ያለን ግንኙነት፣ መዋቅራዊ ስርዓትና አንድነታቸው እንደጠበቀ ምቹ የህይወት መንገድ እንዲኖራቸው የሚፈልጉትን ሂደት የሚመለከት ነው:: በተጨማሪም ማህበረሰቡ በሚኖሩበት አካባቢ ሶስት ነገሮችን አስተካክለው መኖርእንደሚፈልጉይመለከታል:: የመጀመሪያው ተፈጥሯዊ የሆኑ ጉዳዮችን ማክበር ሲሆን በሚመቻቸው መልኩ ከእስሳት አፈጣጠር ጋር ያሉት ስርዓት በማስያዝ መመሳሰላቸውንና መለያየታቸውን የሚመለከት ነው:: ሁለተኛው በማህበራዊ ህይወት ያሉ አስተሳሰቦችን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል የሚመለከት ነው:: ሶስተኛው ደግሞ ያሉበትን የማህበራዊ መዋቅር እንዴት ማሳደግ፣ ማሻሻል እና የተሻለ መንገድ ማምጣት እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው፤ በማለት ይገልፃል::

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው ሰዎች ተፈጥሯዊ የሆኑ ጉዳዮችንም ለማስተካከልና ስርዓት ለመቅረፅ እንዲሁም ማህበራዊ ድልድልን ለመፍጠር እና ለማስቀጠል የሚደረገውን ሂደት ይመለከታል። ተተኳሪ ማህበረሰብ የሴትነት ሚና የሚያደላድሉ ቃል ግጥሞችን በመጠቀም በዜማ በመታጀብ በተለያዩ አወዶች ይከውናሉ። እነዚህ ክዋኔዎች ሴቶች የሚሰጣቸውን ማህበራዊ ትረጓሜዎችን ለማስቀረት፣ መግባባቶችን ለማምጣት ፋይዳ እንዳላቸው ከንድፍ ሃሳቡ አንፃር መረዳት ይቻላል።

## 2.2. ፅንስ ሃሳባዊ ማዕቀፍ

በዚህ ክፍል ደግሞ ለሴትነት ሚና መደላደያ የሚውሉ ቃል ግጥሞች መመርመር ላይ የተዳሰሱ ፅንስ ሃሳባዊ ማዕቀፎች ይቀርባሉ። የስነ ቃል ምንነት፣ የቃል ግጥም ምንነት፣ ባህርይና ፋይዳ፣ የእንስታዊነት (ሴትነት) ፅንሰ ሀሳብ (Feminism)፣ ማህበራዊ ሚና የመሳሰሉት የጥንቱ ፅንስ ሃሳብ ሁነው ቀርበዋል። የፎክሎር ዘውጎች በተመለከተ Dorson(1972) የፎክሎር ዘውጎችን በአራት ይከፈላሉ። እነሱም፦ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ቁስ ባህል፣ ስነ ቃልና ትውን ጥበባት ናቸው፤በማለት ይከፍላቸዋል። ይህ ጥናት ከተከፈሉት አራት ዘውጎች መካከል በስነ ቃል ላይ ያተኮረ ነው። ስነ ቃል በቃላት አማካኝነት የሚገለፁ፣ የሚነገሩ፣ የሚዜሙና የሚተረቱ ሁነቶችን በስሩ የያዘ ሲሆን በፈርጅ ከተቀመጡት ቃላዊ ጥበቦች መካከል በዝረው ቃል ትረካ የሚቀርቡ፣ በአጫጭር ቅርፅና በግጥም የሚከወኑትን አካቶ የያዘ ነው።

## 2.2.1. የስነ ቃል ምንነት

ስነ ቃል የአንድ ማህበረሰብ የጋራ ሃብት ነው። በቃል ተፈጥረው በቃል የሚከወኑ የህዝብ እውቀቶችን የያዘ ዘውግ ሲሆን ለቡድኑ የራሱ ፋይዳ ያለው ነው፡ የስነ ቃልን ሚና አስመልክቶ Brunvand (1979 ፣264) እንዲህ ይላል። ‹‹ስነ-ቃል በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ ምኞትና ፍላጎትን፣ ቅርፅና ውበትን የምንገልጽበት ነው››። ይላል። ይህም ማለት ስነ ቃል ከህብረተሰቡ ተወስዶ መልሶ ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚውል መሆኑን የሚያመለክት ነው። እንዲሁም ፎክሎር በህብረተሰቡ መሰተጋብር ውስጥ የሚፈጠር እና ጥበባዊ በሆነ መልኩ የህብረተሰቡን ባህል መልሶ የሚያንጸባርቅ መሆኑን መረዳት ያስችላል። በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ልጅ ምኞቱንና ፍላጎቱን የሚገልፅበት የፎክሎር ዘርፍ በሆነው በስነ-ቃል አማካይነት የሚነገር፣

የሚዜምና የሚደረስ በመሆኑ ስነ ቃልን ለማጥናት የህብረተሰቡን ባህል፣ የኑሮ ሁኔታ፣ ጤና፣ አስተሳሰብ፣ ችግር፣ ማንነት ወ.ዘ.ተ …ማወቅ እንደሚቻል ያስገነዝበናል፡፡

### 2.2.2. የቃል ግጥም ምንነት

ቃል ግጥም የማህበረሰቡን ባህል መሰረት በማድረግ የተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ በግለሰቡም ሆነ በቡድን የሚቀርብ ጥበብ ነው፡፡ ማህበረሰቡን በዕለት ተዕለት የህይወት እንቅስቃሴ ወቅት የሚያስተውሏቸውን ገጠመኞች፣ ያለውን ፍልስፍና እና ውጴታ ወ.ዘ.ተ ያስተላልፋበታል፡፡ በወቅቱ ወይም አጋጣሚ የተሰማውንም ስሜት ያንፀባርቅበታል፡፡ በቃል ግጥም ስር የሚመደቡ ንዑስ መደቦች በአብዛኛው በቃል ተደርሰው በተለያዩ የአከዋወን ስርዓቶች ታጅበው በቃል ተስተላልፎ በአጭር የግጥም ቅርፅ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፏ ናቸው፡፡ በዚህ ዘርፍ ስር የሚመደቡ ቃል ግጥሞች በርካታ ናቸው፡፡ እነዚህንም የቃል ግጥም አይነቶች ከሚቀርቡት ማህበራዊ አውድ አጋጣሚዎች ጋር በማያያዝ ሚከወኑ ናቸው፡፡ ሰለሞን (2007፣ 129)

> ቃል ግጥሞች በአብዛኛው ማህበራዊ አጋጣሚዎችና ማህበራዊ አውድን መነሻ በማድረግ የሚቀርቡ እንጅ ያለ ምክንያት ወይም በዘፈቀደ በማንኛውም ጊዜ ቦታ የሚከወኑ አይደሉም፡፡ ለምሳሌ ፡- የሙሾ ግጥምን ብንወስድ የሙሾ ግጥም የሚያደርገው ሰው ከዚህ ዓለም በሞት በተለየበት ወቅት ሲሆን ይህ የለቅሶ ማህበራዊ አውድ በሌሉበት ወቅት የሙሾ ግጥም ሊቀርብ አይችልም፡፡ በተመሳሳይ የሠርግ ዘፈን ግጥም በአሸንዳ ወቅት የሚቀርቡ ናቸው፡፡ ስለሆነም በቃ የሚቀርቡ ግጥሞች ከማህበራዊ አውድ ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ በተተኳሪ ማህበረሰብ የሚዜሙ ቃል ግጥሞች ሴቶች በታሪክ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁነቶች ያላቸውን እንቅስቃሴ መሰረት በማድረግ ሲሆን ለመከዎንም ምክንያትና አጋጣሚ የሚሹ ናቸው፡፡ በተጨማሪም Mestin messele (2000) ሲገልፅ÷

ቃል ግጥሞች ከሠው ልጅ ታሪክ ጋር የተቆራኘና ባህላዊ የመረጃና የእውቀት መግለጫ ዘዴ ሆኖ አገልግሏል፡፡ አንዳንዶች ቃል ግጥሞች ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ በቅብብሎሽ የመጡ ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ እንደ ወቅቱና ሁኔታው የሚፈጥሩና ይዘታቸውም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዬችን የሚዘረዝሩ ናቸው፡፡

በዚህ ምክንያት ቃል ግጥሞች አንድን አካባቢ ወይም ማህበረሰብ የጋራ እሴቶች ተደርገው ይቆጠራሉ፤ በማለት ያስረዳል፡፡ ቃል ግጥሞች በተለያዩ አጋጣሚዎች በቀጥታ የሚከዎኑ በመሆናቸው ከዘፈን ጋር የሚመሳሰሉባቸው የጋራ ይዘት አላቸው፡፡ የቃል ግጥሞች በየተማረ ሆነ ባልሰለጠነው ማህበረሰብ ውስጥ ምክንያትና አጋጣሚን ተመርኩዘው አካባቢያቸው ሲከወን ይስተዋላል፡፡ በተተኳሪ ማህበረሰብ ቃል ግጥሞችን ቁጭት፣ ሃዘንን፣ እና ደስታን ለመግለፅ የሚጠቀሙባቸው ሲሆን ከዚህም ባለፈ ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና ለማስረፅ፣ ለመማሪያ፣ እውቀትን እና ልምድን ለማካፈል ያገለግላሉ፡፡ ቃል ግጥሞች በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ሲሆን ዋና ዋና ይዘታቸው ተስፋ፣ ምኞት፣ ፍላጎት፣ግጭቶች፣ ቤተሰባዊ ጉዳይ፣ ስለ ሰው ልጅ መከራና ችግር፣ ፍቅር፣ ሃዘን፣ ስራና ትዳር ወ.ዘ.ተ ናቸው፡፡

በቃል ግጥሞች ጥናት ላይ የተሰማሩ ሙህራን ከግጥም ትንተና ይልቅ ግጥሞችን ለማስባሰብ የሚደረግ ጥረት ጎልቶ ይታያል፡፡ ነገር ግን ሁለቱንም እኩል ክብደት ተሰጥቷቸው ሊከወኑ የሚገቡ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ቃል ግጥሞች ለመረዳት ማብራሪያና ትርጉም መስራት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የብዙ ብሄረሰብ፣ ቋንቋና ባህል ባለቤት ህዝብ የራሳቸው የሆነ ታሪክ፣ ልምድ እና ባህላዊ እሴቶች አሏቸው፡፡ እነዚህ እሴቶች ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃላዊ ስነ ፁሁፍ ሲሸጋገሩ የመጡ ናቸው፡፡

የቃል ስነ ፁሁፍ ጥቅምና አስፈላጊ በአሁኑ ዘመን ጭምር ትልቅ ቦታ የሚሰጠው እና አስፈላጊ ነው፡፡ ሰዎች በዕለት ተዕለት መስተጋብራቸው ውስጥ ሃሳባቸውን የሚገልፁባቸው ድብቅ ስሜታቸውን የሚያስተጋቡበት መሳሪያ ነው፡፡ ቃላዊ ግጥሞች የዚህ አይነት ስነ-ፁሁፍ አንዳኛው ዘውግ ነው፡፡ ቃል ግጥሞች ከአውዳቸው አንፃር ሊገደቡ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ከአውዳቸው ወጭ ግን ለገደብ ያልተጋለጡ በመሆናቸው

የገጣሚውን ቀልብ (ስሜት፣ሀድራ) ሀዘን ተቃውሞ ሊንፀባረቅበት የሚችል አቅም አለው። ስለዚህ ስለ ሴቶች ማደላደያ ሚና ሚዜሙ ቃል ግጥሞች ማሰባሰብ እና መተንተን የማህበረሰቡን እሴቶችና ታሪኮችን ከማወቅ ባሻገር የማህበረሰቡን እይታና የኑሮ፣ ማህበራዊ መዋቅር ሁኔታን ለማወቅ ይረዳል።

## 2.2.3. የቃል ግጥም ባህርያት

ቃል ግጥም የአንድ ማህበረሰብ ስሜት ውጼታና ጥላቻ፣ ሃዘንና ደስታ፣ ተስፋና ምኞት አይረሴ በሆነ ገለፃ የሚያፀባርቁ የህዝብ ሃብት ናቸው። እነዚህ የህዘብ ሃብቶች ደግሞ በጋራ ተፈጥረው በጋራ የሚከወኑ ሲሆኑ የአከዋዎን ስልታቸው እንደ ሚከወንበት አውድ፣ ምክንያትና አጋጣሚ የሚወሰን ይሆናል። ከዚህ በመነሳትም የቃል ግጥሞች የራሳቸው የሆነ መገለጫ ባህርይ አላቸው። አይረሴ፣ ዘያዊ፣ ቁጥብና ፈጠራዊ የሆኑ፣ተከታታይነትና ተደጋጋሚነት እንዲሁም እንደሚከዎንበት አውድ ደግሞ የተለዋዋጭነት ባህርይ እንዳላቸው ይገለፃል። በተተኳሪ ማህበረሰብ የሚዜሙና የሚከዎኑ ቃል ግጥሞች ሴት በማህበረሰቡ ከሚሰጣት ልማድና ደንብ መሰረት የእናትነት፣ እህት፣ ሚስት፣ አይት፣ አያት፣ ምራት፣ አክስት፣ ጓደኛ እና ዋርሳ ከሚባሉ የዘር ሀረግ ድልድልና ክፍፍል አኳያ የተለያየ ቅርፅና ተግባር ይወጣሉ። በዚህም የግጥሞቹ አደራረስና የአከዋወን ስልት ሴትን በተለያዩ ማህበራዊ ደረጃዎች ይገልጣሉ። የመደጋገም፣ የተለዋዋጭነት፣ ባህርይ ይታይባቸዋል።

## 2.2.4. የቃል ግጥም ፋይዳ

ቃል ግጥም በግለሰብ ተደርሰው በቡድን የሚከዎኑ ቃላዊ የፈጠራ ስራ ሲሆኑ ለከዋኙ ማህበረሰቡ እንደሚከውኑት ዓላማ የራሳቸው ፋይዳ አላቸው። finnigan (1977, 3-7) እንዲህ ትገልፃለች÷ቃል ግጥም መረጃን ከትውልድ ወደ ትውልድ ያቀብላል። ባህልን፣ ወግን ጠብቆ ለማቆየት ያገለግላል። ስነ ምግባርን ለማስተማር፣ ከአስቸጋሪ ሁኔታ ለማምለጫነት ጥቅም ላይ ይውላል።ስንፍናን በመንቀፍ፣ የደከመ አእምሮን ለማበረታት ስራን ያለመሰልቸት ለመስራት ያስችላል፤ በማለት ታስረዳለች።

ተተኳሪ ማህበረሰብ በቃል የሚቀኗቸው ግጥሞች ሴት በማህበረሰብ ውስጥ ያላትን ሚና ከእንስታዊነትና ከማህበረሰቡ ተግባር አንፃር ፋይዳ አላቸው፡፡ ቃል ግጥሞች በህዝባዊ ቅኝቶች የተመሰረቱ ዜማና ስሜትን የመንካትና የማዝናናት ሃይል ያላቸው ጥበቦች ናቸው፡፡ ሰሎሞን (2007፣129) ሲገልፅ÷«ቃል ግጥም በሁሉም የማህበረሰብ ክፍል (የሰለጠነውም ሆነ ያልሰለጠነው) ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ፣ በድሮም ሆነ በአሁን ጊዜ የማህበረሰቡን ማንነት በማሳየት ከፍተኛ አስተዋፆኦ የሚያበረክት የጥበብ አይነት ነው»፤ ይላል፡፡ ቃል ግጥም የሁሉም የህብረተሰብ ክፍልና ቡድኖች የአኗኗር፣ የአመጋገብ፣ የሃዘንና የደስታ ወ.ዘ.ተ አጠቃላይ የማንነት ሁነቶችን በሚገኙት ማህበራዊ አጋጣሚዎች ሊያንፀባርቁ የሚችሉ ቃላዊ ጥበቦች እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ ተተኳሪ ማህበረሰብ በተለያዩ ሰርግ፣ የልቅሶ፣ የክርስትና፣ የጥምቀትና የስራ ማህበራዊ አውዶች ላይ ሴት ልጅ በቡድኑ ያላትን ማህበራዊና ተግባራዊ ሚናዎች የማስተላለፍና በቡድኖች መካከል እንዲዳበር ትልቅ አስተዋፆኦ አላቸው፡፡

## 2.2.5. የእንስታዊነት ወይም የሴትነት ምንነት

የእንስታዊነት (ሴትነት) ፅንሰ ሀሳብ (Feminism) እንስታዊነት (ሴትነት) በጽሑፍ ውስጥ ወይም በአንድ ማህብረተሰብ ውስጥ ሴትና የሴት መገለጫ እንዴት እንደተገለፀ የምናይበት መንገድ ነው፡፡ javeed (2017፣3372) ሴትነትን እንዲህ ይገልፃል፡፡

> እንስታዊነት (ሴትነት) ማለት በጾታ እኩልነት ላይ የሴቶች መብት ተሟጋችነት፣ የጾታ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እኩልነት ፅንሰ ሀሳብ ማራመድ፣ ወንዶችና ሴቶች እኩል መብትና ዕድሎች ሊኖሯቸው ይገባል የሚል ፅኑ እምነት ያለውና ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሌሎች የወንዶች መብቶች ሁሉ እኩል ለሴቶችም መብቶች እንዲሆኑ በአስተምህሮው ይደግፋል፤ በማለት ያስረዳሉ፡፡

በእንስታዊነት (ሴትነት) ጽንሰ ሀሳብ ውስጥ የሴቶችን እኩልነት፣ በማህበራዊ እኩል ተጠቃሚነት፣ እኩል መብትና እድል ማግኘትን፣ በተጨማሪም ሴት እናት፣ እህትና

ሚስት ስትሆን ያላትን አስተዋፆኦ ለወንዶች፣ ለቤተሰቦች መመስረት እንዲሁም የሴቶች ተሳትፎ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚሰጠውን አንድምታ ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ውስጥ የሴትነትን ሚና የሚያደላድሉ ቃል ግጥሞች ሴት በማህበረሰቡ ዘንድ እንዴት እንደምትታይበት እና የቃል ግጥሞቹ የክዎና መገለጫ ወይም ተረክ በመመርመር ስለሴት የሚነሳው ሀሳብ ተመርምሮበታል፡፡

## 2.2.6. ማህበራዊ ሚና

ማህበራዊ ሚና የአንድ ቡድን ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ ለመቆየት ይቻለው ዘንድ እያንዳንዱ የቡድኑ አባል የሚወጣቸውን ሚና የሚመለከት ነው፡፡ Perez (2015፣1) ሲገልፅ÷ ማህበራዊ ሚናዎች የጋራ ሃብቶች አጠቃቀምን በተመለከተ በማህበረሰብ ውስጥ የጋራ እርምጃ የመያዝ አቅምን ለመወሰን ወሳኝ ሚና እንደሚጫወቱ ይገልጻሉ፡፡ ማህበራዊ ሚናዎች ከሚናነት ባለፈ የሚያገኙትን የጋራ ጥቅም አለ፤ በማለት ያስረዳል፡፡

በተጨማሪ Sunstein (1996, 928) ሲያስረዳ÷ ማህበራዊ ሚናዎች የማህበራዊ ልማዶች ወይም ደንቦች ውጤት እንደሆኑ እና በተመሳሳይ መልኩ ማህበራዊ ልማዶችና ደንቦች በማህራዊ ሚናዎች እንደሚሰሩ፤ ይገልጻሉ፡፡ ይህም ማለት ማህበራዊ ልማዶች ወይም ደንቦች እና ማህበራዊ ሚናዎች፣ ተከታታይነት ያላቸው እሳቤዎችንና ድርጊቶችን የሚመለከትና ተመሳሳይ ገጽታዎች መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

Masolo (2004, 268-269) Searle (1995) ን በመጥቀስ ሲገልፅ÷‹‹ ማህበራዊ ሚናዎች ተመሳሳይ ገጽታዎች እና ደረጃዎች ያሏቸው ናቸው፡፡ የሚፈጠሩት ደረጃዎችና ህጎች የጋራ ተቀባይነት ያላቸው፤ እንዲሁም በጋራ ሊቀበሏቸው የማይፈልጉ ከሆነ በማህረሰቡ አባላት ሊደመሰሱ እንደሚችሉ፤ ይገልጻሉ››፡፡

ከዚህም አንፃር ማህበራዊ ሚናዎች በማበረሰቡ የጋራ ስምምነትና ፍላጎት የሚመሰረቱ ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሚናዎች ምንም እንኳን የጋራ ተቀባይነት ቢኖራቸውም በጊዜ ሂደት በማህበረሰቡ ዘንድ አስፈላጊነታቸው እየቀነሰ የሚሄድ ከሆነ በሌላ የመተካት ወይም የመለወጥ ሁኔታ ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡ በተተኳሪ

ማህበረሰብ ሴት ከተፈጥራዊ ገፅታ ባሻገር በማህበራዊ እንቅስቀሴና ደንብ መሰረት ያላቸውን ሚና አጉልተው የሚያሳዩ ቃል ግጥሞች አሉ፡፡ እነዚህን ቃል ግጥሞች በተለያዩ አውዶችና መነሻ ምክንያታቸውን በመከተል በማዜምና በመቀኘት የሴቶችን ማህበራዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ሚና እንዳላቸው በማንፀባረቅ ተስተላልፎው እንዲቀጥል ያደርጋሉ፡፡ በዚህም ይህ ተከታታይ ክዋኔና እሳቤ ልማድ እየሆነ የሚመጣበት ሁኔታ አለ፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ፁሁፍ ቅኝት

የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ደግሞ ከዚህ ስራ አስቀድሞ በርዕሱ ዙሪያ የተደረጉ ተዛማጅ ጥናቶች ተከልሰው የቀረቡበት ነው፡፡እኔ ይኼ በተነሳሁት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ሊያግዙኝ የሚችሉ በቂ ቀደምት ጥናቶችን ባለማግኘት አራት በሴትንትና በቃል ግጥሞች ዙርያ ትኩረታቸው ያደረጉ እንዲሁም በተለያዩ የማህበረሰብ ከፍሎች ላይ ተዛማጅነት ካላቸው ጥናቶች መካከል አራት የሚደርሱትን በመዳሰስ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ለማየት ሞክሪያለው፡፡ ቅኝት ካደረኳቸው መካከል የመጀመሪያው የደብረ ወርቅ ሞላ (2010) “የአሆላሌ ጨዋታ ቃል ግጥሞች ፋይዳ ትንተና” በአምባሰል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ከፊል ማሟያ በሚል የቀረበ ነው፡፡ በጥናቱም ሴት ልጃገረዶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ማህበራዊ እይታዎችን የሚገልፅ ጥናታዊ ስራ ነው፡፡ ይህ ጥናት ዋና ዓላማ የአሆላሌ ጨዋታ የቃል ግጥሞች ፋይዳ ትንተና፡፡ ልጃገረዶቹ ግጥሞቹን የሚደረድሩባቸውን የጨዋታ አይነቶች ለይቶ መግለፅ፣ ልጃገረዶቹ ዕርስ በርስ ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነት እና የዕለት ተዕለት ውሎ ምን እንደሚመስል መግለፅ፣ የቃል ግጥሞቹን አደራረስ፣ ተስተላልፎና በማን፣ ለማን፣ ለምን፣ እንዴት እንደሚከወኑ መግለፅእና የጨዋታው ቃል ግጥምች ከዋኝና ተሳታፊዎች በክዋኔ ወቅት ያላቸውን ሚና መግለፅ የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችንም አካቶ የያዘ ነው፡፡ ጥናቱ የራሱ የሆነ ተደረሽነት ያለው ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎች ከዋናው ዓላማ የተመዘዙና የተደገፉ መሆናቸው ስራውን ያጠነክሩታል፡፡ ሆኖም ግን ጥናቱ የከበራውን ጊዜና ወቅት፣ የጫወታ አይነት በጥልቅና በተያያዥነት ቢገለጽ የተሻለ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከእኔ የጥናት ርዕስ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም የእኔ ጥናት ለሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞች መመርመር

የሚል በመሆኑ በአንፃሩ የተለየ ያደርገዋል። ይህም የደብረ ወርቅ ጥናት በሴት ልጃገረዶች ብቻ የተመሰረተ ሲሆን የእኔ ጥናት በሁሉም ዘርፍ የሴቶችን ሚና የሚያነፀባርቁትን ቃል ግጥሞችን የሚዳስስ ነው።

ሁለተኛው ጥናት ደግሞ ሀብታም ተሾመ (2013) "የጾታ ሚና አቀራረጽ ልማድ በሁለት እጁ እነሴ ወረዳ በደብረ ማርያም ቀበሌ ማሳያነት" በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው። የጥናቱ ዋና ዓላማ በልጆች አስተዳደግ ውስጥ ያሉ የጾታ ሚና አቀራረጽ ልማዶችን መመርመር የሚል ነው። ይህንን ዋና ዓላማ መሰረት በማድረግ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት። ማህበረሰቡ ለወንዶች እና ለሴቶች ልጆች የሚሰጠውን ጾታዊ ሚና መግለጽ፣ ጾታዊ ሚናዎች በልጆች አስተዳደግ ውስጥ የሚቀረጹበትን መንገድ ማሳየት እና የጾታ ሚናዎችን ፋይዳ ማሳየት የሚሉትን የያዘ ሲሆን በአንፃሩ ከእኔ ጥናት ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም ሴቶች ለልጅ እስተዳደግ ያላቸውን አስተዋፆኦ የሚያትት ነው። በመሆኑም የእኔ ጥናት በቃል ግጥሞች አማካኝነት የሚሰነዘሩ የሴቶችን ፆታዊ፣ የማህበራዊ፣ ተግባራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ስነ ልቦናዊ ሚናዎችን በፈርጅ ለማሳየት የተጠና ነው።

ሶስተኛው ሀብታም ግዛት (2006) "የዳባት ወረዳ ገበሬዎች የስራ ቃል ግጥሞች ክዋኔና ማህበራዊ ህይወታቸው" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የሚል ሲሆን የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በተለያዩ የስራ አይነቶች /አጋጣሚዎች/ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚያዜሟቸውን ግጥሞች በአውዳቸው በመሰብሰብ የሚያነሷቸውን ርዕሰ ጉዳዮች መተንተን፣የግጥሞቹን ማህበራዊ ፋይዳ መግለፅና ገበሬዎች ያላቸውን ማህበራዊ ግንኙነትና የዕለት ተዕለት ውሎ ማሳየት ነው። ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው። ገበሬዎች ግጥሞችን የሚደረድሩባቸውን የስራ አይነቶች ለይቶ መግለፅ፣ ገበሬዎች እያንዳንዱን የስራ አይነት ሲያከናውኑ የሚያዜሟቸውን ግጥሞች ርዕሰ ጉዳዮች መተንተን፣ ገበሬዎች እርስበርስ ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነት እና የዕለት ተዕለት ውሎምን

እንደሚመስል መግለፅ፣ የቃል ግጥሞቹን አደራረስ፣ ተስተላልፎና በማን፣ ለማን፣ ለምን፣ እንዴት እንደሚከወኑ መግለፅ፣ የስራ ቃል ግጥሞች ከዋኝና ተሳታፊዎች በክዋኔ ወቅት ያላቸውን ሚናመግለፅ፣ ሴቶች በግብርና ስራ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ መግለፅ  የሚሉን የያዘ ሲሆን በዚህ ስራ ዋና ዓላማው በአጭር ያልተቀረፀ፣ በይዘት፣ በቦታና በጊዜ ያልተመጠነ እንደሆነ መታዘብ ችያለሁ፡፡  እንዲሁም ዝርዝር አላማ ዎቹም ተመሳሳይ ሃሳብ የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ከእኔ ስራ ጋር ለገበሬዎች ስራ ማበረታቻ የሚሆኑ ቃል ግጥሞች ፋይዳ የሚሉት ተመሳሳይነት ቢሆንም በፆታ ያልተለየ ነው፡፡ በመሆኑም የእኔ ጥናት ለሴትነት ሚና ማደላደያነት አስተዋፆኦ ያላቸው ቃል ግጥሞችን የሚመለከት ነው፡፡ የሀብታም ጥናታዊ ስራ በግብርና ስራ ለተሰማሩ አርሶ አደሮችን የስራ እንቅስቃሴና ሂደታዊ መሰተጋብሮችን የሚያሳይ ሲሆን በፆታ ደረጃ ሴት ወይም ወንድ ተብሎ የተከፈ የለውም፡፡ በዚህም ከእኔ ጥናታዊ ስራ ጋር የተለየ ያደርገዋል፡፡

አራተኛው ደግሞ አብዱራህማን ፈንታሁን (2006)«የሐጅ ሁሴን ዓለሙ (የነሼህ ዳንግላ) የመውሊድ ባዓል ስርዓትና ቃላዊ ግጥሞች(መንዙማዎች) ክዋኔ ጥናት»፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በዓል ስርዓተ ክዋኔና ቃላዊ ግጥሞችን ከአውዳቸው አንጻር ትንታኔ መስጠት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡ በዳንግላ ከተማ የሚከበረው የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ ስርዓተ ክዋኔ ምን እንደሚመስል በሁነቶች ላይ በመመስረት የክዋኔውን አውድ ማብራራት፤ በስርዓተ ክዋኔው ላይ የሚቀርቡት ቃላዊ ግጥሞች እንዴትና ለምን እንደሚቀርቡ ተግባራቸውን በአውድ በመመስረት ማሳየት፤ የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) መውሊድ ተሳታፊዎች ለበዓሉ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሆነ መግለጽ፤ የስርዓቱ ተሳታፊዎች  በስርዓቱ ላይ መገኘታቸው  የሚያስገኝላቸው  ጠቀሜታ ማብራራት የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ይህ ጥናትም በእስልምና እምነት ተከታዮች በመውሊድ ባዓል የሚያዚሟቸውን የመንዙማ ቃል ግጥሞች ይዘት፣ አይነትና ፋይዳ መመርመር ላይ ትኩረት ያደርገ ነው፡፡ ከእኔጥናት ጋር የሴትነትን ሚና የሚገልፁ የቃል ግጥሞች ፋይዳ በሚለው ፅንሰ ሃሳብ ተመሳሳይነት ቢኖረውም የአብዱራሃማን ስራ በመንዙማ ግጥሞችና

ውስን አውድ ላይ ያነፃፀረ ሲሆን የእኔ ጥናት ግን በተለያዩ የስራ ዘርፎችና እንቅስቃሴዎች የሴትነትን ሚና መደላደል ሊገልፁ የሚችሉ ቃል ግጥሞችን የሚዳስስ ነው፡፡ ከወቅትና ከጊዜ አንፃርም ከእኔ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡ የአብዱራሐማን ጥናት የራሱ የሆነ ተደራሽነት ያለው ሲሆን የጥናቱ ዋና አላማ በአንፃሩ የተመጠነ አይመስልም፡፡ እንዲሁም ዝርዝር አላማዎቹ ከዋናው የተፈለፈሉና ተያያዙ አይመስሉም፡፡

በአጠቃላይ በቅኝቱም ጥናቱ ከቀደሙት ተዛማጅ ጥናቶች ጋር በምን እንደሚመሳሰል እና እንደሚለያይ ለማየት፣ እንዴት እንደተሰራ ለማስረዳት እንዲሁም የጥናቱን መደረግ አስፈላጊንት ለማረጋገጥ ያገገለገለ ነው፡፡ በደብረታቦር ከተማ ይህንን ርዕሰ ጉዳይ የተመለከተ ጥናት ሳካሂድ የተላዩ መዛግብቶች ማገላበጥ እና በባህሉና በቋንቋው ዘርፍ የተማሩና ያገለገሉ ምሁራንን ለማናገር ሞክሪያለው በሴትንት ሚና ዙሪያ የሚያጠኑ በተመለከተ ሁለት ተቀራራቢ ጥናቶች ውጪ የታተመም ሆነ በየመስሪያ ቤቱ የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፎችን ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ይሁን እንጅ በተለያዩ አካባቢዎች ስለ ቃል ግጥም የተሰሩ ተዛማጅ ጥናቶች አሉ፡፡ ከዚህ ርዕስ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ባይኖራቸውም በየማህበረሰቡ የተለያየ ስያሜዎች የሚጠሩ ታላላቅ ሰዎችን የሴትነት ሚናቸውን በተወሰን መልኩም ቢሆን የሚያነሱ በመሆኑ እና ይህም ጥናት በዋናነት በሴትነት ሚና ቃል ግጥም ላይ ተምስርቶ ዋነኛ የሆነውን የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥም ለመመርመር ተዘጋጅቷል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.የደብረታቦር ከተማ አካባቢያዊና ማህበረ ባህላዊ መልክ

በዚህ ምዕራፍ ተተኳሪ ማህበረሰብ ስለ ሚገኙበት የደብረታቦር ከተማ መልካምደራዊ ሁኔታ እና ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ገፅታዎች ወይም ሴቶችን ለማደላደል ሚና ስላላቸው ቃል ግጥሞች መነሻነትና ፋይዳ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡ ከተማው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ ዞኖች በደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ ይገኛል፡፡ ከተማው በዞኑ በሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ ተከዜ፣ ጉና፣ ርብ፣ በሽሎና ጉማራ የልማት ቀጠና ውስጥ ይገኛል፡፡ አንፃራዊ መገኛውም በሰሜን ከእብናት እና ከሊቦ ከምከም ወረዳዎች፣ በደቡብ ከእስቴ ወረዳ፣ በምስራቅ ከላይ ጋይንት ወረዳ እና በምዕራብ ከፎገራ ወረዳ ጋር ይዋሰናል፡፡ ማህበረሰቡም ከእነዚህ ወረዳ ህዝቦች ጋር አንፃራዊ የሆነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ተጋርቶ ይኖራሉ፡፡

### 3.1. የከተማው አጭር ታሪክና የህዝብ ሁኔታ

የደብረታቦር ከተማ አመሰራረትና አሰያየም ከብዙ የሀገሪቱ አስተዳዳሪ ከነበሩና ከነገስታት ዘመነ መንግስት ጋር የተቆራኙ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል÷

የደብረታቦር ከተማ ከ14ኛው እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በአጼ ሰይፈ አርዕድ እንደ ተመሰረታና እንደ ተጀመረ ይነገራል፡፡ ከተማው ስሙን ያገኘውም በንጉሱ አራተኛው ዓመት ከሰሩት ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ከቆመበት ተራራ እንደሆነ እና በደብርታቦር ኢየሱስ ገዳም በሚገኘው ግብረ ህማም ውስጥ ራስ ጉግሳ ወሌ እንደሆንም ይነገራል፡፡ በተጨማሪም ታቦር በእስራኤል (ፍልስጤም) ምድር የሚገኝ አምሳያ ተራራ ሲሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሳዔው በኋላ ለሶስቱ ሃዋርያት የተገለጠበት እንደሆነ (የከተማው ባ/ቱ/ማ ፅ/ቤት፣ 2003 ዓ/ም ያዘጋጀው መፅሄት) ያስረዳል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ስለ ከተማው አመሰራረት እንዲህ ይገለፃል፡፡ በጌምድር ከጥንት ጀምሮ ህዝብ ሰፍሮ የሚኖረበት በመሆኑና የክርስትና እምነትም ለብዙ ምዕተ ዓመታት ያህል ፀንቶ በመቆየቱ በአፄ ሰይፈ አርዕድ ጊዜም ይሁን በሌሎቹ በአምደ ፅዮን 1314-1344፣ በአጼ ዳዊት 1382-1411 ወ.ዘ.ተ በነበሩት ነገስታት ለዘመቻ

ሲዘዋወሩ በአካባቢው ቤተክርስቲያን ሰያቆሙ፣ ከህናት ሲሰይሙ፣ ጉልት ሲጎልቱና ግብር ሲተክሉ ኖረዋል። በመሆኑም በየጊዜው ሲመሩና ሲለቁ የቆዩ ገዥዎች ሲያፈርሱና ሲሰይሙ ማሳለፉንም ያስረዳል። በሌላ በኩል በአፄ ልብነ ድንግል ዘመን ደብረታቦር ጁራ ወይም ሰመራ ይባል እንደነበር በዝርዝር መግለጫው ያስረዳል፤ (የከተማው ባ/ቱ/ማ ፅ/ቤት፣ 2003 ዓ/ም ያዘጋጀው መፅሄት)። ደብረታቦር የብዙ ነገስታትና መንግስታት መቀመጫ በመሆንና በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚዊና ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊ ሁነቶችን በየስዓቱ አሳልፈውበታል። ከብዙ ዘመን መገለባበጥ በኂላ የደብረታቦር ከተማ የአሁን ቅርፅና አወቃቀር ይዟል። በዚህም የደቡብ ጎንደር ዞን ዋና ከተማና የፋርጣ ወረዳ ማዕከል በመሆን ያገለግላል።

### 3.1.1. የከተማው የአየር ፀባይና መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ

ከተማው ቀዝቃዛ ሚባል የአየር ንበረት ያለው ሲሆን ከባህር ወለል በላይ 2200 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኝ ከተማ ነው። የከተማው ሙቀት መጠን ከ10 ሲንቲ ግሬድ እስከ 80 ሲንቲ ግሬድ ይደርሳል»፤ (የከተማው ባ/ቱ/ማ ፅ/ቤት፣ 2003 ዓ/ም ያዘጋጀው መፅሄት) ይህ የአየር ንብረት ተከትለው የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የራሳቸው የአኗኗር፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ ስልት አሏቸው። ከነዚህ መካከል ወንዶች ስፌና ወፍራም ጋቢ፣ ፎጣ፣ ቦት ጫማ የሚዘወትሩ ሲሆን ሴቶች ረጅም ቀሚስ፣ ኩታ፣ ሻሽና መቀነት በመልበስ ይታወቃሉ። ከአመጋገብ አኳያ ደግሞ ድንች፣ገብስ፣ ባቄላ፣ግብጦ፣ ኮረፌ ጠላና ሰማ ወ.ዘ.ተ የምግብ አይነቶች አሏቸው።

"ከዚህ የአየር ንብረት ጋር ተዛምደው የሚኖሩ 62829 የሚደርሱ የህብረተሰብ ክፍሎች አሉ። እነዚህም የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ የሃይማኖት ስብጥር ያላቸውና በመረዳዳት፣ በመከባበር ላይ የተመሰረተ ማህበረ ባህላዊ ስርዓቶች አላቸው፡ ፡ ከተማው በአሁን ስዓት ስድስት የከተማ እና አራት የገጠር ቀበሌዎች የተከፈለና የተደራጀ ነው"፤ (የከተማው ባ/ቱ/ማ ፅ/ቤት፣ 2003 ዓ/ም ያዘጋጀው መፅሄት) ።

ለከተማው የልማት አስተዋፆኦ ካላቸው ውስጥ የአካባቢው የቱሪስት መስዕብ ተጠቃሽ ነው። በከተማው የቱሪስት መስዕብ ተብለው ከሚገለፁት መካከል የፈረስ ጉግስ፣ የወጣቶች የቡሄ ጨዋታ(የደብርታቦር በዓል)፣ የጋፋት እንዱስትሪና የተለያዩ አብያተ

ክርስቲያናት ይገኙበታል፡፡ የፈረስ ጉግስ የሚባለው የተለያዩ ሃይማኖታዊ ከበራዎችንና ፌስቲቫሎችን መሰረት በማድረግ የሚከበር ባህላዊ ጨዋታ ነው፡፡ ይህንም በተመለከተ አቶ ፀጋ ሽበሽ ሲገልፅ÷ «የፈረስ ጉግስ በደብረታበርና አጎራባች ወረዳዎች የተለመደ አገረሰባዊ ጨዎታ ነው፡፡ ይህም በመስቀልና በጥር መርቆሪዮስ በዓላት የሚቀርብ ባህላዊ ጨዎታ ነው፡፡ እንዲህም ይባልለታል፤

ይገርመኛል የፈረስ ጉግስ ጨዎታ

የቀደመውን የሚያስመታ፤ እየተባለ የሚነገርለት ነው»፡፡

በተጨማሪም የቡሄ በዓል የሚጠቀስ ነው፡፡ ቡሄ በአመት አንድ ጊዜ በወርሃ ነሐሴ የሚከበር የወጣቶች ባህላዊ ጨዎታ ነው፡፡ ይህም ሲከበር ከሀይማኖታዊ ይዘቱ በዘለለ የአካባቢው ማህበረሰብ ከወቅቱ እና ከቦታው ተፈጥሯዊ ሁኔታ በመነሳት የሚከወን ነው፡፡ አቶ ደመቀ አላምር ሲገልፅ÷ «በሄ የልጆችና የወጣቶችን ባህላዊ ጨዋታዎችንና መገለጫዎችን የሚታይበት በዓል ነው፡፡ ወንዶች ዳቦና ጅራፍ በመያዝ በየ ሰፈራቸው ቡድን በመመስረት በቃል ግጥሞች እየተነቃቀፉና እየተገራረፉ የሚከውኑት ስርዓት ያለው ባህላዊ ጨዋታ ነው፡፡ ሆኖም ሴቶች ዳቦ ወይም ሙልሙል በማዘጋጀት ሚናቸውን ይወጣሉ»፤ በማለት ያስረዳል፡፡

በከተማው ከሚገኙ የቱሪስት መስዕቦች መካከል አንዱ የጋፋት የኢንዱስትሪ መንደር የሚጠቀስ ነው፡፡ ይህም በአፄ ቴወድሮስ ዘመነመንግስት እንደተጀመረ ታሪክ ያስረዳል፡፡ ጋፋት አሁን ላይ በዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶችና ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች እየተሰራበት ያለ ሲሆን ከቀደመ ታሪኩ ጋር በማስተሳሰርም በከተማው ካሉ የቱሪስት መስዕቦች ውስጥ እንደተመደበ የአካባቢው ነዋሪዎች ይገልፃሉ፡፡ ከተማው በአብዛኛው በከተማ መር ኢንዱስትሪ እና በገጠር ግብርና ኢንዲስቱሪ ሚተዳደሩ የማህበረሰብ ክሎች ይገኙበታል፡፡ ይህም ሲሆን የፆታና የስራ ክፍፍል ቢኖርም ሴቶች በሁሉም የስራ ዘርፎች ተሳታፊ ሆነው ይገኛሉ፡፡

## 3.2. ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረዳጃ እና ዝምድና መፍጠሪያ ተቋማት

ማህበራዊ መረዳጃ ተቋማትና ባህላዊ የዝምድና መፍጠሪያ ስልቶች የአንድ ማህበረሰብ የአኗኗር፣ የአስተሳሰብና አተገባበር ሚናዎችን ያንፀባርቃሉ፡፡ በዚህም የደብረታቦር ከተማ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ማህበረ ባህላዊ እሴቶች ወይም መረዳጃ

ተቋማት የማህበረሰቡን የአንድነትና የአብሮነት መንፈስ የሚጠናክሩ ናቸው፡፡ አንድነትን የሚያጠናክሩ የመረዳጃ ተቋማት እና ማህበረ ባህላዊ እሴቶች የሴትነትን ሚና ለማደላደል፣ የማህበረሰቡን ልማድ ምንነት በማሳወቅ እና በማስተማር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ ከነዚህም የሴትነትን ወይም እንስታዊነትን አጎልተው ሊያሳዩ የሚችሉ ልማዳዊ እሳቤዎችና ድርጊተቶችም መካከል በማህበረሰቡ ዘንድ የሚመሰርቷቸው የመረዳጃ ተቋማት እድር፣ እቁብ፣ ክርስትና፣ ወንፈል እና የቤተሰብ አመሰራረት የሚሉት የዝምድና መፍጠሪ ስልቶች የሚገለፁ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሴቶች በቤት ውስጥ ሆነ በአካባቢው የሚተገብሯቸውን ማህበራዊ ባህላዊ የስራ ሃላፊነቶች የቤት አያያዝ (ሰነ ውበት)፣ የሴቶች ማህበራዊ ኑሮ፣ እና የልጅ አስተዳደግ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### 3.2.1. እድር

እድር ማህበራዊ ተቋማት ከሚባሉት አንዱ ነው፡፡ ይህ ተቋም በተተኳሪ ማህበረሰብ ዘንድ እንደ መረዳጃና ሌሎች ማህበራዊ ደንቦችን ወይም ህጎችን ለማስተግበሪያነት የሚያገለግል ማህበራዊ ተቋም ነው፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ ፀጋ ሽበሽ ሲገልፅ፥ እድር በአካባቢያችን ለረጅም ጊዜ የቆየና አሁንም በሰፊው እያገለገለ የሚገኝ ማህበራዊ ተቋም ነው፡፡ እድር የሌለው ሰው ከንቱ ይህ ማለት ሲኖር ብቻ ሳይሆን ሲሞትም ቀባሪ የለውም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ማንኛው ሰው በማህበራዊ እድር ተቋም የሚሳተፍና የሚተዳደር ሲሆን በአደረጃጀቱ የሚቀረፁ ህጎችና ደንቦችን ማክበር ልማዳዊ ህጎች ወይም ደንቦችን የሚተላለፉ አባላት ተጠያቂ ያደርጋል፤ ይላል (ቃለ መጠይቅ፣ሃምሌ12/11/14ዓ/ም)፡፡

ከዚህም አንፃር ተተኳሪ ማህበረሰብ በቋሚነት ከሚመሰርቷቸው ማህበራዊ መረዳጃ ተቋማት ውስጥ አንዱ ሲሆን ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ራሳቸውን መምራት ወይም ቤት መመስርት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ሊሳተፉበት የሚችሉበት ተቋም ነው፡፡ በአብዛኛው በዚህ ተቋም መሳተፍ ግዴታ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ማህበራዊ ተቋም ሲመሰረት በሚፈልጉት ስልት፣ቅርፅና ቡድን የሚዎሰን ሲሆን አደረጃጀተቸውም የወንድና የሴት በማለት ይሆናል፡፡ ወ/ሮ አስረበብ ምትኩ ስትገልፅ፥«እድር ለህይወታችን እንደ መደን እንዎስደዋለን፡፡ ይህም ማለት ሰው ሲሞት ልቅሶውን በስርዓት መከዎን የሚያስችል፣ የሟች ቤተሰቦችን በማፅናናት፣

በመደገፍና በመርዳት ብቸኝነት እንዳይሰማቸው ማድርግ የሚያስችል ነው፡፡ ከሚያስገኝን ጠቀሜታ በመነሳት እኛም የሴቶች እድር በማቋቋም እንደደጋገፋለን፣ እንርዳዳለን»፤ ትላለች(ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ25/10/14 ዓ/ም)፡፡ እድር በተተኳሪ ማህበረሰብ ሴቶችም ለራሳቸው ቡድንና ማህበራዊ ተቋም በመመስረት ይረዳዳሉ፤ ማህበራዊ ችግሮችን በጋራ መፍታት የሚያስችል የመረዳጃ ተቋም እንደሆነ ማወቅ ተችሏል፡፡

## 3.2.2. እቁብ

እቁብ በተተኳሪ ማህበረሰብ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ ሁነቶች ቡድኖች የሚረዳዱበትና የሚደጋገፉበት ማህበራዊ ተቋም ሲሆን በዚህ ማህበራዊ ተቋም ሴቶች በራሳቸው የአደረጃጀት ስልትና ደንብ በመሳትፍ ሚና እንዳላቸው በመስክ ሂደቱ ማወቅ ችያለሁ፡፡ ወ/ሮ አትጠገብ መልኬ÷ «ለእኛ ለሴቶች ትልቅ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም በገንዘብ፣ በሃሳብ፣ በማህበራዊ ህይወታችን እንድንደጋገፍ ሚና ያለው ተቋም ነው»፤ ትላለች(ቃለ መጠይቅ፣ሰኔ 25/10.14 ዓ/ም)፡፡ እቁብ ቡድኖች እንደሚፈልጉት ዓላማ ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ በማለት የሚመሰረት ሲሆን በተተኳሪ ማህበረሰብ የሚገኙ ሴቶች በቁብ በገንዘብ፣ በሃሳብ፣ በሌሎች ስራና ማህበራዊ ሁኔታዎች ለተቸገሩ አባላት መፍትሄ ለመስጠት፣ ለመረዳዳት ሚና እንዳለው ይገልፃሉ፡፡

## 3.2.3. ወንፈል

ሰዎች ለሚፈልጉት አላማ ቡድን ይመሰርታሉ፡፡ ይህ ቡድንም ለችግሮች መፍትሄ ለመስጠት፣ ተግባብቶ ለመኖር የጋራ ህይወትን ለማጣጣም ሲባል የሚመሰረት ይሆናል፡፡ ከሚመሰረቱ የቡድን ስልቶች ውስጥ ወንፈል አንዱ ነው፡፡ መ/ር ትግስት አለሙ÷ «ወንፈል የጋራ የሃሳብና የስራ ክንውን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ነግለኔ (በእኔም አለ፣ይደርሳል) በማለት የሚተገበር፤ በጋራ መስራትና ማሰብ የሚያስችል ማህበራዊ መረዳጃ ስልት ነው»፤ ትላለች(ቃለ መጠይቅ፣ሰኔ 25/10/14 ዓ/ም)፡፡ ተተኳሪ ቡድኖች ወንፈልን ሲተገብሩ ነገ ይደርስብኛል አለያም በተናጠል የማያልቁ፣ የማይመቹና የማይከዎኑ ክርስትና፣ ሰርግ፣ ልቅሶ፣ የተለያዩ ስራዎችን እና ሁነቶችን የያዘ ሲሆን ከሚኖረው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አኳያ ቡድኖች የሚሳተፉበት

መረዳጃ ስልት እንደሆነ ማወቅ ተችሏል፡፡ በተተኳሪ ማህበረሰብ የሚገኙ የሴቶች ቡድኖች በአካባቢያቸው ከሚተገብሯቸው የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያ መረዳጃ ተቋማት በተጨማሪ ለዝምድና መመስረቻና የመደጋገፊ ማህበራዊ ስልቶች እንዳሏቸውም ማወቅ ተችሏል፡፡ በአካባቢው ከሚተገብሯቸው ተግባሮች መካከልማህበራዊ ባህላዊ የስራ ሃላፊነቶች የቤት አያያዝ (ሰነ ውበት)፣ የሴቶች ማህበራዊ ኑሮ፣ እና የልጅ አስተዳደግ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## 3.2.4. የቤተሰብ አመሰራረት

የሰው ልጅ ከተናጠላዊ ህልውናው ይልቅ ቡድናዊ ህይወቱን ይበልጥ ይመርጣል፡፡ ይህም ቤተሰብ ለመመስረት የሁለቱም ፆታዎች ማለትም የሴትና ወንድ ጥምረት ቀዳሚ ጉዳይ ነው፡፡ ተተኳሪ ማህበረሰብ እንደሌሎች አካባቢ ቡድኖች ሁሉ ባህላዊ የሰርግ ስርዓትን መሰረት አድርገው ሴትና ወንድ ጎጆ ወይም ቤተሰብ ይመሰርታሉ፡፡ ይህንም በተመለከተ አቶ ደረጀ ወርቁ እንዲህ ነግሮኛል÷ ወንድ ሆነ ሰሴት ብቻዋን መኖር በአካባቢያችን ነውር ነው፡፡ ቁሞ ቀር፣ ዘር የለሽ የሚባሉ ግሳዔዎች ይከተላሉ፡፡ በመሆኑም ለወንዱ አቅመ አዳምና ሴቷ ለአቅመ ሄዋን ከደረሱ በሀገር ባህል ደንብ የወንድ ቤተሰብ የሴቷን ቤተሰብ ሽማግሌ በመላክ ያጫሉ፤ የሴቷ ቤተሰብም በዝምድናው ካመኑበት የጭራ ማሰረሪያ (የቃል ማሰሪያ) ይቀቀበላሉ፤ ቀን ቆርጠው ሰርግና ምላሽ አድርገው ልጆቻቸውን ይድራሉ፤ ይላል (ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ27/10/14 ዓ/ም) ፡፡ ከዚህም አንፃር የቤተሰብ መመስረቻ መንገዶች መካከል አንዱ ጋብቻ ሲሆን የወንድና የሴት ልጆች ቤተሰቦች በሀገር ባህል ደንብ መሰረት ልጆቻቸውን በማጋባት የራሳቸውን ህይወት እንዲ መሩ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም ሁለቱ ጥንዶች ከቤተሰቦቻቸው የቀሰሟቸውን ልምድና ስልት ተከትለው ሌላ ቤተሰብ ይመሰርታሉ፡፡ በዚህ ሂደትም እናት ልጇን በግብር፣ በስራና በስልት በሚገባ በመቅረፅ ሚና እንዳላትም ወ/ሮ አስረበብ ምትኩ እንዲህ ትላለች÷ «እኛን ቤተሰቦቻችን እንደ ዳሩን፣ እንደ ኳሉን ሁሉ ልጆቻን አይናቸውን በአይናቸው እንዲዩ፣ እኛም ለፍተን ያሳደግናቸውን ቁም ነገር ማስያዝና ራሳቸውን ለማስቻል እድሜያቸው ሲደርስ እንድራለን፤ እናት የምትደሰትበት፣ ውጤቷን የምታይበት ይሆናል፡፡ ያልዳረ፣ ያልኳለና እርጥብ ዳስ ያላየ እናት አባት ከንቱ ነው ይባላል»፤(ቃለ መጥቅ፣ቡውድን ተኮር ውይይት ሃምሌ16/11/14 ዓ/ም)፡፡ በዚህም ጋብቻ ሴት ሚናዋ ምን ያህል ነው? ለሚለው ጥያቄ፤«ሴት በለመደችው

የቤት ስራ፣ ጠላውን፣ ምግቡን በማዘጋጀት፣ ልጇቷን (ሙሽ ራዋን) ስራ በማስተማርና በመቅረፅ በባህሉ መሰረት ማስዋብና መሞሸር የመሳሰሉትን ታደርጋለች»፤ ትላለች (ቃለ መጠይቅ፣ ሃምሌ12/11/14ዓ/ም) ፡፡

### 3.2.5. የሴቶች የስራ ሃላፊነት

በተተኳሪ ማህበረሰብ የሴትነት ሚና የሚያሳዩ ልማዳዊ ድርጊቶችና እሳቤዎች አሏቸው፡፡ ሴት እናት፣ ሚስት፣ አያት፣ አይት፣ አክስት፣ጓደኛ እና እህት በመሆኗ የቤት አያያዝና ሌሎች የቤት ውስጥ የስራ ሃላፊነቶች እንደ ሌሎች አካባቢ ማህበረሰቦች ሁሉ የሚሰጥ ቢሆንም በእነዚህ ቡድኖች የተለመዱ ክዋኔዎች አሉ፡፡ ትግስት አሸናፊ ስትገልፅ÷ «ሴት ልጅ በስራ ክፍፍሉና ሃላፊነት ላይ ሚናዋ ብዙ ነው፡፡ በቤት ውስጥ ምግብና መጠጥ ዝግጅት፣ልጅ አስተዳደግ፣ የፆታ ቀረፃ፣ ይሁን ከቤት ውጭ በማህበራዊ ኑሮ በመሳተፍ፣ የግብርና ስራዎች መሳተፍና ለባሏ፣ ወንድሟና አባቷ ረዳት፣ አሌንታና ጉልበት በመሆን ሃላፊነቷን ትዎታለች»፤ ትላለች(ቃለ መጠይቅ ሃምሌ12/11/14 ዓ/ም)፡፡ በተተኳሪ ማህበረሰብ ሴት ልጅ ያላትን የስራ ሃልፊነት በመስክ ቆይታዬ ባህላዊ የምግብ ዝግጅት፣ የልጅ አስተዳደግና የፆታ ቀረፃ፣ አምጦ የመውለድ፣ የማርገዝ እና የቤት ውበት የመጠበቅ ሃላፊነት በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በደብረታቦርና አካባቢው ማህበረሰብ ድንች፣ ሳማ፣ የስንዴ ዳቦ እና ኮረፌ ጠላ በብዛት የሚታወቁ ባህልዊ ምግብና መጠጦች ናቸው፡፡ ሴቶች እነዚህንና ሌሎች ምግብና መጠጦችን በማዘጋጀት የስራ ሃላፊታቸውንና ሚናቸውን ይወጣሉ፡፡

#### 3.2.5.1. የልጅ አስተዳደግ ስልት

የልጅ አስተዳደግ ሚና ወይም ስልቶች ገና ከእናታቸው ማህጸን ከመውጣታቸውና ከተወለዱ በኋላ እንዲሁም ተፈጥሯዊ ፆታቸው ከሚታወቅበት ጊዜ እንደሚጀምር ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገበት ማህበረሰብ ይገልፃሉ፡፡ ልጆች ከመወለዳቸው በፊት በእርግዝና ወቅት አንዳንድ ወላጆች የሚወለዱ ልጆች ጤነኛ እንዲሆኑ፣ ወላጆች የሚመኙትንና የሚፈልጉትን ተግባር ወይም ድርጊት መፈፀም የሚችሉ እንዲሆኑላቸው ለእርጉዟ ሴት ልዩ ምግብና መጠጥ እንድትመገብ በማድርግ፣ ጥሩ ነገር እንድትመለከትና ከአስጨናቂ ጉዳዮች እንድትርቅ ያደርጋሉ፡፡ ትግስት አለሙ

÷"እኛ ጥሩ ልጅ እንዲወለድ ሴት እንዳረገዘች ያየቸውን፣ ያማራትን እንድትበላ ማድርግ፣ አለማስጨነቅና ለሚወለደው ልጅ መልካም አእምሮና ጤነኛ እንዲሆን እንከባከባለን። ይህም ወደፊት የሚያሰጉ ክስተቶችን ለመከላከል ሲባል ነው"፤ ትላለች(ቃለ መጠይቅ፣ሃምሌ12/11/14/ዓ/ም)። በቅድመ ወሊድ ጊዜ እርጉዟን ሴት መከባከብ ለሚወለዱ ልጆች ስርዓት፣ ደህንነትና መልካምነት ሲባል የሚከዎን ልምዳዊ ተግባር እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ድህረ ወሊድ ጊዜ ደግሞ በማህበሰቡ ልማዳዊ የልጅ አስተዳደግ ስልትና ስርዓት የሚከዎኑ ድርጊቶችና እሳቤዎች አሉ። ይህም ከተወለዱበት ዕለት ጀምሮ ስም በማውጣት እና ሌሎች ልማዳዊ ድርጊቶችን በመከዎን ይጀመራል። አቶ ነጋሽ ቢምረው ፣ ልጅ ከተወለደ በኋላ በአካባቢያች ደንብና ስርዓት መሰረት ማደግ አለበት። ይህም የሚሆነው ነፍስ ካወቁ ጀምሮ ትንሾቹ ትልቆቻቸውን እንዲያከብሩ፣ ምግብ ሲበላ ትንሾች ተራቸውን ተብቀው ይበላሉ። በቤት ውስጥ ከአቀማመጥ ጀምሮ ቅድሚያ ለትልቆች መስጠት፣ ስም ማውጣትና የትልቆችን ልብስ ተቀብሎ መልበስ ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉት እንዲከባበሩ እንዲረዳዱ እናት አባት ሃላፊነታቸውን ይወጣሉ፤ ይላል (ቃለ መጠይቅ፣ ሃምሌ12/11/14 ዓ/ም)።

ከዚህም አንፃር በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚለመዱና የሚተገበሩ የልጅ አስተዳደግ ስልቶች ወደ አካባቢው በማሳደግ የቡድኖች ልማዳዊ ህጎች እየሆኑ ይመጣሉ። በነዚህ ደንቦች ደግሞ ወላጆች ልጆቻቸውን በመቅረፅና ስራዓት በማስያዝ ሚና ይኖራቸዋል። በአጠቃላይ ተተኳሪ ማህበረሰብ የመተሳሰብ እና የመረዳዳት ፅኑ ባህል ያላቸው እንደሆኑ በጥናት ሂደቱ ማረጋገጥ ችያለሁ። በዚህም ሴቶች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ መስተጋብሮች የራሳቸው ድርሻ ያለቸው ሲሆን በተለያዩ አውዶችም ማህበራዊ ደረጃቸውን ሊያሳዩ የሚችሉ ቃል ግጥሞች ሲዜሙ፤ ሲቀኙ ይስተዋላሉ። በዚህም የሴትን የተለያዩ ተሳትፎዎችንና ሚናዎችን በመግለጥ አሰተዋፆኦ አላቸው።

### 3.2.5.2 የቤት አያያዝ ወይም ስነ ውበታዊ ጉዳዮች

እያንዳዱ ማህበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ የሚያገኘውን ግባዓት ተጠቅሞ ለአካላዊ ሆነ ለስነ ልቦናዊ እርካታው ሲል ይቀርፃል፤ ያዘጋጃል። በዚህም በተተኳሪ ማህበረሰብ

ዘንድ ሴቶች የቤት ሆነ የቤተሰቦቻቸውን ስነ ውበት በመጠበቅ ሚናቸውን ይወጣሉ፡፡ ስነ ውበታዊ ሲባል ልዩ ውስጣዊ ስሜትን ሊያንፀባርቅ በሚችል መልኩ የሚዘጋጁትን የሰው ልጆችን የፈጠራ ውጤቶችን የሚመለከት ነው፡፡ ወ/ሮ አትጠገብ መልኬ÷ «ሴቶች በአካባቢያቸው የሚያገኘነውን ቁስ ተጠቅመን በከብት እበት ቤትን መለቅለቅ (ማሳመር)፣ ጭቃ አቡክተው ድንጋይ ገንብተው መደብ (መቀመጫ ወንበር) እንሰራለን፡፡ በተመሳሳይ በተቦካ ጭቃ ጎታ(የእህል ማስቀመጫ)፣ አከንባሎና ሌሎች የቤት መገልገያ ዕቃዎችን በማምረት ቤታችንን እናሳምረዋለን»፤ ትላለች(ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ፤ ሰኔ 27/10/14 ዓ/ም)፡፡ ሴቶች በቤት ውስጥ ሆነ በውጭ ብዙ ስነ ውበታዊ ጉዳዮችን ሲከዉኑ፣ ሲተገብሩ ይታያሉ፡፡ ይህም በአካባቢያቸው ያገኙትን ግባዓት መሰረት በማድረግ እና ባላቸው የስነ ውበት እውቀት፣ ፈጠራና አስተሳሰብ በማስተሳሰር ቅርፅና ይዘት እንዲኖራቸው በማድረግ ስነ ውበታዊ ጉዳዮችን ይተገብራሉ፡፡

### 3.2.5.3. የሴቶች ማህበራዊ ኑሮ

ማህበራዊ ኑሮ (social life) አንድ ማህበረሰብ በባህሉና ስርዓቱ በሚፈቅደው መሰረት የመረዳዳትና መደጋገፍ ስልት ያለበት ፅንስ ሃሳብ ነው፡፡ በተተኳሪ ማህበረሰብ ሴቶች በሀዘንም ይሆን በደስታ ወቅት ከወንዶች በተለየ መልኩ በመረዳዳት ሚናቸው ከፍ ያለ እንደሆነ ወ/ሮ አስካል ወረታው ትገልፃለች÷

አንድ ግለሰብ ከወዳጅ ዘመዶቹና ቤተሰቦቹ ባሻገር ከጎረቤትና ከአካባቢው ማህበረሰብ ሀዘን ሲሆን ማስተዛዘን ወይም ማፅናናት፤ በደስታ ጊዜ ደስታውን መካፈል ደንብ ነው፡፡ ሆኖም እኛ ሴቶች የራሳችን እድር፣ ማህበር እና ሌሎች መዋቅሮችን በመፍጠር በሁሉም የማህበረሰቡ ደንብና ስርዓት እየተረዳዳን፣ እየተመካከርን እንሰራለን፡፡ ይህ የቡድን ሚናችን ከወንዶች በተሻለ ማህበራዊ አንድነታችን እንዲጠነክር አስተዋፆኦ አለው፤ ትላለች፡፡ (ቃለ መጠይቅ ሀምሌ 30/ 11/14/ዓም) ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ ተተኳሪ ማህበረሰብ ስለሚገኙበት የደብረታቦር ከተማ ማህበረ ባህላዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ገፅታዎች የተገለፀ ሲሆን በተጨማሪም በከተማው ስለሚኖሩ የህበረተሰብ ክፍሎች የአኗኗር፣ አመጋገብ፣ አለባበስ፣ የአስተሳሰብ እና ሴቶች በማህበረሰቡ ስላለቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ሚናዎች በአንፃሩ ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥምች ትንተና

በዚህ ምዕራፍ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውውይት ስልቶች የተገኙ መረጃዎችን አውድን መሰረት በማድረግ በአይነትና በፈርጅ  እንዲሁም በገለፃና በትንተና ቀርበዋል።

## 4.1. በደብረታቦር ከተማ ማህበረሰብ በቃል ግጥሞች አማካኝነት የሚገለጡ የሴቶች ሚናዎች

ስነ ቃል ተስተላልፎው በቃል የሆነ የሰውን ልጅ እውቀት የሚገለፅበት ቃላዊ ጥበብ ነው። ይህም ሲባል ስነ ቃሎች ሲነገሩ፣ ሲዜሙና ሲተረቱ የቡድኖችን የአኗኗር፣ የአነጋገር፣ የአለባበስና የአመጋገብ እንዲሁም ቁሳዊና መንፈሳዊ ሃብቱን ይገልፃሉ። በእነዚህ ቃላዊ ጥበቦች የሴቶችን ደልዳናነት በማጉላት በቡድኖች ውስጥ ያላቸውን ማህበራዊ እና ተግባራዊ ሚናዎችን ለማስቀጠል ኪነ ተግባቦት እንዲፈጠር አስተዋፆኦ ያላቸው ናቸው። በስነ ቃል ዝውግ ውስጥ ከሚካተቱ የስነ ቃል አይነቶች ውስጥ ቃል ግጥም ተጠቃሽ ነው። ቃል ግጥም በቃል ተደርሰው በቃል የሚተላለፉ፣ የሚከዎኑ የህዝብ ሃብት ናቸው። ይህ ጥናትም በደብረታቦር ከተማ ማህበረሰብ ውስጥ የሚዜሙ ቃል ግጥሞች ሴት በማህበረሰቡ ያላትን ሚና እንዴት እንደሚገለጡ ለማሳየት የተሰራ ነው።

ሴት ወይም የሴትነት ፆታዊ ጉዳይ ለሴቶች በተፈጥሮ ከተሰጣቸው ፀጋ በመነሳት በስራ፣ በባህል፣ በተሳትፎ፣ በግጼታና ውዴታ፣ ጥላቻና ፍቅር እንዲሁም የቡድኑን ልማዳዊ እንቅስቃሴ መሰረት በማድረግ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚቀኙና የሚዜሙ ቃላዊ ግጥሞች ማህበራዊ ደረጃቸውን፣ ሚናቸውንና ተግባራቸውን ለመለየት ያስችላል። ይህንንም አስመልክቶ Genilloud (2000, 4) ሲያስረዳ÷ የሴቶች ሚና ሙሉ ለሙሉ የሚገለጸው አንድን ጉዳይ በሚያከናውነው እና በሚከናወነው ጉዳይ ማለትም በተከዋኙ እና በከዋኙ መካከል የሚኖረው መስተጋብር ነው፤ እንደሆነ ይገልጻል።

ስለዚህ፣ ሚና በአድራጊው እና በተደራጊው ጉዳይ መካከል በሚደረግ ግንኙነት መሰረት የሚመጣ ሃላፊነት ነው። የተከዋኙ ጉዳይ ጠባይ የከዋኙን ጠባይ የሚቀርጽ መሆኑንም መረዳት ይቻላል። በአንድ ማህበረሰብም እንበል ቡድን ውስጥ ግለሰቦች ወይም ንዑሳን ቡድኖች ያላቸው ሚና በተለያዩ መንገዶች ሊገለፁ ይችላሉ። በተተኳሪ ማህበረሰብ የሴቶች ሚና የሚገለጡ የቃል ግጥሞች ይዘትና ጭብጦች ስንመለከት ከተፈጥሮ፣ ከግብርና ከባልትና ስራ፣ ከሀቀኝነት፣ ከሃላፊነት፣ ከንፁህነትና ሰው ወዳድ እንዲሁም ከጦርነት መሰል ጉዳዮች ጋር በማዛመድ ሚና እንዳላቸው ተወስዶ ቃል ግጥሞችን ይደረድራሉ። በዚህ ጥናት ከተፈጥሮ ወይም ከእንስታዊነት አንፃር እና ከማህበራዊ ተግባራት አንፃር የሚገለጡ የሴቶች ሚናዎችን ተተንትነው ቀርበዋል።

## 4.1.1. ከተፈጥሮ ወይም ከእንስታዊነት አንፃር ሚገለጡ የሴቶች ሚና

የሰው ልጅ ከሚያስጨንቀው ቁሳዊና ህሊናዊ ጉዳይ በመነሳት ከሃይማኖቱ ጎን በመቆም ሌሎች ስነ ቃላዊ ፈጠራዎችንና ክዎናዎችን መሰረት በማድረግ ለአእምሮው ምላሽ ይሰጣል። እነዚህ ስነ ቃላዊ ፈጠራዎችና ክዋኔዎች በመነገር፣ መተረትና በመዜም ሊቀርቡ ይችላሉ። ቃል ግጥሞችም ስለ ሴትና ወንድ ተፈጥሯዊ ሁኔታ(ፆታዊ ሚና)፣ በቃል በማዜም ማህበራዊና ተግባራዊ ሚናቸውን መግለጥ ያስችላሉ። እነዚህ ቃል ግጥሞች በተተኳሪ ማህበረሰብ ሴትነትን ከሃይማኖት አስተምሮት መሰረት ያደረጉ ፅንስ ሃሳቦችን ማጣቀሻ ያደርጋሉ። ይህን በተመለከተ መርጌታ ተስፋ አለሙ ሲገልፁ÷ «እግዚሐብሄር አምላክ አዳምን ከብቸኝነቱ ይወጣ ዘንድ ሄዋንን ፈጠረለት። በመፈጠሯም የሰው ልጅ ዘር ሊበዛ፣ ሊባዛና ምድርን ሊሞላ ችሏል»። በመሆኑም ከብቸኝነት ወይም ከግለሰብ ህይወት ይልቅ ቡድናዊ ሁነቶች እንዲፈጠር ሴት የቀደመና ተፈጥሯዊ ሚና እንዳላት መረዳት ይቻላል። ሴት በመፈጠሯ እናት፣ እህት፣ ሚስት፣ አክስትና አያት ትሆናለች። ይህም በተፈጥሮ ጉዳይ ሴት እንደ ወንድ ሁሉ ፆታዊ ሚና እንዳላት የሚገልፅ ሃሳብ ነው።

እንስታዊነት ቀደምት ከሰው ልጅ አፈጣጠርና አመጣጥ ጋር የተቆራኙ ምላሾችንና መላምቶችን የሚገለፅበት ጉዳይ ቢሆንም እነዚህን ከተፈጥሮ የተወሰዱ ፅንስ ሃሳቦችን በመያዝ ማህበራዊ ድልድሎችና ተግባራቶች ሲከዎኑ ይታያሉ። በተተኳሪ

ማህበረሰብም ሴትነትን ከስራ ሃላፊነት፣ ከመረዳዳት፣ ቡድን ከመመስረትና ከወዳጅነት የሚመነጩ እሳቤዎችንና ድርጊቶችን በእናትነት፣ እህትነት፣ ሚስትነት፣ አያትነት፣ አክስትና ጓድኝነት የተደለደሉ ሁነቶችን በቃል ግጥሞቻቸው ያወሳሉ፡፡ አቶ ነጋሽ ቢምረው÷

እጣቷን አትቁረጡት ይኑር እንዳገዳ

ሸኝታበታለች ብዙ አያሌ እንግዳ፤

«መልካም ሴት ለባሏ፣ ለወንድሟ፣ ለእህቷ፣ ለአክስቷና ለጓድኛዋ አትሰለችም፡፡ ይህን ደግነቷን ለመግለፅ ሲባል ብትሞትም እንኳን እጇን ወይም እጣቷን አትቅበሩት፤ እሷ ብዙ እንግዳ አስተናግዳለች ለማለት ነው»፤ ይላል፡፡

የሚዜሙ ቃል ግጥሞች ቡድኖች ምቹ የጋራ ህይወት እንዲኖራቸውና ቀጣይነት እንዲፈጠር ካላቸው ምኞት አንፃር ማህበራዊ መስተጋብሮችን ይከውናሉ፡፡

## 4.1.2. ከስራ ወይም ማህበራዊ ተግባራት አንፃር የሚገለጡ የሴቶች ሚና

ስራ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በመንፈስም ሆነ በአካል እንቅስቃሴ የተፈቀዱ ማህበራዊ ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ የሚከዎን ሲሆን ሴት ከተሰጣት ተፈጥሯዊ ገፅታ አንፃር የራሷ የስራ ድርሻና ፆታዊ ሚና አላት፡፡ ፆታዊ ሚና የማህበረሰብ አባላት ለቡድናቸው ህልውና መጠበቅ ሲሉ የሚወጡትና የሚከውኑት ሃላፊነትና ተግባር ነው፡፡ ሚናውም በዕድሜ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በጾታ ወ.ዘ.ተ. የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ ፆታዊ ሚናን አስመልክቶ Barni & et al (2017, 10) Smith, (1983) በመጥቀስ እንደሚከተለው ይገልፁታል፦ ቤተሰብ ልጆች በህይወታቸው ውስጥ ለሚኖራቸው የግንኙነት ብቃት ብቻ የሚያስፈልጓቸው አይደለም፡፡ ይልቁንም የመጀመሪያ የባህል እሴቶች ማስተላለፊያ አውድ ጭምር ናቸው እንጂ፤ አባቶች እና እናቶች ለልጆቻቸው እሴትን በማሳወቅ እና በማስተላለፍ በኩል እንደ ማህበረሰቡ የመጀመሪያ ተወካዮች በመሆን በባህሉ ውስጥ ትልቅ ሚናን ይጫወታሉ፤ በማለት ያስረዳል፡፡

ይህ ማለት የሰው ልጅ ሁሉ ማንኛውንም ነገር ከቀደሙ ቤተሰቦቹ የሚማር፣ የሚቀበል ትውልዳዊ ቅብብሎሽ ያለው እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም

ማህበራዊ ደረጃን፣ ፆታን፣ እድሜንና ሌሎች ሁኔቶችን መሰረት በማድረግ የተለያየ ሃላፊነትና ሚና ይሰጣቸዋል፡፡ በተተኳሪ ማህበረሰብም ፆታን መሰረት በማድረግ ለሴትነት ማደላደያ ሚና ያላቸውን ግጥሞች የተለያዩ አውዶችን በመጠቀም በቃል ግጥሞች ሲቀኙ፣ተግባሮችን ሲከውኑ ይታያሉ፡፡ ይህ ተግባር ደግሞ ከግለሰብ ግለሰብ ከቡድን ቡድን ቃላዊ በሆነ መልኩ ይከዎናሉ፡፡ ከሚከዎኑ ስራዎች መካከል የልጅ አስተዳደግና የፆታ ሚና ቀረፃ፣ ምግብና መጠጥ ዝግጅት እንዲሁም ሌሎች የቤተሰብ ሃላፊነትን የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የልጅ አስተዳደግና የፆታ ሚና ቀረፃን በተመለከተ ወ/ሮ አስረበብ ምትኩ ስትገልፅ÷ ሴቶች እናት ሲሆኑ ከመወለዳቸው በፊት ማርገዝና በእርግዝና ወቅት አንዳንድ ሃላፊነቶችን መዎጣት፣ በዚህም ጊዜ አንዳንድ ቤተሰቦች ለእርጉዟ ሴት የስራ ድካምን በማየት ሴት ልጅ እንዲወለድላቸው ይፈልጋሉ፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት

የሚያነሱት ወንድ ልጅ ለቤተሰቡ ጋሻና መከታ ቢሆንም በቤት ውስጥ ለሚከዎኑ ስራዎች ደግሞ ወንድ ልጅ የቀን ጅብ ነው፤ እንደ ሴት ልጅ ቤተሰቡን አይንከባከብም፤ ለትዳር ሲደርስም ጥሎሽ ያስወጣል፤ በሚል ሴት ልጅ እንድትወለድላቸው የሚፈልጉ ወላጆች አሉ፡

በዚህ ሁኔታ እናቶች ልጅ የማሳደግና የጾታ ቀረፃ ልማድ የሚጀምረው ልጆች ሲወለዱ ጀምሮ ተፈጠሯዊ ወይም ፆታዊ ሚና በማስከተል እንደሆነ መረዳት ያስችላል፡፡ ፆታ ተፈጥሮ ቢሆንም ቡድኖች እንደ አካባቢያቸውና ባህላቸው አኳያ ፆታዊ የስራ ድርሻና ሚናዎችን ይሰጣሉ፡፡ በመሆኑም እናት ልጅን አርግዛ መውለድና ተከባክባ ማሳደግ ትልቁ ስራ ሃላፊነቷ ነው፡፡ ሃላፊቷንም ልጇቿን በስርዓት ማሳደግና እንደ ፆታቸው የወደፊት ህይወታቸውን የመቅረፅ ሚና እንዳላት ማስተዋል ችያለሁ፡፡ ብርቱካን ቴወድሮስ ÷ «ሴት እናት ስትሆን እምጦ ከመውለድ ጅምሮ ብዙ ስራዎችን ታደርጋለች፡፡ ሴት መሬት ናት ይባላል፡፡ ቻይና ጠንካራ ብትሆን ነው፡፡ ሰውን ያህል ነገር የምትሸክም፤ የተወለዱ ልጆችን እንደ ማህበረሰቡ ልማድ ፆታቸውን አይታ ሴት እንደ ሴትነቷ ወይም ወንድን ደግሞ እንደ አባቱ እንዲሆን ለፍታ፣ ደክማ ታሳድጋለች፡፡ አንዳንዴም በማህበሩ፣ በልቅሶው፣ በሰርጉና በሌሎች አጋጣሚዎች»፤

እናታለምዬ ውለታሽ ብዙነው፣

ስንቱን ተናግሬ እጨርሰዋለው፣እያል እናወድሳታለን፤ በማለት ነግራኛለች (ቃለ መጠይቅ፣ሃምሌ15/11/14 ዓ/ም)፡፡

ተተኳሪ ማህበረሰብ ሴት እናት በመሆኗ ልጅን ለመውለድና በፆታ ቀረፃ ስራ ከፍተኛ ሃላፊነት የምትወስድ፣ ጠንካራ የህይወት መሰረት የሆነች፤ ህፃናትም በእናታቸው የቀረፃ ስልት ታግዘው የሚዘልቁ እንደሆነ መረዳት ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ብርቱካን ቴወድሮስ ስገልፅ÷

እናትስ አትሙት ትኑር አጎብሳ

ተባይ ትገላለች በጨለማ ዳሳ፤

«እናት ሚናዋና ደግነቷ ቀላል አይደለም፡፡ እንኳን በብርሃን በጨለማ ከመጥፎ ነገር ልጆቿን ታወጣለች፣ ትከላከላለች፡፡ እናት ከልጆቿ በፊት መስዋዕት መሆን የምትችል እንደሆነች የሚያሳይ ነው»፤ትላለች (ቃለ መጠይቅ፣ ሃምሌ15/11/14 ዓ/ም) ፡፡ ከዚህም አንፃር ሴት ልጅ እናት በመሆኗ ለልጅ እንክብካቤዋ፣ አስተዋፆኦዋ ብዙ እንደሆነ የሚገልፅና በአይኗ አይታ ከምትከዉናቸው ተግባራት በበለጠ በጨለማም ከተባይ (ነፍሳት) ን ትገላለች የሚል ትርጓሜ ያለው ነው፡፡ እነ ፈትለወርቅ ውሌ ስለእናት ሚና ሲገልፁ÷

ሚስቴ ትፍጨውና እናቴ ትጋግረው

ይህን በላ ብላ የማትገመግመው፤

«እናት ሲፈጥራት ከሁሉም የምትበልጥ ናት፤ ስስት፣ ንፉግነት የሌላት ናት፡፡ ሚስት፣ እህት፣ አክስትና ሌላ ዘመድ ብትሆንም እንደ እናት አትሆንም፡፡ አንጀቷ ልውስና ሩህሩህ ናት፡፡ ልጇ በላ የማትል ደግ ናት የሚል እንደሆነ»፤ ያስረዳሉ (ሃምሌ 15/11/14 ዓ/ም) ፡፡

ሴት እህት፣ ሚስት፣ አክስትና ሌሎች ማህበራዊ ደረጃዎችን ሚሰጣትና የምትገኝ ቢሆንም የእናትነት ሚናዋ ደግሞ ወደር እንደሌለው የሚገልፅ ግጥም ነው፡፡ ሴት እናት ከመሆኗ ባለፈ እህት ስትሆን ደግሞ እነ ፈትለወርቅ ውሌ ትነግረኛለች÷«ሴት

ልጅ ጌጥ ናት። ለቤት አያያዝ ድምቀት፣ ሙቀትና ደስታ ሰጭ ናት።እናት ባትኖር ለወንዶች እናት፣ ተተኪ የምትሆን ለእናቷ ድጋፍና ባላ በመሆን ታገለግላለች»፤ ይላሉ( ሃምሌ15/11/14 ዓ/ም)።

በዚህም ያታና ሃላፊነት ሲባል በእድሜ፣ በማህበራዊ ደረጃና ከቡድኑ የተሳትፎ ሁኔታና ሚና አንፃር የሚሰጥና ቀብብሎሽ ያለው ጉዳይ ነው። እናት ከቀደመ ቤተሰቧቿ ያገኘችውን ልምድና ስልት በመጠቀም ሴት ልጇን ትቀርፃለች። ልጅቷም ከእናቷ የተማረችውን በቤት ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች ቤተሰቦች በማገልገልና በመተግበር የምትዘልቅ ይሆናል። ሴት እህት ከእናቷ ከወሰደች እና ከማህበረሰቡ ልማድ መሰረት አንፃር ምግብና መጠጥ በማዘጋጀት፣ ልብስ በማጠብና ሌሎች ድጋፎችን በመስጠት ለወንድሞቿ እናታዊ ተግባር በመስራት ክፍተቶችን ትሞላለች። መልካም እህት ለወንድሞቿና ቤተሰቦቿ ከእናት ያላነሰ ተግባርን እንደምትዎጣ ማወቅ ችያለሁ። ከእነ ብርቱካን ቴወድሮስ ቤት÷

ልጅቱስ ድግ ናት ልውስ ነው አንጀቷ

መመኪያ ሁናለች ወጥታለች በእናቷ (ምልከታ፣ሰኔ27/10/14 ዓ/ም)

የሚሉ ስንኞችን በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች በማዜም የስራ ሃላፊነቷና ለቤተሰቦቿ ያላትን ሚና ይገልፁበታል። ስራና ቤተሰባዊ፣ ማህበራዊ ሃላፊነቶች ቡድኖች በተገኙ ማህበራዊና ባህላዊ አጋጣሚዎች ሴት በእህትነቷ ደረጃ የተገበረችውን የሴትነት ሚና በቃል ግጥም ይቀኛሉ።

ተተኳሪ ማህበረሰብ እንደ ሌሎች አካባቢዎች ሁሉ ሴትን እናት፣ እህት የሚቀድሙ ማህበራዊ ወይም ባህላዊ ቅርፃች ሲሆኑ ሚስት፣ አያት፣ አክስትና ጓደኛ ደግሞ ቀጣይነት ያላቸው መዋቅሮች ናቸው። በዚህም ሴት ሚስት ስትሆን የሚኖራት ሚናን በተመለከተ አቶ ደረጀ ወርቁ÷ «አዳም ብቻውን እንዳይሆን ከግራ ጎኑ ሄዋን እንደተፈጠረችለት ሁሉ እኛም ወንዶች ሚስት ካላገባን መኖር አንችልም። ሚስት ለባሏ ገመናውን ሸክፋ፣ ስራ ስርቶ እንዲመለስ ምክሯን ለግሳ፣ ቤታቸውን እንዲደምቅ በአቅም ሰርታ፣ ለብቸኝነታቸው ልጅ በመውለድ ሚናዋን የምትጫዎት ናት»፤

ሽጋ ሚስት ያለው ሰው ጥሩ ሚስት ያገባ

ለባሏ አሊንታናት ለልጆቿ ካባ፤ በማለት ይልፃል (ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ27/10/14 ዓ/ም)፡፡

ይህ ማለት ሴት ሚስት በመሆኗ ለባሏ ወይም ለትዳሯ፣ ለልጆቿ ቁልፍ ሚና የምትጫዎት እንደሆነች ማወቅ ይቻላል፡፡ «ሚስት ለባሏ ዘውድ ናት» እንደሚባለው ሁሉ ሴት ከቤት አያያዝ ባሻገር ባሏ ከሌሎች ቡድኖች ጋር መልካም ግንኙነቶች እንዲፈጠር፣ የበሰለ አእምሮ እንዲኖረው ሃላፊነት እንዲሰማው ማድረግ የምትችል ናት፤ ብሎ ማህበረሰቡ የሚያምን መሆኑን ለማየት ይቻላል፡፡

ሌሎች የማህበረሰብ አደረጃጀቶን ስንመለከት ሴት ከእናት፣ ከእህትና ሚስት አልፋ አያት ትሆናለች፡፡ ይህ አደረጃጀት ደግሞ የዘር ሀረግን መሰረት በማድረግ የሚመጣ ሲሆን በቡድኑ ውስጥ ልጅ በመውለድና ዘርን ማስቀጠል ተፈጥሯዊ ሂደት ቢሆንም ሴት እናት ከሆነች ማግስት ለልጇ ባል ወይም ሚስት በማጋባት ለሚወለድ ልጅ አያት የሚለውን መዋቅር ትይዛለች፡፡ በዚህም ለቤተሰቦቿና ለልጅ ልጇ የእናትነትን ሚና በድጋሚ ትዎጣለች፡፡ ወ/ሮ ትብለጥ ይርዳው÷ ስትገልፅ «ከእናት፣ ከእህትና ከሚስት የሚጎሉትን በመሙላት፣ በማብላት፣ በማጠጣትና ሃብቷን በማውረስ ልጆች ሌላ አማራጭ እንዲኖራቸው፤ በነፃነት እንዲያድጉና ተስፋ እንዲኖራቸው አያት ሚና አላት»፤ ትላለች (ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 23/10/14 ዓ/ም)፡፡

ይህ ማለት ሴት ልጅ በማህበራዊ አደረጃጀት አያት በመሆን ለሚወለዱ ልጆች ሰፊ ማህበራዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው ከወላጅ እናት ያለን ፍቅርና ደግነት ለልጅ ልጅ በመስጠት ማህበራዊ ትስስሮች እንዲቀጥሉ ሚናዋን ትወጣለች፡፡

ይህ የቡድን አደረጃጀት እየሰፋ በጊዜ ሂደት የሚዘልቅ ሲሆን ሴት አክስት በመሆን ለእህቷና ለወንድሟ ልጆች ቤተሰባዊ ድጋፏን ትሰጣለች፡፡ ይህም ሲባል አክስት በቤተሰብ ትስስር የሚከሰቱን ማንኛውም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ልማዳዊ ድጋፏችን ታደርጋለች፡፡ ወጣት አስቴር እናናው÷ «ሰው ብቸኝነትቱን የሚሞላበት ሲወልድ ሲዋለድ ነው፡፡ አክስትም የእህቷንና የወንድሟን ልጆች እንደ ልጆቿ ትንከባከባለች»፤ትላለች (ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 23/10/14 ዓ/ም) ፡፡

ሴት አክስት ስትሆን ዝምድናዋን፣ ቤተሰባዊነቷን በማስላት የጋራ ህይወትን ለማስቀጠል ሚናዋን ትወጣለች፡፡ ከቤተሰባዊነት ባለፈ በተተኳሪ ማህበረሰብ እንደሌሎች አካባቢዎች ሁሉ ሴት ጓድኛ በመሆን ማህበረ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ መደጋገፍና መረዳዳት የሚያሳዩ ሁነቶች አሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ሴት ልጅ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖራትን ሚና ሰፋ የሚያደርግ እና አስተዋፆኦ የሚገልፅ ነው፡ ፡ ገለፃው የሚቀጥለውና የሚመሰረተው ቃል ግጥሞችን በማዜም በመቀኘትና በመደርደር ይሆናል፡፡ አስለቃሽ አስራት ዘውዱ እንዲህ ያዜማል÷

እህት ያለውማ አክስት ያለውማ

ቢሞት አያስለቅስ ቢያጣ አያሳዝን

ሁልጊዜ ሙሉ ነው ድርብ ባለሽማ፤ እያልን

በደስታ፣ በሃዘን ቦታዎች መልካምነቷን፣ በመኖሯ ለሌላው ሰው እናሳውቃለን፤ (ቃለ መጠይቅ ሃምሌ፣ 5/11/14 ዓ/ም) ይለኛል፡፡ ይህም ማለት የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ስርዓቶችን ተከትሎ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከውናቸው ልማዳዊ እሳቤዎችና ድርጊቶች በማህበራዊ፣ ተግባራዊ ሁነቶች የተሻለ የርዕስ በርዕስ ግንኙነቶችና መስተጋብሮች እንዲኖሩ ያደርጋሉ፡፡ ከልማዳዊ ድርጊቶች እና እሳቤዎች ውስጥ ዝምድናን መቅረፅ፣ ማብጀቱ እንደሆነ የሚያሳዩ ሁነቶች አሉ፡፡ እነዚህ ዝምድናዎችና ስርዓቶች ደግሞ ማን፣ ምንና እንዴት የሚሉትን ለይቶ ለማወቅ ያስችላሉ፡፡ በተተኳሪ ማህበረሰብም አክስት የሆነች ሴት ከተመዘዘችበት የዘር ሃረግ አኳያ የወንድሟንና የእህቷን ልጆች በመከባከባ ሚና እንዳላት በቃል ግጥሙ መረዳት ችያለሁ፡፡

ሴት ጓድኛ ስትሆን ደግሞ ከቤተሰባዊነት ባለፈ ከሌሎች የአካባቢው ነዋሪዎች፣ በስራ ባልደረባነት፣ በማህበራዊ አጋጣሚ በሚመሰረቱ ተቋሞት፣ በአበልጅነትና ሌሎች የጓድኝነት መመስረቻ መንገዶች በሚመሰረት ጓድኝነት የመደጋገፍና የመረዳዳት ሚና እንደምትወጣ ማስተዋል ችያለሁ፡፡ መ/ር ትግስት አዝመራው እንዲህ ትላለች÷ «ጓድኝነት በሴትነት ደረጃ እንደተመሰረተበት ምክንያትና አጋጣሚ ፆታዊ ወይም ተፈጥሯዊ ገመናዎችን መሸፍ፣ሚስጢር ብሎ መያዝና መደጋጋፍ የተለመደ ነው፡፡ በሌሎች ማህበራዊ ህይወቶች መረዳዳትና መመካከር ምቹ የህይወት ዘመን ለማሳለፍ

አስተዋፆኦ ትልቅ የሚባል ነው፡፡ ይህ ጥሩ ጓድኝነት ያየ ሰርግ፣ ክርስትና፣ ማህበርና ልቅሶ ላይ ይቀር፣< ሚስጢሬ ጓዴ >ይባላል»፤ በማለት ታስረዳለች(ቃለ መጠይቅ፣ ሃምሌ 20/11/14 ዓ/ም)፡፡

በተተኳሪ ማህበረሰብ ሴት በጓድኝነት ሚና ቡድኑ መሰረት እንዳደረገው ወይም ሴቶች እንደመሰረቱት ዓላማ ከንዑስ ቡድን እስከ ሌሎች ማህበራዊ ተቋማቶች ድረስ የጋራ ህይወትን በመመስረትና ምቹ የህይወት ዘመን ለማሳለፍ የሚመሰርቱት ሲሆን ከግለሰብ ይልቅ ቡድናዊ ሁነቶች እንዲቀጥሉ ሚና እንዳላት መረዳት ይቻላል፡፡ ሴት ልጅ አይት፣ ምራት እና አማት የሚሉ ማህበራዊ ደረጃዎችንም ታገኛለች፡፡ በተተኳሪ ማህረሰብ ሴት በማህበረሰቡ ከምትገለጥበት ማህበራዊና ተግባራዊ መዋቅራዊ ሚናዎች መካከል አይት፣ ምራትና አማት ይጠቀሳሉ፡፡ አይት፣ ምራትና አማት ሲባል ከቤተሰብ መመስረቻዎች ውስጥ ጋብቻ ነው፤ ይህን ጋብቻ መሰረት በማድረግ አይት፣ ምራትና አማት የሚፈጠሩ ልማዳዊ ቅርፆች ናቸው፡፡ ይህን በተመለከተ አስረበብ ትኩ ስትነግረኝ÷ «ሚስት ለባል እህት አይት ስትሆን ለባል ወንድም ደግሞ ዋርሳ ትሆናለች፤ በሰርግ ስርዓት

የእኔስ አይቴ ውብ ናት

የእንጀራ ሞሰብ አላት፣

እየተባለ ትወደሳለች»፤ ትላለች(ቃለ መጠይቅ፣ ሃምሌ20/11/14 ዓ/ም)፡፡ አዲስ ስለምታገባ ሚስትም መልካምነቷን፣ ቁንጅናዋንና ወደፊት ስለምትሰራቸው ተግባራት በማህበረሰቡ የቃል ግጥም ቅኝት ይነገራታል፣ ይዜምላታል፡፡ በዚህም ሴት ስትሞሽር ለምታገባው ባል ሚስት ባሻገር ለእህቱ አይትና ለወንድሙ ዋርሳ በመባል ዝምድና ቤተሰባዊነት ትመሰርታለች፡፡ በተጨማሪም ደግሞ ለሚጋቡ ሁለት ጥንዶች ወይም ሴትና ወንድ ሴት አማት በመሆን ማህበራዊ ሚናዋን ትወጣለች፡፡ የሰው ልጅ ከግለሰባዊነት ይልቅ ቡድናዊ ህይወቱን ያስቀድማል፡፡ በመሆኑም በጋብቻ ስርዓት መሰረት እንግዳ ሁነው ለሚመጡ ጥንዶች እንደ እናት በመሆን ሃሳብ ጭንቀታቸውን በማቃልና በማደላደል ሚና ትወጣለች፡፡ ወ/ሮ ሰናይት ደግሰው ስትነግረኝ÷ «ሴቷን ከባሏ እንድትለምድ የልጇን ግብርና ፀባይ በመንገር አዲስ የሚመስሉ ያታዊ ሁነቶችን በማስተማር እንዲሁም በተማረችው ትምህርት ደግሞ ቤት እንድትሰራ ትነግራታለች፡፡ ወንዱን ደግሞ ፍራት እንዲለቀው ተግባብቶ እና

ተላምዶ እንዲኖር ምክርና ድጋፋ በማድረግ የእናት አይነት ሚና ትሰራለች»፤ ትላለች(*ቃለ መጠይቅ፣ ሃምሌ*20/11/14 *ዓ/ም*)።

ሴት በተተኳሪ ማህበረሰብ ዘንድ በተለያዩ ማህበራዊ አደረጃጀቶች በመደልደል እንደ ቡድኑ ልማድ ከሌሎች ቡድኖች ጋር በመቀላቀል ከወላጆቿ ባለፈ ሌላ ቤተሰብ በመመስረት ማህበራዊ መዋቅሮች እንዲሰፉ አስተዋፆኦ እንደላት በጥናት ሂደቱ ማወቅ ችያለሁ።

## 4.2. የሴትነት ሚና ማደላደያ ቃል ግጥሞች

የቃል ግጥሞችን አይነት ለመመደብ አስቸጋሪ ቢሆንም በቡድን ይሁን በተናጠል፣ በተማሩ ይሁን ባልተማሩ፣ በቃልም ሆነ በፁሁፍ ለሰው ልጅ ለአእምሮ ቅርብ በሆነ መንገድ የሚቀርብ ጥበብ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚነሳው በቃል ወይም በሰዎች አእምሮና አንደበት ተሰንቀው የሚቀርቡ ቃል ግጥሞች የአንድን ማህበረሰብ የአኗኗር መልክ፣ የሩቅና የቅርብ አስተሳሰቦች፣ ፍላጎትትንና ጥላቻ ለማስረፅ ስነ ውበታዊ በሆነ መልኩ የሚቀነባበር የጥበብ ስልት ነው። እነዚህ ስነ ውበታዊ ጉዳዮች ሴቶችን በሚኖሩበት ማህበረሰብ ዘንድ የመደላደያ መንገድ እንዲሆንላቸውና ማቅለያ ዘዴ ነው። ሴቶችን ሊያደላድሉና ክፍታ ሊሰጡ የሚችሉ የግጥም አይነቶችና ይዘታቸው ብዙ የሚባሉ ናቸው። ከነዚህም መካከል በተተኳሪ ማህበረሰብ ጥንካሬን ስራና ተግባራትን፣ መልካምነት የሚያላብሱ እና ቤተሰባዊነነትን የሚገልጡ ቃል ግጥሞች ብሎ በመለየት ከዚህ ቀጥለው ቀርበዋል።

### 4.2.1. ጥንካሬና ብርታትን የሚገልፁ

ሴትነት ወይም እንስታዊነት ስነ ህይወታዊ ጉዳይ ሲሆን ተተኳሪ ማህበረሰብ እንደ ሌሎች አካባቢ ቡድኖች ሁሉ ያላቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁነቶች ተሳትፎና ብርታት በቃል ግጥሞች ያንፀባርቃሉ። ይህን በተመለከተ አቶ ከበረ መላክ ሲደረድር÷ ሳጠፋ ገስፃ እንዳልኮራ መክራ፡

በእርታ እያለችኝ ሁሌም እንዳልፈራ፡

አይዞህ አልከፋም ሴት ያሳደገኝ ነኝ፤

ስድብ ከመሰለህ ደጋግመህ ስደበኝ፡

አልቀየምህም በስሚ ስትጠራኝ፡

እውነቱን ልንገርህ አዎ የሴት ልጅ ነኝ፤

እንዲህ የምንለው ሚስት ከሚስትነት አልፋ ለባሏ እንደ እናት፣ እህትና ጓድኛ ሁና ስናጠፋ መምከር፣ ወደፊት ለምንሰራው ማቀድና እንዳንዘናጋ፣ ሚስጢርን መያዝ ጠንካራና ብልህ እንድሆን፤ ቤት እንድንይዝ አስተዋፆኦ አላት፤ይላል እንዲህ እያለ ሲቀኝ የስንኞቹን ይዘትና ፋይዳ እንሚከተለው ያስረዳል፡፡ በአካባቢያችን የወንድ ጠንካራነት የሴትን ደግሞ ደካማነት የሚያጎሉ ልማዳዊ ድርጊቶች አሉ፡፡ እነሱም÷ ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ፣ ሴት ወደ ማጀት ወንድ ወደ ችሎት እየተባላ ይነገራል፡፡ ቢሆንም በቤት አያያዝ፣ በልጅ አስተዳደግ፣ከጥንካሬ አኳያየሚገጠሙ ስንኞች ሴቷ ወንዱን መክራ፣ ለፅኑ አላማ አርቃና አቃንታ፣ ተስፋ መቁረጥን አስቁማ አበረታች ሃይል በመሆን ያሳየችውን ሚና የሚገልፅ ነው፤ ይላል (ቃለ መጠይቅ፣ ሃምሌ25/11/14 ዓ/ም) ፡፡

ከዚህም አንፃር የቃል ግጥሙ ስንኞች ደግሞ የሴትነትን ጥረትና ትጋት ውጤት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ሴት ልጅ ለወንዱ ባደረገችው ጠንካራ ስራ ወንዱ ለምንጊዜውም ኩራት እንዲሰማው እና ሴት የሚለውን ማህበራዊ ድልድልን ከፍ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም አቶ ሞላ ጥጋቡ ሴት ልጅ የትዳር አጋር ስትሆን ያላትን ጥንካሬ እንዲህ ያስረዳል÷

የቤት አያያዝን ለወንድ አስተምራ

የወለደችውንም ልጇንም ጨምራ

ይሰምራል ትዳሩ በትብብር ስራ

ወንዱንም ሴቱንም በደንብ ተቆጣጥራ፣

«ይህን ግጥም የምንለው አዲስ ቤት ስትሰራ፣ በቤቷ ውስጥ ማህበር፣ ክርስትና፣ ሌላ አመት ባዓል ካደረገች በባሏ ፊት ክብርና ሞገስ እየተሰማት ይዘፈናል፡፡ ይህ ያየ ማህበርተኛ ወይም የተጠራ ሰው የእግሌ ሚስት አቤት ድግስ በማለት ደግሞ ሚስቱን ያስተምራል»፤ በማለት ይገልፃል፡፡

ሴት ልጅ ሚስት ስትሆን ባሏንም ይሁን ልጆቿን በጋራ መኖርን፣ መተሳሰብንና መጠንከርን በማስተማር መልካም የህይወት ዘመን እንዲኖር፣ እንዲፈጠር ሚናዎ ከፍ ያለ ነው። ይህም ማለት ያገባችውን ባሏን ብቻ ሳይሆን የወለደችውን ወንድ ልጅ በማረም እና ትምህርት በመስጠት የህይወት ቅብብሎሽ እንዲኖር ሚና እንዳላት መረዳት ይቻላል። እነ ወ/ሮ አየለች ደማሙ «ስለ እህት ጥንካሬ ስታወሳ ፥እንዲሁ በሰርግና በደስታ ቀን የምንለው ሲሆን አንዳንዴ ደግሞ በአካባቢያችን ግጭት፣ ሽምግልና ሲኖር ስለ ወንዱ ጀግንነት ስናወራ ብልህ ሴቶች እንዲህ ይላሉ»፤፥

ወንድ ልጅ ለጥቃት ይላል ያላወቀ

እህቱ አብልታው ነው ክንዱ የጠበቀ፣

ለወንድ ልጅ ጉልበቱና ልቡ ሴት ናት ማለት ነው፤ ይላሉ(ተ/የቡ/ው፣ ሃምሌ 12/11/ 14 ዓ/ም)።

ይህ ማለት ወንድ ልጅ ለሚተገብራቸው ጀብዶች ሁሉ ሴት እናቱ፣ እህቱ፣ ሚስቱና አክስቱ ወ.ዘ.ተ ጉልበቱ ናት። አንጀቱን አቃንታ አእምሮውን አድሳ ለውጤት እንደምታበቃው ያስረዳል። ሴት እናት ስትሆን ያላትን ብርታትና ጥንካሬ በተለያዩ አውዶች ይገለፃሉ። እናት ስትሞትም የነበራትን ሚና ለመግለፅ ሲባል ከሚገጠሙ ቃል ግጥሞች መካከል አስለቃሽ ሙሉጌታ አስማረ እንዲህ አጎራጉሮልኛል፥

ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን አርግዛ በሆዷ

ሶስት አመት አጥብታ አዝላ በመሄዷ

እናት እሩህሩህ ናት አይጨክንም ሆዷ፣

እናት ውለታዋ ብዙ በመሆኑ እንኳን በህይወት እያለች ስትሞት ትዝታዋ ሩህሩህነቷ ሲታውስ እንድናዝን ያደርገናል፤ ቤተ ዘመዱ ይህን ግጥም ሲሰማ ያዝናሉ፤ (ምልከታ፣ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 23/10/14 ዓ/ም) ።

ይህ ማለት ምን ያህል ወርና ጊዜ ለፍታ ስታሳድግ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ የማትል ብርቱና ጠንካራ መሆኗን ያሳያል። ከዚህም አንፃር ሴት የእናትነት ሚናዋ ከፍ ያለ እንደሆነ የሚያሳይ የስንኝ ቋጠሮ ነው። በተተኳሪ ማህበረሰብ ሴት በሚሰጣት

ማህበራዊ ደረጃ በቃል ግጥሞች አማካኝነት ከወቅትና ከሁኔታ ጋር በማዛመድ ይዜምላታል። አስረበብ መልኬ ሴት አማት፣ አያት ስትሆን ልጇን በዳረች ወቅት ስለ ባልትናዋ፣ ስራና ተግባሯ እንዲህ ይዘፈንላታል ÷

የሙሽሪት እናት ቁሚ ተመረቂ

የጠመቅሽው ጠላ ጠጅ ነው አረቂ፣

ይህ ዘፈን ቤተዘመድ በተጠመቀ ጠላ፣ በተዘጋጀ ምግብ ስደሰቱ እንዲህ እያልን እናወድሳለን፤ ትላለች (ቃለ መጠይቅ፣ ሃምሌ 25/10/14 ዓ/ም) ። ይህ ማለት ሴት አማትነቷ፣ እናትና አያት ስትሆን በሰራች ስራ በቃል ግጥም ትወደሳለች። ስለ ሴት ልጅ ሚና እና አስተዋፆኦ የሚዜሙቃል ግጥሞች እንደሚገቡበት አውድና ተግባር ትርጓሜያቸው ስፊ እንደሆነ ማወቅ ችያለሁ ሊቀ መኳስ አደራጀው ሲያዜም÷

እናት የሌለው ለእጅ ቀላል እንደ ጌሾ

ባይበላም በላነው ቢናገረም ዋሾ ፤

ሴት በማህበረሰቡ ዘንድ በሚሰጣት የስራ ሃለፊነት፣ ጥንካሬ፣ የቤተሰብ አመሰራረት፣ ለሌሎች አዕርያ ከመሆን አኳያ እና ሴት እናት ስትሆን ለልጇ የሚኖራት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው። በተጨማሪም አደራጀው ሲያዜም÷

ለእናቴ እናት ሆንኳት ቀረ ልጅነቴ

ብድሯን ልትመለስ ገብታለች ካንጀቴ፤

ሴት ለእናቷ ልጅ በሆነች ማግስት የእናትነት ሚና ትወጣለች። በልጅነት ያለፈን ነፃነት ልጅ በመውለድና የቤት ሃላፊነት በመያዝ የሚስተዋሉትን ሁለንተናዊ ጉዳዮች በማሰብ ተተኪ መሆኗን ያስረዳል፣ ይገልፃል (ምልከታ፣ ነሃሴ13/12/14 ዓ/ም ከነ አሰረበብ ምትኩ ቤት)።

### 4.2.2. መልካምነትን የሚያሳዩ ቃል ግጥሞች

ተተኳሪ ማህበረሰብ የሴትነት ማደላደያ ሚና ከሚያንፀባርቁባቸው ቃል ግጥሞች መካከል ከመልካምነት እንዲሁም ደግነታቸውን የሚያደላድሉ እንዳሉ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡ አቶ ሞገስ ደማሙ ሲያዜም÷

በማህፀኗ ውስጥ ገብቼ ተኝቼ

የጡቶቿን ወተት ጨምቄ ጠጥቼ

ልጄ ልጄ ስትል ፍቅሯ የተመቼ

ምን ብየ ልናገር እንግዲህ ስለ እናት

አንድ እድርጎ ፈጥሯታል መተኪያ የሌላት

እንዲህ የምንልበት ደግሞ የእናትን ደግነት በጥምቀት፣ በሰርግና ሌሎች ቦታዎች ክብረ ባዓል ሲኖር ዘፋኝ እንዲህ እያለ ያቀነቅናል፤ ሌሎች ደግሞ በእልልታና በጭብጨባ ይቀበሉታል፡፡ የእናት ውለታ በሁሉም የሚነሳ ስለሆነ ነው፤ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 22/09/14ዓ/ም)፡፡

ከላይ የቀረቡት ስንኞች የእናት ፍቅር ወደር የሌለው ስለ መሆኑ የሚያስረዱ ናቸው፡ ፡ እናት በማህፀኗ መሸከም ብቻ ሳይሆን ጡቷቿን ሳትሰስት ማጥባት የምትችል፣ በንፁህ ፍቅር አሰጣጧ ለልጇ ስትቆረቆር፣ ስትንከባከብ የሚያሳይ ቃል ግጥም ነው፡፡ ሴት ከእናት ባለፈ ደግሞ ሚስት ስትሆን ፍቅርና መተሳሰብን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች ስንመለከት፤ አስለቃሽ ሙሉጌታ አስማረ

የትዳሬ አጋር ናት ፍቅሯ የሚቀዳ

የእኔነቴ ፍቅር የትዳሬ ጓዳ፣

«እንዲህ የምንለውማ ባል ሚስቱን ሲያሞግስ በቤት በማህበሩ፣ በሰርግ በክርስትናው ይዘፍንላታል»፤ ይላል፡፡ ይህ ቃል ግጥም አንድ ባል ለሚስቱ የሚያዜመውና ምስጋና

የሚሰጥበት የትዳር አጋሩ ከምትሰጠው የፍቅር ስጦታና ከሚያገኘው ደስታ የሚመነጭ ነው፡፡ በተጨማሪም ሙሉጌታ አስማረ ሲያዜም

ገመና ሸሻጊ ሚስጢሬን ጠባቂ

ሚስት ለወንድ ልጅ ጥሩ ሃሳብ አፍላቂ

በተከፋ ጊዜ በምክር አራቂ

ሚስትናት ለትዳር ጠንቃቃና አዋቂ፣

«ውለታዋን ለወንድ ልጅ ማገር መሆኗን እንደነገርኩሽ በተለይ ቤተዘመድ በሚገኝበት የደስታ ቀን ስንበላ ስጠጣ ስንጫዎት ከደስታችን ብዛት እንወድሳታልን፡፡ እሷም ደስ እያላት ቤተዘመዱን ትከባከባለች፣ ታደስታለች»፤ ይለኛል (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት23/ 09/14 ዓ/ም)፡፡

ሴትነት ከሚገለፅበት መንገድ አንዱ በእህትነት ሚና ነው፡፡ በዚህም እህት መልካምነቷንና ደግነቷን የሚሳዩ ስንኞች ስደረደሩ ይታያሉ፡፡ ወ/ሮ ትብለጥ አንዳርጌ እንዲህ ታዜማለች፦

እስኪ በስማም ብዬ እህቴን ላንሳት

ምንም አትለይም ሁልጊዜም እንደ እናት

ከደረቷ ወተት ባንጠቀምባት

ክብር ይገባታል እህትም እንደ እናት፣

«ይህም ቤተዘመድ ሲሰበሰብ፣ አዝማሪ ቅዳ ሲል ስለ እህት መልካምነት ከእናት ያላነሰ ውለታ እንዳላት ትወደሳለች»፤ ትላለች፡፡ ከዚህም አንፃር ሴት እህት ስትሆን ለቤተሰቦቿና ወዳጇቿ የምትሰጠውን ፍቅር የሚያነፀባርቅ ስንኝ ነው፡፡ ለቤተሰቦቿ ያላትን ደግነትና ሚና የሚያስረዳ ነው፤ ትላለች (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 24/09/14/ዓ/ም) ፡፡

ሴትነት ተፈጥሯዊ ስርዓትን ተከትሎ የሚመጣ ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም በተተኳሪ ማህበረሰብ ሴቶች በእንስታዊነታቸው በማህበረሰቡ ያላቸው ያታዊ ሚና በቃል ግጥሞቻቸው እንዲህ ያወሳሉ፡፡ ከሚወሱና ሚናዋ ከሚገለጥባቸው መካከል አያት፣ ጓደኛ፣ አክስት፣ አይትና አማት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

መቀነቱን እማ ሁሉ ይታጠቃል

አክስት አለም፣ እህት አለም፣ እናት አለም ሆዴ ውሉ ባንች ይጠብቃል፣

ይህ ግጥም ሴት አክስት፣ እህት አንዳንዴም እናት በመሆኗ በቤተሰቦቿና በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሚኖራት ሚና ለመግልፅ የሚዜም ቃል ግጥም ነው፤ (ምልከታ፣ ሀምሌ 21/11/14 ዓ/ም አስፋው ግራር ሰፈር የሴቶች ወርሃዊ የማርያም ፅዋ ማህበር)፡፡ በተጨማሪም ወ/ሮ አለሚቱ ውዱ እንዲህ ታዜማለች÷

የቤቱማ ምሶሶ የቤቱማ ማገር

እንደሚስት የታለ ለቤትማ ክብር

ይህ ማለት ሴት ሚስት በመሆኗ በቤት ውስጥ ትልቅ ሃላፊነትና ሚና እንዳለት፣ ጥሩ ሚስት ለቤቷ ታታሪና ቅን አሳቢ በመሆን ባሏን በመቅረፅ መልካም ህይወት እንዲኖር ታደርጋለች፡፡ አቶ አስራት ዋለ በቤታቸው ሰኔ 23/10/14 ዓ/ም በፅዋ ማህበር ላይ ሲያዜም÷ የወንድ ልጅ ክብሩ የወንድ ልጅ ቤቱ

በጎጆ አያያዟ በልጣለች ሚስቲቱ፤

የምግብ፣ የመጠጥ ዝግጅቱን፣ ጥሩ መስተንግዶዋን ሲታይና ለሌሎች ምሳሌ የሚሆን ደግነት፣ ቅንነት የባሏን ሃሳብ የምትቀበል፣ ዘዴ የምትችል ስትሆን እንዲህ ይባልላታል፤ (ምልከታ፣ 23/10/14/ዓ/ም)፡፡

ይህ ማለት ለጎጆ ወይም በቤት ውስጥ ለጥሩ የስራ እንቅስቃሴና የልማታዊ አሰራር ለማበልፀግ ሴት ሚስት ሁና ባሏንና ልጆቿን ቀርፃ፤ ስርዓት ማስያዝ እንደምትችል የሚያስረዳ ቃል ግጥም ነው፡፡ በተተኳሪ ማህበረሰብ ሴት እህት ስትሆን የራሷ ያታዊ ሚና እንዳለት በቃላዊ ግጥሞች ሲዜሙ፣ ሲደረድሩ በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተሰበሰቡ መረጃዎች እንዲህ ቀርበዋል፤ አቶ ነጋሽ ቢምረው ሴት እህት ከእናት ያልተለየ ሚና እንዳላት በቤታቸው ተገኝቸ ስታሰብ፤

ከእናት አትለይም የእህትማ ነገር

ስራዋ እጅግ ነው ይነገር ለሃገር፣

ያው እንደሰማሽው በአካባቢያችን እህት ከእናት አትለይም፣ በሰርጓ፣ በድግሷ የተገኘ፣ የተደሰተ ደግነቷን ለወንድም ተቆርቋሪነቷን ለመግለጥ ለማስደሰት እዘፍናለን፤ በማለት ትግልጻለች (ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ ሃምሌ16/11/14 ዓ/ም)፡፡

ከዚህ አንፃር ሴት እህት ስትሆን ለቤተሰቿ ያላትን ደግነት፣ ክብርና ሩህሩነት ከእናት ያነሰ አለመሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ ወንድም እህቱ የምትሰጠውን ማህበራዊ ሚና የሚሳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቃል ግጥሞች ስለ ሴት ደግነቷንና መልካምነቷን በብዙ መንገድ መግለጥ ያስችላሉ፡፡ ሴት በቤት ውስጥ ባላት ተግባርና ማህበራዊ ግንኙነት፣ ለሌሎች ባላት ቅንነት ህፃናት በቡሄ፣ በአሸንዳና በአካባቢው ክብረ ባዓላት በቤቷ ሲገኙ እንዲህ ይላሉ÷

ከጎታ ላይ ሁና ታሽካካለች ዶሮ

የእኔማ……ድልድል ወይዘሮ፣

እያሉ እናትም፣ አያትም፣ እህትም፣ ጓድኛም፣ አክስትም ስትሆን ይገጠምላታል፤ (ምልታ፣ ነሃሴ 23/12/14 ዓ/ም)፡፡ ከዚህም አንፃር ቃል ግጥሞች በተለያየ አውድና ቅርፅ በመግባት የሴትን ልዩ ማህበራዊ ደረጃዎች ወይም ሚና በመግለጥ አስተዋፆኦ አላቸው፡፡ ሴት በምትቀመጥበት፣ በምትሳተፍበት የስራ ክፍፍል ወይም በቤት እመቤትነቷ እና ቡድኑ በሚከውናቸው ማህበረ ባህላዊ ክዋኔዎች ላይ በቃል ግጥሞች አማካኝነት ትገለጣለች፤ አቶ ነጋሽ ቢምረው «የሴት ወይዘሮ በቤቷ ጋግራ፣ ጠምቃና ሰርታ ስታበላ፣ ስታጠጣ በቡድኑ እንዲህ ትወደሳለች፤

የጠመቀች እንደው አስመስላ ቢራ

የጋገረች እንደው አስመስላ ሞራ

ወጥ የሰራች እንደው በሽታ የሚያበላ

ማን ይስተካከላል ቆንጂት ካንቺ ጋራ፣

«ይህ ሲባል እንግዲህ እናት፣ አክስት፣ ሚስት፣ እህት፣ ጓደኛ፣ አይትና አያት ልትሆን ትችላለች። በድግሱ ተሳታፊ የሆነ፣ ልጅ፣ አጎት፣ ባል፣ አባት ከባለቤቲቱ ያለውን ዝምድና መሰረት በማድረግ ከደስታው ብዛት ያወድሳል» (ቃለ መጠይቅ፣ ሃምሌ 15/11/14 ዓ/ም) ። ሙያዋና ችሎታዋን ለሌሎች ተሳታፊዎች እንዲገለጥ፣ እንዲተላለፍ በቃል ግጥሙ ይገልጣል። አይት፣ ምራት ስትሆንና ልጅ ወልዳ ክርስትና ስታስነሳ ደግሞ አቶ ሞገስ ደማሙ ቤት ሊቀ መኳስ አደራጀው ሲዘፍን÷

በጥቁር አንቀልባ ወንድ ልጅ አዝላለች

የሴቶቹ ቁንጮ እሷ ትሆናለች፣ (ምልከታ፣ ነሃሴ 22/12/14 ዓ/ም)

ሲል በመስክ ምልከታ ሳደርግ በመልካም አጋጣሚ ያገኘውት የክርስትና አውድ ላይ የተገኘ የአዝማሪ ቃል ግጥም ነው። ሴት ከልጅነት ህይወት ተሸጋግራ የእናትነት፣ የሚስትነት፣ የአይት፣ የምራትና ሌሎች ድልድሎችን እንደምትይዝና በምትቀረፅበት ደረጃም የራሷሚና እንዳላት ቃል ግጥሞች ተከትለው በማሳየት ያስረዳሉ። ተተኳሪ ማህበረሰብ ሴት በምትቀረፅበት ማህበራዊ ደረጃ ያላትን የመልካምነት፣ የደግነትና የስራ ሃላፊነት አኳያ ሚናዋን ለማሳየት በቡድኑ የተፈጠሩና ስወርድ ሲዋረድ በተቀበሏቸው ቃላዊ ግጥሞች ይገልጣሉ። የሚገለጡ የሴት ሚናዎች እና የሚዜሙት ቃል ግጥሞች እንደሁኔታው የሚቀያየሩና የሚደጋገፉ፣ ቀጣይነት ያላቸው እንደሆኑ በጥናቱ ሂደት ማወቅ ችያለሁ።

## 4.3. ቃል ግጥሞቹ ለተተኳሪ ማህበረሰብ የሚያስገኙት ፋይዳ

የቃል ግጥም ፋይዳ ሲባል የሚከዎኑት ቃል ግጥሞች ለስነ ቃሉ ባለቤቶች ያላቸውን ጠቀሜታ ይመለከታል። የተለያዩ የቃል ግጥም አይነቶች ለየራሳቸው የሆነ ጠቀሜታና ተግባር ይኖራቸዋል። የተለያየ ቅርፅ ያላቸው ቃል ግጥሞች ደግሞ ተመሳሳይ ፋይዳ ሊኖራቸው ይችላል። አስረበብ ምትኩ÷ "በደስታ ሆነ በሃዘን ወቅት የግጥም ችሎታና ድምፅ ያላቸው ግለሰቦች የሚከወነውን ስራ፣ ደስታ፣ሰርግ፣ ጥምቀትና መከራ ያደምቁበታል። ባለጉዳይም ደስታም ከሆነ ይደሰታል። ሃዘንም ከሆነ ስሜቱን ያሳይበታል" ትላልች(ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 23/10/14 ዓ/ም)። ተተኳሪ ማህበረሰብ ለሴትነት ሚና ማደላደያ የሚገልፁ ቃል ግጥሞችን ጊዜና ቦታ በመያዝ

ያዜማሉ፡፡ የሚዜሙ ቃል ግጥሞች የሴቶችን ጠንካራነት፣ መልካምነትና ማህበራዊ ሚናን የሚገልፁ ሲሆኑ ሌሎች የማህበረሰቡን የሴትነት ማህበራዊ ደረጃን፣ መዋቅር፣ የስራ ባህል፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ ልቦናዊ ማንነት የማሳየት ፋይዳ ያላቸውን የተለያዩ አውዶችን በመፍጠር የሚከዎኑ ናቸው፡፡ ሞገስ ደማሙ÷"ሸጋ ሴት በቤቷ ስጠምቅ፣ ስትጋግር እና እንግዳ ስትሸኝ ከኖረች ብትሞትም እንዳልሞተች የሚመስል ልቅሶ ይውልላታል"፡፡

ጎረ ዝም አትበሉ እናንተስ አልቅሱ

እናት አፈር በላት የትገኛል መልሱ፣

ያንሁሉ እንግዳ ያንሁሉ ዘመድ ሰርታ እንዳላበላች

እክሊት ምነካት በሯ የተዘጋ ሰው አላይም ብላ እረቃ ሄዳለች፣

"ያው በህይወት እያለች ደግና ጥሩ የነበረች ሴት ስትሞት መልከምነቷ፣ ድግነቷና ጥንካሬዋ ቢቀርም በግጥም ግን ሲለቀስላት እና ሲፎከርላት ይውላል"፤ (ቃለ መጠይቅ፣ ሃምሌ 13/11/14 ዓ/ም) ፡፡ ከዚህ አንፃር ማህበረሰቡ የሞተችን ሴት ስታደርጋቸው የነበሩን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ተሳትፎዎችን በልቅሶ የቃል ግጥም አይነቶች በመግለፅ ለከዋኙም ልባዊ ስሜት እንዲፈጠር ከፍተኛ አስተዋፆኦ እንዳላቸው መረዳት ያችላል፡፡

በዚህም ተተኳሪ ማህበረሰብ በሚከወኗቸው ቃል ግጥሞች ስነ ልቦናዊ፣ ተግባራዊና ማህበራዊ ፋይዳዎችን እንደሚያገኙበት በጥናት ሂደቱ ተደርሶበታል፡፡ በዚህም ቃል ግጥሞች ለተተኳሪ ማህበረሰብ የማስተማርና የመትከል ተግባር ሚና ይወጣሉ፡፡

### 4.3.1. ስነ ልቦናዊ ፋይዳ

ሰነ ልቦናን በተመለከተ Lipner, et al (2017, 2—3) ሲገልፁ ፦በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ቡድኖችን ስለ ነገሮች አይነት፣ሁኔታ እና ገጽታ በጋራ በመወያየት አእምሯዊ ዕደገት ማምጣት መቻል፣ ስነ ልቦናዊ እንዲሁም አእምሯዊ ህክምና መስጠት እንደሚቻል፤ ያስረዳሉ፡፡

ይህም ማለት ቡድኖች በሚፈጥሯቸው አውዶች ማለትም በክብረ ባዓላት፣ ሰርግ፣ ክርስትና እንዲሁም ፌስትባልና ከበራዎች ላይ የሴትነት ሚና ማደላደያ የሚገልፁ ቃል ግጥሞች በሚዜሙበት ወቅት ውስጣዊ ሀሴትን በመፍጠር፣ የርዕስ በርዕስ ግንኙነታቸውን በማጠናከር፣በመከባበርና በወዳደስ ስነ ልቦናዊ እርካታ እንደሚሰጣቸው ማወቅ ተችሏል፡፡ አቶ ስራት ዋለ ሲገልፅ÷

የገበያ ድንጋይ እና ልጅ ያልወለደ ሰው ሁለቱ አንድ ናቸው

ሲለዩ መቅረት ነው አስታዋሽ የላቸው፤

«ይህ እንግዲህ በአንድ ድግስ ወቅት የተገናኘ ሰው በተለይ ክርስትና ላይ መውለድ፣ መተካት አስደሳች መሆኑ የሚያሳይ ግጥም ነው፡፡ ቤተዘመድ በልቡ ይደሰታል፣ ያልወለደ ደግሞ ያስባል» (ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 21/10/14 ዓ/ም) በማለት ያስረዳል፡፡ ሴት ልጅ በሚኖራት ማህበራዊ ደረጃና በሚሰጣት ማህበራዊ ሚና አኳያ እና በምትተገብራቸው መልካም ስራዎች፣ ቤተሰባዊ መረዳዳት፣ ልጅን መውልድና የቀረፃ ሚና በሚዜሙ ቃል ግጥሞች የስነ ልቦና ፋይዳ እንደሚገኝበት በጥናቱ ተደርሶበታል፡ ቃል ግጥሞች በሃዘን ጊዜ የማህበረሰቡን ልቦና በመንካት ማልቀስ እንዲችሉ፣ የልቅሶው አውድ እንዲደምቅ ሚና አላቸው፡፡ አቶ ነጋሽ ቢምረው÷

ያ ቀሚስ የማነው ታጥቦ የተሰጣው

የእከሊት ይሆናል ባለቤቱን ያጣው፣

“ሲባል ቤተዘመድ ያለቅሳል፤ ይንሰፈሰፋል፡፡ ብዙ ጊዜ ዝም ብለን ብናለቅስ ላይገፋን ይችላል፡፡ አስለቃሽ ግን በግጥም ሲያለቅስ የውስጥ ስሜታችን ይዎጣል፣ እናለቅሳለን”፤ በማለት ይገልፃል (ቃለ መጠይቅ፣ ነሃሴ 17/12/14 ዓ/ም) ፡፡ በዚህም የሰው ልጆች መሰሎቻቸው ሲለያቸው እና ሲሞቱባቸው ማልቀስ ልማዳዊ ተግባር ሲሆን በዚህ ጊዜም ለሚከዎነው ጉዳይ እና ለከዋኝ አካላት ሙሉ ሴሜቶችን ለሰጡ የሚያስችሉ ቃል ግጥሞች ሚና እናዳላቸው መረዳት ያችላል፡፡ የክዋኔው መድመቅና የአባላት ሙሉ ስሜት ደግሞ ከስነ ልቦናዊ ጉዳይ የሚመነጩ እንደሆኑ መረዳት ያስችላል፡፡

### 4.3.2. ተግባራዊ ፋይዳ

ሰሎሞን (2007፣ 75) «ፎክ ቡድኑ የሚያገኘውን ወይም ሎሮች ለማህበረሰቡ ያላቸው አውዳዊ ትርጎሜ የሚያደርግና በተግባራዊ ንድፍ ሃሳብ የሚካተቱ ተረቶች፣ ሚቶች እምነቶች ወ.ዘ.ተ እንዲሁም ሎሮቹ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ስነ ልቦናዊ ወይም ሌላ ጥቅም መስጠትና ፍላጎት ማሟላት ይኖርባቸዋል»፤ በማለት ያስረዳል።

ተተኳሪ ማህበረሰብ ምክንያትና አጋጣሚን ወይም ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታን መሰረት በማድረግ ቃል ግጥሞችን ይከውናሉ። የሚከወኑና የሚዜሙ ቃል ግጥሞች የሴቶችን ሚና ማደላደል በማህበረሰቡ ዘንድ ሴቶች ያላቸውን ያታዊ ሚና እንዲቀጥል፤ ለሌሎች የቡድኑ አባላት የሚሰጡትን አገልግሎት ተከትሎ ምቹ የህይወት ዘመን እንዲፈጠር ያደርጋሉ። አስረበብ ምትኩ÷

የእኔ አስረበብ ምትኩ የስንዴ ክምር

እንዴት አማረባት ሴት ልጇን ስትድር፣

«ይህ እንግዲህ እኔም ሆንኩኝ ሌላሰው ልጁን ሲድር የሚዘፈንለት ነው»።

ልጅ የዳረማ ሰው እርጥብ ዳስ የጣለ

ቢሞት አይቆጭ አበባውን አይቶ ልጁን ደለደለ፤

«በልጁ ደስታ ከወዳጅ ዘመዱ ጋር ተደስቶ፤ ለቀጣይ ደግም ልጁን ተክቶ ቢሞት አይቆጭም» ትላለች (ቃለ መጠይቅ፣ ነሃሴ11/9/12/14 ዓ/ም) ። ይህም የመተካካትና የመደጋገፍ ፅንስ ሃሳብን የሚመለከት ነው። በተጨማሪም ትውልዳዊ ቅብብሎሽን የሚመለከት ሲሆን ከሚያስጨንቁ ጉዳዮች ጎን በመቆም የደስታ ምንጮችን መፈለግ የሚያስችል እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ከዚህም ባሻገር በተለያዩ የህብረተሰብ መዋቅሮች ሚናቸው ተለይቶ እንዲዘልቅ፤ ትውልዳዊ ቅብብሎሽ እንዲኖር ትልቅ ፋይዳ አለው።

በተተኳሪ ማህበረሰብ የሴቶችን ሚና ማደላደያ የሚያሳዩ ቃል ግጥሞች ሴቶችን በማህበረሰቡ ውስጥ እንዴት መኖር እንደሚችሉ፣ የሚሰጣቸውን ማህበራዊ ደረጃ ለመለየት፣ ሴቶች በቡድኖች አማካኝነት በጤነኛ አዕምሮ ተረጋግተውና ተስማምተው ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው እና ሰላማዊ ትስስር ተፈጥሮ በስርዓቱ ውስጥ እንዲኖሩ ያስችላቸዋል። ይህም የግጥሞች ተግባር ይታይበታል።

### 4.3.3. ማህበራዊ ፋይዳ

ማህበራዊ ፋይዳ ሲባል ቃል ግጥሞች እንደ ቅርፃቸውና አይነታቸው በከዋኝ ቡድኑ ውስጥ ስለሚገኙና ስለተለመዱ ልማዳዊ እሳቤዎችና ድርጊቶች በመግለፅ የጋራ መግባበትና አንድነት ላይ እንዲደርሱ የማድረግ ፋይዳ አላቸው። ብቸኝነትን በማስቀረት ግለሰቦችንና የማህበረሰቡን የርስበርስ ግንኙነት ያጠናክራል። የርዕስ በርዕስ ትስስራቸው ስለሚጠነክር በማህበረሰቡ ውስጥ ልማዳዊ ህጎችን በመቅረፅና በመተግበር የተለያዩ ክዋኔዎች እንደፈጠሩ ሚና አላቸው። ከሚፈጠሩት ውስጥ በሰርግ፣ በክርስትና፣ በጥምቀት፣ በክብረ ባዓልና በስራ ቦታዎች እንደ ማበረታቻ፣ ስሜት በመስጠትና በማዝናናት ረገድ ፋይዳ አላቸው።

በልቶ ጠጥቶ ዝም

የጋን ወንድም፣

አስረበብ ምትኩ «ቤተዘመድ በጋራ ሲበላ ሲጠጣ በደስታ ላይ ዝምታን ለመስበር የሁሉንም ተሳታፊ ወይም አባል ስሜት ለመቀስቀስና ለማገናኘት መተፋፈርን መስበር የሚያስችል ግጥም ነው። በጋራ መጫዎት መረደዳትን፣ መተሳሰብን ያንፀባርቃል»በማለት ትገልፃለች (ቃለ መጠይቅ፣ ነሃሴ 18/12/14 ዓ/ም) ። ይህ ደግሞ ተከታታይነት እንዲኖረውና እንዲከዎን ማህበራዊ እሴቶች እንዲጠነክሩ ጠቀሜታቸው የጎላ ነው። በሃዘን ጊዜም ቃል ግጥሞችን በማዜም የሟች ቤተሰቦችን በማበረታታትና በማፅናናት፣ ስለ ነበራቸው ማህበራዊ ሚና በመግለፅ ቃል ግጥሞች ጠቀሜታ አላቸው።

አየ ጉድ እናንት የእኔማ እንትና የሁላችን እናት፣ የደሳቹም እናት

እንግዲህ ምን ይሆን እሷን አፈር በላት፣

"ያው ይህን ሲባል እናትም፣ እህትም፣ ሚስትም ሌላም ልትሆን ትችላለች። የሟች ቤተሰብ የሆኑትን ሁሉ ሞት የፈጣሪ ስራ በመሆኑ አትዘኑ፣ እሷ ለሁሉም የምትራራ፣ ደግ፣ ጥሩ ሰው ነበረች። አሁን ግን አፈር ሁናለች አታለቅሱ ነው"(ቃለ መጠይቅ፣ ነሃሴ 18/12/14 ዓ/ም) ። በዚህም በሃዘን ውስጥ ለሚገኙ የቡድን አባላት ሃዘኑ የጋራ እንደሆነ በመግለፅ የመጋራትና የመረዳዳት ስሜት እንደሚፈጠር

የሚያሳዩ ቃል ግጥሞች እንዳሉ ለማወቅ ያስችላል፡፡ በተጫሪም ቃል ግጥሞች የመትከልና የማስተማር ተግባራቸው በቡድኖች እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡

ቃል ግጥሞች በማዝናናት መልክት በማስተላለፍ ከፍተኛ ጥቅም አላቸው፡፡ ይህም ሲባል ሴቶችን ስላላቸው ፆታዊ ወይም የሴትነት ሚናና ተግባር በማንሳት፣ በማዜም የቡድኖችን የማህበራዊ እና የርዕስ በርዕስ ግንኙነት እንዲዳብር ፋይዳ አላቸው፡፡ አቶ አስራት ዋለ÷

እረጅም መቀነት ሳይስቡት ይጠብቃል
የሽጋ ልጅ ፍቅር መቺ ቶሎ ይለቃል፣
ብወድሽ ነው እንጂ የማነክሰው
እኔ ራሴን ችየ ቁሜ የምሄድ ሰው፣

"በጥምቀት ወቅት ወንዱም ሴቱም አምረው፣ ተውበው የሚታዩበት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ዘፈን ሲነሳ ወንድ አቀንቃኝ የተነሳ እንደሆን ዙሪያ ገበውን፣ ሴት ቆነጃጅቶችን እያየ ይዘፍናል፡፡ ሴቶችም እየተሽኮረመሙ፣ ዘፈኑን ይቀበላሉ፣ ያጨበጭባሉ፡፡ አንዳንዶች የሚተጫጩበት ወቅት ነው"(ቃለ መጠይቅ፣ ነሃሴ 18/12/14 ዓ/ም)፡፡ በዚህም ወጣት ወንዶች በጥምቀት ጊዜ አቻቸውን ለማግኘት እና ሴት ተወዳጅነቷን፣ ለወንዶች ያላትን ፆታዊ ሚና ለመግለፅ ለመተጫጨት እንዲሁም ሌላ ህይወት ለመመስረት የሚጠቁሙ ቃል ግጥሞች ናቸው፡፡ በተጨማሪም አስራት ዋለ÷

ብወድሽ ነው እንጂ ቢያደላልሽ ሆዴ

እንደነፍሰ ገዳይ ዱር ለዱር መሄዴ፤ እንግዲህ በጥምቀትና ሌሎች ሰፊ ከበራዎች ላይ ዘፈን ከተነሳ ወጣት ወንዶች በደስታና በፈገግታ ሲፈኑ ሴቶችም የግጥሙን የወንዶችን ሁኔታ እየታዘቡ የደስታው ተከፋይ የሚመስሉበት ሁኔታ ይታያል፤ ይላል (ቃለ መጠይቅ፣ነሃሴ18/12/14 ዓ/ም) ፡፡ በዘፈን መልኩ የሚቀርቡና የሚዜሙ ቃል ግጥሞች በተተኳሪ ማህበረሰብ የቡድኖችን ማህበራዊ ተራክቦዎችን የሚያመላክቱና ሴት ለወንድ ልጅ ያላትን የፍቅር አሌንታ ስለመሆኗ ለማንጠባረቅ፣ ለማስተሳሰር ሚና ያላቸው እንደሆነ መረዳት ያስችላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5.ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሃሳብ

### 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በደብረታቦር ከተማ ለሴትነት ሚና ማደላደያ የሚገልፁ ቃል ግጥሞች ትንተናን ለማሳየት የቀረበ ነው። በዚህም ስለ ቃል የግጥሞቹን ሚና፣ በመተንተን እና ሴት በማህበረሰቡ ውስጥ ያላትን እንስታዊና ተግባራዊ ሚና ቅደም ተከተል በሆነ መልኩ፣ ገፅታና ትስሰሩን በመመርመር ለመተንተን ጥረት ተደርጓል። ሴት ልጅ በማህበረሰቡ ያላትን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሚና በመለየት እንዲሁም ሴት የምትዎከልበትን ማህበራዊ ቅርፅና ደረጃ በመመስረት በቃል ግጥም አማካኝነት እንዴት እንደሚገለጡ፤ ሚናዎችን በተደራጀ መልኩ በመመርመር፣ መተንተን ተችሏል።

በጥናቱ የተቀመጡትን ዓላማዎች ለማሳካት የምርምር ጥያቄዎችን  በማዘጋጀትና በመስክ ቆይታ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች ተግባር ላይ ውለዋል። በመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች አብዛኛዎቹ ተፈጥሯዊ መቼትን መሰረት ያደረጉ ሲሆኑ በአንፃሩ ሰው ሰራሽ ወይም አርቴፊሻል መቼት ተጠቅሜያለው።

ለሴትነት ሚና ማደላደያ የሚዜሙ ቃል ግጥሞች ትንተና በሶስቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች የተሰበሰቡትን መረጃዎች  ከእንስታዊ እና ከተግባራዊ ንድፍ ሃሳቦች ጋር በማያያዝ ገላጭ የትንተና ዘዴ ተጠቅሜያለሁ። በቃል ግጥሞች አማካኝነት የሚገለጡ የሴቶች ሚናዎችን የሚያሳዩ ቃል ግጥሞች

 ለማህበረሰቡ የሚያስገኙት ፍይዳዎችን በመለየት፣ በመመርመር የጥናቱ የመጨረሻ ግኝት የሆኑት የሚከተሉት ናቸው።

ለሴትነት ሚና ማደላደያነት በሚዜሙ ቃል ግጥሞች አማካኝነት ቡድኖች የተለያዩ አውዶችን መሰረት በማድረግ ሴት እናት፣ እህት፣ አክስት፣ አያት፣ አይት፣ ጓደኛ እና ሚስት ስትሆን የሚኖራት ቤተሰባዊ፣ ማህበራዊና ሀገራዊ ፋይዳዎች በቃል

ግጥሞች አማካኝነት በማዜም ይበልጡን በቡድኖች ውስጥ የማደላደልና የማመቻቸት ጉዳዮች እንዳሉ በጥናቱ ተደርሶበታል፡፡ ሴት በማህበረሰቡ በሚሰጣት ማህበራዊ ደረጃና የስራ ክፍፍል ፆታዊ ሚና፣ ትጉህ የቤተሰብ መሪ፣ ፍቅርና ደስታን በማብሰር፣ ጥላቻና ድክመትን ማቅለልና ተማኝ ጓደኝነት የሚሉት እና በሚዜሙ ቃል ግጥሞች የሴቶችን ጥንካሬና ብርታት፣መልካምነትን በመሰንዘር ለተተኪ ትውልዶች ፆታዊ ሚናቸው እንዲቀጥል ማድርግ መቻላቸው፤ ሴቶች በግልም ሆነ በቡድን የሚተገብሯቸው ማህበራዊ ድርጊቶች ለሌሎች ሴቶች ቡድኖች ተሞክሮ (ነግለኔ ብለው) እንዲያስቡ፣ እንዲረዳዱ የሚቀርፁ ሁነቶች መኖራቸውን ማረረጋገጥና የጥናቱ ግኝት ሁነው የቀረቡ ናቸው፡፡ እንዲሁም በቃል ግጥሞች አማካኝነት የሚገለጡ የፆታ ሚናዎች ለተጠኝ ማህበረሰብ ስነ ልቦናዊ፣ ተግባራዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች እንዳላቸው በጥናቱ ማወቅ ተችሏል፡፡ ቃል ግጥሞች ለከዋኝ ማህበረሰቡ እና በሚከዉኑበት አውድ የማህበረሰቡን የፈጠራ ኪነ ጥበብ ችሎታ ከማሳየቱ በላይ ሴት ልጅ ያላትን ሚና ማንፀባረቅ፣ መግለፅና ለተተኪ ትውልድ ማስተላለፍ እንዲቻል አስተዋፆኦ መኖራቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ሴት በቡድን ውስጥ ያላትን አይነተኛ ሚና የሚገልፁ የህዝብ የፈጠራ ስልቶች መካከል ቃል ግጥሞች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ቃል ግጥሞች በተተኳሪ ማህበረሰብ ዘንድ የሴት ልጅ ሚና ከትውልድ ትውልድ እንዲቀጥል፣ማህበራዊና ተግባራዊ የማህበረሰብ ግንባታዎች እንዲመሰረቱ እና እንዲስተካከሉ፤ ሴቶች እንዲደላደሉ አስተዋፆኦ መኖራቸውን ተደርሶበታል፡፡

## 5.2. የይሁንታ ሃሳብ

ለሴትነት ሚና ማደላደያ የሚዜሙ ቃል ግጥሞችን በመመርመር ለተተኳሪ ማህበረሰብ የሚሰጠው ፋይዳ እንዳለ በትንተና ክፍሉ ቀርቧል፡፡ የቃል ግጥሞች ምክንያትና አጋጣሚ ወይም ክዋኔ ማህበረሰቡ ይሁነን ብለው በቀረፁት ባህልና ልማድ የቡድን አንድነትን፣ መረዳዳትን፣ እንዲሁም ሴት እናት፣ ሚስት፣ አክስት፣ አይት፣አያት፣ ጓደኛ እና እህት ስትሆን የሚኖራት ሚና ወይም ደግሞ በልጅ አስተዳደግ፣ በቤት አመሰራረት፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባሮች አስተዋፆኦ እንዳላት የሚዜሙ ቃል ግጥሞች አካላዊና ስነ ልቦናዊ ርካታ እንዲያገኙ

ከማድረጋቸው ባሻገር ሴትነት የማደላደል ፋይዳ እንዳላቸው በጥናቱ ማረጋገጥ ችያለሁ። በመስክ ሂደቱም በአገኘውት መረጃ የእነዚህን ቃል ግጥሞችን ፋይዳ አለመረዳትና ሰንዶ አለማስቀመጥ ለትውልድ አለማሻገር ኋላቀር አመለካከት በሚል፣ በባህል በመበረዝ፣ በዘመናዊነት ፅንስ ሃሳብ እየጠፋ ይገኛሉ። እንዲሁም ሴት ልጅ በማህበረሰቡ ያላትን ማህበራዊ፣ ተግባራዊና ፆታዊ ሚና በሚገባ አለመረዳት፣ ተገቢውን የስራ ክፍፍል፣ ማህበራዊ ደረጃ አስጣጥ አናሳ መሆንና ተግባራዊ አለማድረግ በአንፃሩ የተመለከትኩት፣ የታዘብኩት ጉዳይ ነው።

በመሆኑም በቃል ግጥሞች አማካኝነት የሴቶችን ማህበራዊ፣ ተግባራዊና እንስታዊነት ሚና መግለጥ የሚያስችሉ በመሆናቸው የከተማው ባህልና ቱሪዝም እነዚህንና ሌሎች የፎክሎር ሃብቶች ይህን መሰል የጥናትና የምርምር ስራዎችን በማጠናከር በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያሳዩትን የመከባበር እና የመረዳዳት ፋይዳ በመረዳት ከመንግስት ስራ መመሪያዎች ዕቅዶች ጋር በማዛመድ ማህበረሰብ አቀፍ ተግባሮች ቢፈፀሙ፣ ክትትልና ድጋፍ ቢያደርግላቸው መልካም ነው። የዘርፉ ምሁራን በቃል ግጥም አማካኝነት የሚገለፁ ፆታዊ ሚናዎችን በተለያዩ አውዳዊ ከዎናዎች በመመዘን የሴቶች ማህበራዊ ፋይዳዎች በሚል ተለይተው መጠናት የሚችሉ ናቸው።

# ዋቢ መፅሀፍት

ሀብታም ግዛት ፡፡ (2006) ፤ "የዳባት ወረዳ ገበሬዎች የስራ ቃል ግጥሞች ክዋኔና ማህበራዊ ህይወታቸው"፤ አዲስ አበባ፣ ዩኒቨርሲቲ፤ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ሀብታም ተሾመ ፡፡ (2013) ፤"የጾታ ሚና አቀራረጽ ልማድ በሁለት እጁ እነሴ ወረዳ በደብረ ማርያም ቀበሌ ማሳያነት"፤ በባህር ዳር፣ ዩኒቨርሲቲ፣ ለፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ሰሎሞን ተሾመ ፡፡ (2007) ፤ <u>‹‹ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ››</u>፣ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ማተሚያ ድርጅት፡፡

አብዱራህማን ፈንታሁን: (2006) ፤ «የሐጅ ሁሴን ዓለሙ (የነሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በአል ስርዓትና ቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች) ክዋኔ ጥናት»፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት፡፡

ደበበ ኃ/ጊየርጊስ እንግዳ ፡፡ (1999) ፤ <u>"አዲሱ ምሣሌያዊ አነጋገሮች"፣</u> አስቴር ነጋ የግል ማተሚያ ድርጅት፡፡

ደብረ ወርቅ ሞላ ፡፡ (2010) ፤ "የአሆላሌ ጨዋታ ቃል ግጥሞች ፋይዳ ትንተና" በአምባሰል፤ አዲስ አበባ፣ ዩኒቨርሲቲ፣ ለማስተርስ ዲግሪ፣ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

የደብረታቦር ከተማ አስዳደር ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት፣ (2003) ፤ ስለ ደብረታቦር ከተማ ገጽታ የተዘጋጀ መጽሄት

ያለው እንዳወቀ፡፡ (1998) ፤<u>‹‹የምርምር መሰረታዊ መርኖዎችና አተገባበር››</u>፣አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ የስነ ጽሁፍ መሰረታውያን፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓም

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1991) ፤ "<u>የሥነ -ቃል መምሪያ"፤</u> አዲስ አበባ፤ ኢትዮ ጥቁር አባይ አሳታሚዎች፡፡

Barni D. et al. (2017). Personal and Family source of Parents Socialization Values: A multilevel Study. Italy: LUmsa University of Rome.

Brown, R. R.A. (1935). On The Concept of function in social Science. American, part1, Anthropologist, New series, vol.37, no.3, Part 1, pp.394—402, Blackwell Publishing on Behalf of the American Anthropological Association.

Brunvad, V. (1979). Reading American Folklore.

Dorson, M.R. (1972). <u>Folkloreand Folklorelife</u>: An Introduction Chicago and London, The University of Chicago press.

Hirdmann, Y. (1996). Key concepts in feminism theory; Analyzing gender and welfare. Department of history, international and social studies, Aalborg university, FREIAs teksisere no,34 http//do.org/10.5278/frela.141136339

Javeed, A,R.(2017). Feminism; An overview, international journal of research, M.A, set English, university of Kashmir,https// edupediapublications.org/journals/index.php/lir, javied34αgmial.com.

Finnegan Ruth. (1970). *Oral Literature in Africa*. Nairobi, Kenya. Oxford Unversity Press.

Genilloud G. and Wegman A. (2000). A New Definition for the Concept of Role, and Why it Makes Sense.

Goldestein, K. (1964).A Guidefor Filed works in Folklore. London, Sage Publication, Thousand, OAKS Newdelhi.

Lipner, L., M., mendelsohn, R. & muran, J. C. (2017). The Sage Encyclopedia of Abnormaland Clinical Psychology, psychoanlysis, Thousand Oaks, SAGE Publicatios, Inc.

Nicole, K. (1999). Feminist theory and folklore. Folklore forum, 30/;1/2 1999.

Mack, N., woodsong, C., Macqueen K. M., Guest, G. & Namey, E.

(2005). Qualitative Research methods: a data Collctions Field Guide, Family Health Internayional, Research Triangle Park, North Carolina (USAID).

Malinowski,B. (1939).Sex and Repression inSavage Society,London and New Work, Kegan Paul, et al co.ltd.

Masolo, C. (2004). *Social Roles and thier Descriptions.* Rome, Italy.

Mesfin, M. (2000) Abba Wudde Oral Poetry in South Wollo Auiscriptive

Analysis፣ MA thesis Addis Abeba Unversity .

Mila, A. (2020). Feminism; equality gender in literature, see discussion, universty of baturaja, stats and auther profile for this publication at, https// www.reseachgate.net/publication/3444186149

Perez I.et al. (2015). Social Roles and Performance of Social Ecological Systems: Evidence from Behavioural Lab Experments .

Saps Ford, R. & Jupp, V. (2006), *Datacollction and Analysis*, 2nd (Ed), In Association with the Open University, London.Thousand. New Delhi, SAGE Publication.

Sunstein, C. R. (1996). *Social Norms and Social Roles.* Chicago.

## አባሪ1. በአካባቢው የሚዜሙ የፍቅር ቃል ግጥሞች

- የሆዴ ሰመመን የልቤ መብራት

  ወዳንች ስመጣ መታኝ እንቅፋት

- ብወድሽ ነው እንጂ ቢያደላልሽ ሆዴ

  እንደነፍሰ ገዳይ ዱር ለዱር መሄዴ

- እረጅም መቀነት ሳይስቡት ይጠብቃል

  የሸጋ ልጅ መቺ ቶሎ ይለቃል

- እናትስ አትሙት ትኑር አጎብሳ

  ታወጣለች ተባይ በጨለማ ዳብሳ

- አንችን የመሰለ መልካም ቆንጆ ሳይ

  እንባየ ይፈሳል በደረቴ ላይ

- ከሮዝ አበባ ላይ አሞኝ ተኝቻለሁ

  ፍቅሬን አስጨርሽኝ እሞትብሻለሁ

- ሰው ሁሉ ይመኛ ወርቅና ጎትቻ

  እኔ እምፈልገው ፍቅርየ ብቻ

  በሶስት ፊደል ቀመር ተሰርቶ'ላት

  ቀላል ትመስላለች እናት ሲሏት

- እጅግ የምታምር አለም አስደናቂ

  አዛኝ በመሆኗ በሰዎች ታዋቂ

  አብልታ አጠጥታ ጤናችን ጠባቂ

- ምን ብየ ልጀምር እግዲህ ካንጀቴ

ምግብ መገበችኝ በ'ትብቷ እናቴ

ዘላለም ኑሪልኝ  ህይወት መሰረቴ

የፍጠራንን ዘር አግኝተሽ ከአባቴ

አንችን አልኩኝ እጅ ውቢቱን ውቢቱን

እነግሚትማ ሞልተውታል ቤቱን

ከታማሁኝ አይቀር ከተባልኩኝ ሌባ

በኩታየ አዝየህ ልግባ አዲስአበባ

እኔ ደሮ ሁኝ በጎሮ ስጭር

አንተ አሞራ ሁነህ ይዘህኝ ብረር

እንኮን ጋራ ዙርሽ እንኮን ጋራዙሬ

ትናፍቂኝ አለሽ አብሬሽ አድሬ

አይኑ ጎላ ጎላ የትሙቡሃ ፍሬ

አንተን የወለዱ መልካም ሽማግሌ

## አባሪ 2. አብይ የመረጃ ምንጮች÷

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዩ ስም | ፆታ | ዕድሜ | አድራሻ | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ትብለጥ አንዳርጌ | ሴ | 45 | ህሩይ | የቤት እመቤት |
| 2 | አስራት ዋለ | ወ | 60 | ህሩይ | አስለቃሽ |
| 3 | ነጋሽ ቢምረው | ወ | 40 | አስፋው ሰፈር | የቤተ/አገልጋይ |
| 4 | አለሚቱ ውዱ | ሴ | 50 | አሰፋው ሰፈር | የቤት እመቤት |
| 5 | አስረስ ምትኩ | ሴ | 54 | ፀጉር ሜዳ | የሴቶች ማህበር ሰብሳቤ |
| 6 | ወ/ሮ አትጠገብ መልኬ | ሴ | 49 | ፀጉር ሜዳ | የቤት እመቤት |

## አባሪ ÷ 3. አጋዥ የመረጃ ምንጮች፤

| ተ/ቁ | የመረጃ አቀባዩ ስም | ፆታ | እድሜ | አድራሻ | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ከበረ መላክ | ወ | 44 | ፀጉርሜዳ | ገበሬ |
| 2 | አቶ ሞገስ ደማሙ | ወ | 54 | ህሩይ | ገበሬ |
| 3 | አቶ ሞላ ጥጋቡ | ወ | 60 | አስፋው ግራር | ገበሬ |
| 4 | ወ/ሮ አየለች ደማሙ | ሴ | 34 | ፀጉርሜዳ | የቤት እመቤት |
| 5 | አቶ ሽበሽ ፀጋ | ወ | 70 | አስፋው ግራር | ገበሬ |
| 6 | ወ/ሮ አስካለ | ሴ | 42 | ህሩይ | የቤት እመቤተ |
| 7 | መ/ር ትግሰት | ሴ | 38 | አስፋው ግራር | መ/ር |
| 8 | አቶ ሙሉጌታ አስማረ | ወ | 56 | ፀጉርሜዳ | እስለቃሽ |
| 9 | ወ/ሮ አስረበብ ትኩ | ሴ | 52 | አስፋው ግራር | የቤት እመቤት |
| 10 | ሊቀ መኳስ አደራጀው | ወ | 45 | ህሩይ | አዝማሪ |